አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድኅረ ምረቃ

መርሐ ግብር

# የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

መሪማ መሐመድ

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድኅረ ምረቃ

መርሐ ግብር


በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ


መሪማ መሐመድ

አማካሪ

ዘላለም መሠረት (ዶ/ር)


ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት የድኅረ ምረቃ

መርሐ ግብር

# የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

መሪማ መሐመድ

2009 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ፊርማ

_______________ _______________

_______________ _______________

የፈታኝ ስም ፊርማ

1. _______________ _______________
2. _______________ _______________

# ምስጋና

ይህንን ጥናት በማዘጋጅበት ወቅት በተለያዩ መልኩ እገዛ ያደረጉልኝ አካላት በርካታ ናቸው፡፡ የጥናቱ አማካሪ ዘላለም መሠረት (ዶ/ር) ረቂቁን ጽሑፍ በማንበብ፣ ለጥናቱ አቅጣጫ በመጠቆም እና በዳበረ ልምዳቸው ጥናቱ መልኩን እንዲይዝ በማድረግ ለጽሑፉ ዳር መድረስ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉ ባለውለታ ናቸው፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህንን የትምህርት ዕድል እንዳገኝ በማድረጉ እና ለጥናቱ መሠረታዊ ወጪዎች ድጋፍ በመስጠቱ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል፡፡

ጊዜያቸውን በመሠዋት የሚያውቁትን ሁሉ በማካፈል ፈቃደኛ የሆኑልኝን መረጃ አቀባዮቼን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ለወራት በሕመም ከቆዩበት ዐልጋ ላይ በመነሣት "ይህንን ታሪክ ይገኙ እንዳልሞት የተላክሽልኝ ነሽ" በማለት በእድሜያቸው ሁሉ የሚያውቁትን ታሪክ የነገሩኝን የዘጠና ዓመት አባት የሆኑትን መምሬ ልሳነ ወርቅ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ምንም እንኳን አንድ አጥኚ ለጥናት ቢነሣሣም ያለ መረጃ አቀባዮች ምንም ማድረግ አይቻልምና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም ያለ እኔ ልጆቻችንን ይዘህ "ለእነርሱ እኔ አለሁ፡፡ አንቺ ብቻ በርቺ!" እያልክ ትምህርቴ ላይ እንዳተኩር ላበረታታኸኝ ውድ ባለቤቴ አንተነህ ባያብል እና ምንም እንኳን ሦስት ዓመት ቢሆንሽም "እናቴ ዛሬ እናንብብ" እያልሽ ለምታነሣሽኝ ውድ ልጄ አቅለስያ አንተነህ ለእገዛችሁ ምስጋናዬ ከልቤ ነው፡፡ ይህንን ጥናታዊ ጽሁፌን ደከመኝ ሳትል በትእግስት ለተየበችልኝ አዜብ ቦጋለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ለጥናቱ አስተዋፅኦ አድርጋችሁ በዝርዝር ያልተጠቀሣችሁ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**ማውጫ**


ርዕስ ገፅ

ምስጋና ..... I

የሰንጠረዥ ማውጫ ..... V

አጠቃሎ ..... VI

ምዕራፍ አንድ ..... 1

1. መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ አደረጃጀት ..... 1

1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች ..... 2

1.3. የጥናቱ ዐላማዎች ..... 2

1.3.1. ዋና ዐላማ ..... 2

1.3.2. ዝርዝር ዐላማዎች ..... 2

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3

1.5. የጥናቱ ወሰን ..... 3

1.6. የጥናቱ ዘዴ ..... 3

1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ..... 4

1.6.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..... 5

1.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 5

1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ..... 5

1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ..... 7

1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ርምጃዎች ..... 7

ምዕራፍ ሁለት ..... 8

2. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ..... 8

2.1. የገዳም ምንነት ..... 8

2.2. የገዳም ሕይወት ጅማሮ በኢትዮጵያ ..... 9

2.3. የገዳም ሕይወት የአኗኗር ሥርዓት (ደንብ)....................................................11

2.2. የተረክ ንድፈ ሐሳብ........................................................................................15

2.2.1.1. ሚት........................................................................................16

2.2.1.2. አፈ-ታሪክ....................................................................................17

2.2.1.3. ተረት........................................................................................17

2.3. የኦክፔውሁ የተረክ አከፋፈል...................................................................19

2.3.1. አፈ ታሪክ........................................................................................19

2.3.2. ገላጭ ተረቶች...................................................................................19

2.3.3 ፋቡላ................................................................................................20

2.4. ተረክን የማጥናት ጠቀሜታና የአጠናን ሥልት...............................................20

2.5. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ................................................................................21

2.6. ቁሳዊ ባህል...............................................................................................23

2.6.1.የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች.......................................................25

2.7. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት...............................................................................26

2.7.1. በቅድስት ሥላሴ የሥነ መለኮት ኮሌጅ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ................26

2.7.2. በታሪክ ትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ.................................28

2.7.3. በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተደረጉ

ጥናቶች ክለሳ..........................................................................29

ምዕራፍ ሦስት..................................................................................................36

3. ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራና የተያያዥ ጉዳዮች ዳራዊ ገለጻ.......................................36

3.1. ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራ መልክአ ምድራዊ ገለጻ...........................................36

3.2. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት ...................................39
3.3. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የሰንበት ትምህርት
ቤት አመሠራረት.........................................................................................42
ምዕራፍ አራት .............................................................................................46
4. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች እና
ቁሳዊ ባህሎች ትንተና ..................................................................................46
4.1. ከእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች ትንተና............46
4.1.1 የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች..................................................46
4.1.2. የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች...............................................48
4.1.3. የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮች ........................................51
4.1.4. የገዳሚን ቅድስና የሚዘክሩ ትንቢት ነክ ተረኮች....................................53
4.1.5. ከተአምር ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ..........................................56
4.1.5.1. በቁጣ (በራእይ) መልክ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ
በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች..........................................................................59
4.1.5.2. በራእይ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች.......62
4.1.6. በፈውስ መልክ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ......65
4.2. በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና ......72
4.2.1. ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት የሚያገለግሉ ቁሶች.........73
4.2.2. ሥርዓት አምልኮን ለመፈጸም የሚያገለግሉ ቁሶች ......................................78
ምዕራፍ ዐምስት ...........................................................................................84
5.1. ማጠቃለያ..................................................................................................84
5.2 የይሁንታ ሐሳቦች ........................................................................................85
ዋቢ ጽሑፎች..................................................................................................86
ዐባሪዎች .........................................................................................................1
ዐባሪ አንድ ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች.........................................................1
አባሪ ሁለት፡ ከገዳሚ የተሰበሰቡ ፎቶዎች .........................................................11
አባሪ ሦስት፡ መረጃ ለመሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች ...........................................16

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ዐባሪ አራት፡ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ ........................................................ 19
ዐባሪ አምስት፡ የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ንብረቶች ........................................ 21
ዐባሪ ስድስት፡- የገዳሚ ካርታዎች ......................................................................... 24

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ላይ የተካሄደ ሲሆን ከፎክሎር ዘውጎች ውስጥ የሚገኙትን ቁሳዊ ባህሎች እና ተረኮች መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሣው ዋና ዓላማም ተረኮቹ እና ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳማውያኑና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ያላቸው ፋይዳ መመርመር እና ተምሳሌታቸውን ማሳየት የሚል ነው፡፡ በርእሰ ጉዳዩ መመረጥ እንደ ዓቢይ ምክንያት የሚጠቀሡት የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ከ1500 ዓመት በላይ ያስቆጠረች ቢሆንም በገዳሟ ዙሪያ ላይ በቂ የሆኑ ጥናቶች አለመድርገቸው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የራሱ የሆነ የሚያበረክተው ነገር ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የጥናቱ ዐላማ ግብ ይመታ ዘንድ የምርምር ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲያገኙ መረጃዎች ከቤተ መጻሕፍት እና ከመስክ ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎችም በካሴት፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በካሜራና በማስታወሻ ደብተር በማጠናቀር መረጃዎቹ ከግብ ለማድረስ ተችሏል፡፡ በእነዚህ አማካኝነት የተሰበሰቡት ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በተረክ ንድፈ ሐሳብ፣ በቁሳዊ ባህል ፅንሰ ሐሳብ ሞዴሎችንና ተረክንም ሆነ ቁሳዊ ባህልን ለመፈከር በሚያስችለው በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ተተንትነው በገለጻና ትንተና ሥልት ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

በጥናቱ እንደታየው በእንጦጦ ሐመረ ኞኅ ኪዳን ምህረትገዳም ውስጥ ከሚተረኩት ትረኮች መካከል አባ ሊባኖስ ወደዚህች ገዳም ከመጡበት ጊዜ አንስቶ እንደሆኑ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህችም ገዳም ፈጣሪ ለመስራቹ በራዕይ ታቦቷን በማሳየት የተመሰረተች መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህም ተረክ ለጋዳማውያኑ ይህች ገዳም እንዴት ተመሠረተች ለሚለው ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቹ የገዳሟን ጥንታዊነት እና ታሪካዊነት የመዘከር፣ የስፍራዋን ክብር ከፍ የማድረግ፣ የስፍራዋን ቅድስና የመስበክ ሚና እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቁሳዊ ባህሎቹመረጃዎች አጠቃላይ እንድምታ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የጥበብ ዕሴት መገለጫ፣ የመንፈሳዊ ዕሴት ነጸብራቅ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ መሆንዋ በጥናቱ ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የሃይማኖት መታገጊያ፣ የማንነት ማጽኛና መገንቢያ መሣሪያ መሆናቸው በጥናቱ በሰፊው ተመልክቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በዐምስት ክፍሎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ፣ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዐላማ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች በቅደም ተከተል የቀረቡበት ነው፡፡

በሁለተኛው ክፍል የገዳማውያንንሕይወት፣ ተረክን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ፅንሰ ሐሳቦች እንዲሁም ከጥናቱ ጋራ በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ተዳሰዋል፡፡ ምዕራፍ ሦስት የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አጠቃላይ ገለጻ በሚል ርእስ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረትን ገዳም የአመሠራረት ታሪክ፣ ቅርስና መልከአ ምድራዊ ሁኔታ የሚያስቃኝ ትንተና የቀረበበት ነው፡፡

ምዕራፍ አራት ከመስክ የተሰበሰቡ ተረኮችና ባህላዊ ቁሶች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

ዐምስተኛው ምዕራፍ ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች ይዟል፡፡ ዋቢ ጽሑፎች እና ዐባሪዎች በጥናቱ መጨረሻ ላይ ቀርበዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ላይ ይህንን ጥናት ለማድረግ ካነሣሡኝ ምክንያቶች መካከል

- በአንድ የትምህርት ጉዞ አማካኝነት ገዳማትን በጎበኘሁበት ወቅት ከገዳማቱ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩትን ተረኮች መስማቴ እና ገዳማት ውስጥ ያሉት ማኅበረሰቦች የሚገለገሉባቸውን ቁሶች ማየቴ፣ይህም ቢጠና የሚያበረክተው የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ይኖራል ብዬ ማሰቤ፣
- የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም 1500 ዓመት እንዳስቆጠረች መዛግብት ቢጠቁሙም በገዳሟ ላይ በቂ የሆኑ ጥናቶች አለመደረጋቸው በተረኩና በቁሳዊ ባህሉ ላይ የተደረጉ ጥናቶች አለመኖራቸው፣
- በገዳሟ የሚገኙት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች የሚኖራቸውን ማኅበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ያለኝ ፍላጎት ማየል የሚሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዐላማዎች

### 1.3.1.ዋና ዐላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዐላማ ከእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና በገዳሟ ውስጥ የሚገኙት ቁሳዊ ባህሎች ለገዳማውያኑና ለእምነቱ ተከታዮች የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ይሆናል፡፡ ከዚህ ዋና ዐላማ በመነሣትም ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዐላማዎች ይዟል፡፡

### 1.3.2.ዝርዝር ዐላማዎች

- የገዳሟን አመሠራረት ታሪካዊ ሁኔታ መመርመር፣
- በገዳሟ ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን መግለጽ፣
- ከገዳሟ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ተረኮች መተንተን

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ላይ መደረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- ስለ ገዳሟ አመሠራረት እንዲሁም ከገዳሟ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ታሪኮች ለመመርመር ለሚነሡ አካላት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል
- በተረኮችና በቁሶች መካከል ያለውን ተያያዥነት በማሳየት ረገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፣
- ተረኮቹና ቁሶቹ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በተወሰነ ደረጃ ሊኖራቸው የሚችሏቸውን ጠቀሜታዎች በማሳየት ጥናቱ የራሱ የሆኑ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት ታሪክጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ጥናቱ ገዳሟ ለመመስረቷ እንደ ምክንያት በሚጠቀሱ ጉዳዮች እና ከዚም ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮች እንዲሁም በቁሳዊ ባህሎች ላይ ትኩረት በማድረግ ተርኮቹም ሆኑ ቁሶቹ ለገዳሟ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምን ይመስላል በሚሉት ላይ ትኩረትን አድርጓል፡፡ ይህች ገዳም በውስጧ ወንዶች ምነኮሳት እና ሴቶች መናኮሳይያት በአንድነት ይኖሩበት የነበረች ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት የሴቶች ገዳም በውስጡ ሦስት መነኮሳይያት ብቻ ያሉበት በመሆኑ ከገዳሟ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች በቃልም ሆነ በጽሑፍ ባለመገኘታቸው ይህ ጥናት በወንዶች ገዳም ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.6.የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የገዳሟን አመሠራረት፣በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩትን ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች መመርመር በመሆኑ ገላጭ የምርምርዘዴን /descriptive study/ እና ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን /functionalism Approach/ በመጠቀም መረጃዎችን ተንትኗል፡፡

### 1.6.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከቤተ መዛግብት ፍተሻ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ አማካኝነት ነው፡፡ በአብዛኛው ክፍት ቃለ መጠይቅ እንዲሁም ስምምነታዊ ምልከታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ቀዳሚው የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው የቤተ መዛግብት ፍተሻ ነው፡፡ በዚህም አማካይነት ከመስክ በፊት ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎች፣ ከጥናቱ ጋራ የተያያዙ ዕሳቤዎችና የትንተና ማካሄጃ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራዎች ተዳሠዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መካከል ቃለ-መጠይቅ አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ዘዴ በመጠቀም የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት ገዳም አመሠራረት፣ ከገዳሟ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን አስመልክቶ የተለያዩ የገዳሟ ማኅበረሰብ አባላት ያላቸው ዕውቀት፣አመለካከትምን እንደሚመስሉ መረጃ ማግኘት ተችሏል፡፡

መረጃዎቹም በአጠቃላይ የተሰበሰቡት በገዳሟ ውስጥ እና በገዳሟ ዙሪያ ከሚኖሩ በዕድሜ የገፉ አባቶችን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ በቃለ መጠይቆቹ በአጠቃላይ ከአርባ በላይ የሚሆኑ ተረኮች ተገኝተዋል፡፡ ከተገኙት ተረኮች መካከል አብዛኞቹ የመረጃ ሰጪዎቹ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በስሚስሚ የሚያውቋቸው ናቸው፡፡

የመረጃ አቀባዮቹ አብዛኞቹ ከሠላሳ ዓመት በላይ በገዳሟ እና በአካባቢው የኖሩ የተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎች የነበሯቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህም አካላት መረጃ ለመሰብሰብ በአብዛኛው ክፍትቃለ መጠይቅ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መረጃ ሰጪዎቹ ያለ መረጃውንበነጻነት ስሜት እንዲሰጡኝ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

በዚህ መንገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ወደ ጽሑፍ ሲቀየሩ በተቻለ መጠን የተናጋሪውን የዐረፍተ ነገር አሰካክ እንዳለ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ አንዳንዴም በተቻለ መጠን ይህንን እንዲያመላክቱ ያስችል ዘንድ ቀበልኛ ይዘት ያላቸውን ቃላት  በተቀራረቡ ፊደላት ለመተካት ተሞክሯል፡፡ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል አንዳንድ ድግግሞሾች እና ከርእሰ ጉዳዩ ጋራ ግንኙነት የሌላቸው ወደ ጽሑፍ ሳይቀየሩ ቀርተዋል፡፡ ከቃለ መጠይቁ በተጨማሪ ስምምነታዊ የምልከታ ዘዴ ቁሶቹን ለመሰብሰብ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ምልከታ አጥኚው በክዋኔው ቦታ ላይ ተገኝቶ በመረጃ ሰጪዎች የሚነገሩትን መረጃዎች በአይኑ በማየትና በማመሳከር መረጃውን የሚያጎለብትበትኃይልነው፡፡ በዚህ መሠረትም በገዳሟ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቁሶች አገልግሎታቸው ምን እንደሚመስል፣ መቼ፣መቼ

እንደሚገለገሉባቸው፣ እነማን እንደሚጠቀሙባቸው ቁሶቹን በመመልከት መረጃ ማግኘት ተችሏል፡፡

### 1.6.2.የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በፎክሎር ጥናት ዋንኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከሆኑት መካከል ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ አጥኚዋ ተጠቅማለች፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የተገኙት መረጃዎች በቪዲዮ ካሜራ ተቀድተው፣ በፎቶ ግራፍ ተነሥተው፣ በመቅረጸ ድምፅ ተቀድተው በማስታወሻ ተጽፈውና ተሰንደው ተይዘዋል፡፡

### 1.7.የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ የጥናት ዘርፍ ተረኮቹን እና ቁሳዊ ባህሎችን ለመተንተን ከሚያስችሉ ንድፈ ሐሳቦች መካከል ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ቀዳሚው ነው፡፡ እንደ ንድፈ ሐሳቡ አቀንቃኝ እንደ Willam Bascom አገላለጽ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማኅበረሰቡ ወይምለፎክ ቡድኑ የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን ዐውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህም ጥናት በገዳሚ የሚነገሩት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ገዳማውያኑን በማስተማር፣ በመግታት እና በመቆጣጠር ረገድ ያላቸው ሚና ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በተጨማሪም ይህ ጥናትየቁሳዊ ባህሎችን አጠቃላይ ገጽታ ለማሳየት ገላጭ እና ተንታኝ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በመጨረሻም ባህላዊ ተረኮቹ እና ቁሶቹ ያላቸውን ትእምርታዊ ፍቺ አሳይቷል፡፡ David ትእምርት አንድን ነገር ወክሎ የሚገኝ ማንኛውም ነገር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ትእምርት የሁለት ነገሮች ጥምረት ነው፤ አንደኛው በዐይን የሚታይ እና ተጨባጭ ምልክት ሲሆን ሁለተኛው ከሚታየው ወይም ከሚሰማው ነገር ጋራ የተያያዘ ሐሳብ ነው፡፡ ይህም ጥናት ተረኮቹ እና ባህላዊ ቁሶቹ ያላቸውን ጥምረት እና ትእምርታዊ ፍቺያቸውን በሰፊው ተንትኗል፡፡

### 1.8.ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

ጥናቱ ተጀምሮ እንከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የታለፉባቸው የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህንም በዚህ ሥር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ጥናቴን “ሀ” ብዬ ከመጀመሬ በፊት ስለ

እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ዙሪያ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች የተፃፉ መጽሐፍቶች እና መጽሔቶችን በመፈለግ ተመልክቻለሁ፡፡ ወደ ገዳሟ በመሄድ ለጥናቴ ግብአት የሚሆኑኝን መረጃዎች ሊያቀብሉኝ የሚችሉ ሰዎችን ለማግኘት ሞክሬያለሁ፡፡ ይህንንም ሙከራ ወደ ገዳሟ ለአራት ጊዜ በመመላለስ አካሂጃለሁ፡፡ይሁን እንጂ መረጃ ሰጪዎቼ ነጻ ሆነው መረጃውን ሊሰጡኝ የሚችሉት ደብዳቤዎችን ከተለያዩ አካላት አጽፌ ሳመጣ እንደሆነ በመረዳቴ ከትምህርት ክፍሌ ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ከዚያም ጥናቱ ወደ ሚካሄድበት ገዳም ለመውሰድ ችያለሁ፡፡ይህም ሂደት ከ20 ቀን በላይ የወሰደ ነበር፡፡ ከገዳሟ ጥናቱ እንዲካሄድ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ጥናቱ ተሠርቶ እስኪጠናቀቅ ለስምንት ሳምንታት ያህል ወደ ገዳሟ በተለያዩ ጊዜያት ተመላልሻለሁ፡፡ ቀዳሚው ጉዞ በቤተ ክህነት ደብዳቤ በማፅፍበት ወቅት ደብዳቤውን በመምራት ሥራ ላይ በተሰማራው በብርሃኑ ኢሳያስ አማካኝነት መረጃ አቀባይ የተጠቆምኩትን እና መረጃ አቀባዮቼን አግኝቼ ያነጋገርኩበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ከዚህ ሰው ጋራ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን እንደሚያገናኘኝ ተነጋግረን በቀጠሮ ተለያይተናል፡፡ በቀጣይም በቀጠሮው መሠረት በመጋሚ በመገኘት ይጠቅምሻል ያሉኝን በርካታ ግለሰቦች የተዋወኩበት እንዲሁም ከጥቂቶቹ ጋር በዚያው እለት የተወሰኑ ቃለ ምልልሶችን በማድረግ መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በተጨማሪም በእነዚሁ ግለሰቦች አማይነት ከእኛ የተሻሉ ናቸው፤ ጽሑፋዊ መረጃዎችን ከቤታቸው የሚያስቀምጡ ለታሪክ ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ናቸው ያሏቸውን ሰዎች የጠቆሙኝና እንዳገኛቸው የረዱኝ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ በዚህም አማካይነት ጥቂቶቹ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆናቸው ቃላዊውንም ጽሑፋዊውንም መረጃ ለማግኘት የቻልኩበት ጉዞዬ ነበር፡፡ እነኚህም ሂደቶች ከየካቲት 17 እስከ መጋቢት 5 ቀን 2009ዓ.ም ባሉት ቀናት ውስጥ የተከናወኑ ነበሩ፡፡ በሦስተኛው ጉዞዬ ከዚህ ቀደም የሰበሰብኳቸው መረጃዎች አብዛኞቹ ተረኩ ላይ ያተኮሩ ስለነበሩ በዚህኛው ጉዞዬ ቁሳዊው ላይ በማተኮር በገዳሟ ያሉትን የዕቃ ቤት ኀላፊ አባ ኪዳነ ማርያምን በማነጋገር ከገዳሟ ጋራ ተያይዘው የሚገኙ ቁሶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲነግሩኝና ቁሶቹንም እንዲያሳዩኝ በመጠየቅ ቁሳዊ መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ቁሶቹም በዕቃ ቤት አሁን ላይ አገልግሎት በማይሰጠው ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

በገዳሟ ዐጥር ግቢ ውስጥ እና ውጪ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቁሶች አባ ኪዳነ ማርያም አማካይነት፣ ከግቢ ውጪ የሚገኙትን ደግሞ ከመሪጌታ ነቅዐ ጥበብ፣ ከዲያቆን ፈቃደ ከመምሬ ልሳኑ አማካይነት በተለያዩ ጊዜያት መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ይኸውም ከመጋቢት 10 እስከ 23 ቀን 2009 ዓ.ም ባሉት ቀናት የተፈጸመ ነው፡፡ የመጨረሻው ጉዞዬ እስከ አሁን የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በድጋሚ ያመሳከርኩበት በውሰት መልክ ከገዳሟ መረጃ አቀባዮች የወሰድኳቸውን ለጥናቴ ግብአት የሆኑትን የተለያዩ መረጃዎችን የመለስኩበት እና (በርካታ መረጃ ሰጪዎቼ መረጃውን ቤታቸው ድረስ ሄጄ ያፈራውን ከእነርሱ ጋር እየተመገብኩ እንድሰበስብ ከጥናቱ ባሻገር እንደ ቤተሰብ እንድሆን አድርገውኝ ነበርና) ለዚህ ሁሉ ምስጋናዬን ያቀረብኩበት ነው፡፡ ለዚህም በገዳሙ ለ10 ቀናት በተከታታይ ተመላልሻለሁ፡፡ ይህም ከሚያዚያ 2 እስከ ሚያዚያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም የቆየ ነው፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች

### 1.9.1.ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ርምጃዎች

በጥናቱ ወቅት ሥራውን ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ችግሮች በጥቂቱም ቢሆን ገጥመውኝ ነበር፡፡ በችግሮቹም መካከል ከገዳሟ ፈቃድ አለማግኘት ስሜ መሪማ መሐመድ በመሆኑ መረጃ ሰጪዎች መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ለታሪኩ ቅርብ ናቸው የተባሉት አባቶችም መረጃውን ከመስጠት ይልቅ “እገሌ ይንገርሽ፣ እኔ ብዙም አላስታውሰውም” ማለት እና በቀጠሮው ቀን አለመገኘት የሚሉትሊጠቀሡከሚችሉት ችግሮች መካከል ናቸው፡፡

ከፈቃዱ ጋራ በተያያዘ ፈቃዱን እስኪሰጡኝ ድረስ በቤተ መጽሐፍት ያሉ አንዳንድ መረጃዎችን ስጠቀም ቆይቻለሁ፡፡ ስሜን በተመለከተ ክርስትና መነሣቴንና በአሁኑ ሰዓት የክርስትና እምነት ተከታይ መሆኔን በመናገር እንዲሁም ለሌሎች መረጃ አቀባዮቼ በክርስትና ስሜ እራሴን በማስተዋወቅ ችግሩን ለመፍታት ችያለሁ፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቼ ላይ የነበረውን ሥጋት ለመቅረፍ ከዩኒቨርሲቲ እና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ሕጋዊ ደብዳቤ አምጥቼ ለገዳሟ ኀላፊዎች መስጠቴን በመንገር፣ በሚያውቋቸው ሰዎች በድጋሚ ወደ እነርሱ በመሄድ ሰዎቹ መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩኝ ስለነገሯቸው እኔም የገዳሟ ታሪክ መጠናቱ ለገዳሟ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው በመንገር በመረጃ አቀባዮቼ በኩል የነበረው ችግር ሊቀረፍ ችሏል፡፡ የመጨረሻው የነበረው በቀጠሮው ያለመገኘት ችግር ሌሎች ተደጋጋሚ ቀጠሮችን በመያዝ በአብዛኞቹ መፍትሔ ላይ ተደርሷል

**ምዕራፍ ሁለት**

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ ቀዳማዊው ለጥናቴ እንደ መታገኒያ በመሆን የሚያገለግሉት የፎክሎር ጉዳዮች የሚዳሠሡበት የንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ክፍል ሲሆን ካልዓዩ ደግሞ ከእኔ ጥናት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው የምርምር ሥራዎች የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቶች ናቸው፡፡

## 2. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

ለጥናቱ መሳካት በዋናነት ትኩረት የምሰጥባቸው የገዳም ምንነት፣ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህል (material culture) ንድፈ ሐሳቦች ናቸው፡፡ በዚህም ዙሪያ የፎክሎር ምሁራን የዳሠሧቸውን ሐሳቦች አነሣለሁ፡፡

### 2.1. የገዳም ምንነት

የገዳምን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ጸሐፍት የተለያዩ ፍቺዎችን ሰጥተው እናገኛለን፤ ከእነዚህም መካከል በዚህ ጥናት የተወሰኑትን እናያለን፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሉ (1948፣302) "ገዳም በቁሙ ምኔት፣ ደብር፣ የመነኮሳት ሰፈር፣ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፣ በደለኛ ሸሽቶ የሚጠጋበት፣ ደውሎ የሚማጠንበት ደብር፣ ምጽላይ፣ ዱር፣ ጫካ፣ ወማ፣ በረሀ፣ በዳ፣ ከሀገር ከመንደር የራቀ የአራዊት ክፍል…" በማለት ገልጸውታል፡፡

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣503) ገዳም ማለት መነኮሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖት ሥርዓት እና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ አንድ ሰው ገዳም ገባ ሲባል ዓለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር መቀመጥ ጀመረ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ"(1997፣22) ገዳም የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

> *የላመ የጣመ ሳይቀመስ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብስ፣ ጤዛ ለብሶ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምፀ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሦ፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቆ፣ ከሥጋዊ ክብርና ተድላ ደስታ ተጠብቆ፣ ከዕለታዊ ኑሮው ሁሉ ከሰው ሽክምነት ተላቆ፣ እራሱን በእራሱ እየረዳ ዘወትር በጾምና በጸሎት፣ በገድልና ትሩፋት ተጠምዶ የሚኖር የእግዚአብሔር ሰው ማለት ነው፡፡*

በገዳም ሕይወት የእኔ የግሌ የሚሉት ንብረት የለም። ሁሉ በማኅበር፣ በአንድነት፣ በጸሎት፣ በሥራ እየተጉ ፍጹም የዓለምን ኀላፊነት ተረድተው፣ የማታልፍ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳለች በመገንዘብ ዘወትር በቀኖና ተወስነው የሚኖሩበት ነው። ይህም ሕይወት የቅዱሳን መኖሪያና ጸጋ እግዚአብሔር የማይለይበት ሲሆን በአንጻሩም ከሁሉ የከበደ የአጋንንት ጾር የሚበዛበት ቦታ ነው። ገዳምና ገዳማዊ ሕይወት አስፈላጊ በመሆኑ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አርአያ ሆኖን በገዳመ ቆሮንቶስ በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ተቀመጠ (ማቴ 4÷1-11) ፤ፈታኝ ዲያብሎስንም ድል አደረገው። ገዳማዊ ሕይወትን የመሠረተልን አምላካችን- አርአያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በአጠቃላይ ገዳማዊ ማለት "ስለ እኔ ብሎ ቤቶችን ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ አባቶችን፣ እናቶችን፣ እርሻን የተወ ሁሉ መቶ ዕጥፍ ይቀበላል፤ የዘላለም ሕይወትም ያገኛል" (ማቴ 19፡29) የሚለውን አምላካዊ ቃል ተከትለው ሀብት-ንብረትን፣ ወዳጅ ዘመድን ትተው፣ ከዓለማዊ ሕይወት ተገልለው የሚኖሩ መነኮሳትን ያመለክታል። ይህንን ሁሉ ትተው በመመንኮስ እንደ አብነት የሚጠቀሠው በዘመነ ብሉይ እና በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሦ የምናገኘው የሔኖክ ታሪክ ነው (ያረጋል፣ 1993፡185)።

ከጥቅሦቹ የምንረዳው ምንኩስና ራሳቸውን ለፈጣሪ ለማስገዛት እና ለማቅረብ፣ ዓለማዊውን ሕይወት ንቀው ሀብት-ንብረታቸውን ትተው፣ አሉን ከሚሏቸው ሁሉ ተለይተው፣ አምላካቸውን ለማገልገል በበርሀ ጎጆ ቀልሰው፣ አራዊትን ሳይፈሩ፣ ለሚመገቡት፣ሳይጨነቁ የሚኖሩት ሕይወት መሆኑን ነው።

## 2.2. የገዳም ሕይወት ጅማሮ በኢትዮጵያ

የገዳማዊ ሕይወት በመጀመሪያ ሰሜናዊ ክፍል በትግራይ ዋና ከተማ በነበረችው በአክሡም አካባቢ የተወሰነ ነበር። የመጀመሪያው የገዳማውያን ማኅበረሰብ በ5ኛው ምእት ዓመት ዘግየት ብሎ ከኢያሪኮ ባሕር አካባቢ (ምናልባትም ከሶሪያና ከግብጽ በመጡ ዘጠኝ መነኮሳት እንደተመሠረተ ይነገራል) (ያረጋል 1993፣185) ተጀምሯል። ከዚሁ የተቀደሰ መንፈሳዊ ሕይወታቸው የተነሣ ተስዐቱ ቅዱሳን ተብለዋል። በነዚሁ ቅዱሳን ከተመሠረቱት ገዳማት በጣም ታዋቂ የሆነው ደብረ ዳሞ የተቋቋመው ከተስዐቱ ቅዱሳን መካከል ስማቸው ጎልቶ በሚታወቀው ቀድሞ ዘ-ሚካኤል ኋላ አቡነ አረጋዊ በሚባሉት ቅዱስ አባት ነው (ሉሌ 1997፣30)።በዚያው ዘመን "ጻድቃን" በመባል የሚታወቅ ሌላው የመነኮሳት ማኅበር በሰነአፌ

ደቡብ /በአሁኑ ጊዜ ደቡብ ምሥራቅ ኤርትራ/ በመጠራ፣ በባረክናሃ፣ በደቡባዊ ጎንደርም ወንጌልን ይሰብኩ ነበር (ያረጋል፣ 1993፣185፤ ሉሌ፣ 1997፣30)።

የተወሰኑ ገዳማት በሁለቱ ነገሥታት በአብርሀና አጽብሐ /4ኛው ምእት ዓመት/ እንደተመሠረቱ ይገልጻል። ከዚያ ዘግየት ብሎ በገዳማት ምሥረታ የታወቁ ሌሎች ነገሥታት መኖራቸው ይነገራል (ያረጋል፣1993፣189)።

በከፍተኛ ደረጃ የታወቁት አበው እስከተነሡበት እስከ 13ኛው ምእት ዓመት ድረስ ስለ ገዳማዊ ሕይወት የሚያስረዱ ሰነዶች ብዙ አልነበሩም።የደብረ ዳሞው የአቡነ ዮሐኒ መንፈሳዊ ልጅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1287 ነው ያረፉት። የመነኮሱት እስከ ዛሬም የገዳማዊነት ማእከል በሆነው በደብረ ዳሞ ነው። አቡነ ኢየሱስ ሞአ በ1248 ወደ ቤተ ዐምሐራ፣ ማለትም የእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ወደሚገኝበት ወደ ሐይቅ ተጉዘው የደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስን ገዳም መንፈሳዊ ት/ቤት አቋቋሙ። ገዳሙ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ (13ኛው ምእት ዓመት) ጋራ የቀረበ ግንኙነት ነበረው። የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀመዝሙርና በጣና ሐይቅ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መሥራች እንደ ነበሩት እንደ አቡነ ኂሩተ አምላክ ያሉት ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ከገዳሙ የተገኙ ወይም በገዳሙ መንፈሳዊ ሕይወት እየተሳቡ ከሌላ ቦታ የመጡ ናቸው (ዳኛቸው ካሳሁን፣1999፣133፣ ሉሌ፣1958፣60-61፣ አሳምነው፣2000፣56)

በጣና ሐይቅ ደሴቶች ዙሪያ የገዳማዊ ሕይወት ምሥረታ የተጀመረው ቢያንስ በ14ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ በዐፄ ዐምድ ጽዮን ዘመን ነው። በጣም ታዋቂ ከሆኑት የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ተክለሃይማኖት ናቸው። (ዳኛቸው ካሳሁን 1999፣ ተክለሃይማኖት ወደ ምዕራቡ የሀገሪቱ ክፍል በመሄድ በ13ኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ በሸዋ ውስጥ የደብረ ዐስቦን (ኋላ በ1445 ደብረ ሊባኖስ የተባለውን) ገዳም አደራጅተው አቋቁመዋል። ብዙ ገዳማትን በመመሥረት እጅግ ታዋቂና ተደማጭነት የነበራቸው ሌላው መነኩሴ በትግራይ ገረ አልታ ውስጥ የነበሩት የታላቁ መናኝ የአቡነ ዳንኤል የእኅት ልጅ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ /1273-1352/ ናቸው (ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም፣1999፣133-134)።

ከዚህ በኋላ በገዳማዊ ሕይወት የሐረግ አወራረድ ሁለት ታላላቅ ሐዋርያዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት በዋንኛነት ወደሸዋ እና ከዚያም ራቅ ወዳለ ደቡብ እንደዚሁም በምዕራብና በሰሜን ሲሰማሩ፣ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ደቀ መዛሙርት ደግሞ በዋንኛነት ወደ ሰሜን /ወደ ትግራይና ኤርትራ/ እንደዚሁም ወደ ምዕራቡ ክፍል ተጉዘዋል፡፡ከአቡነ ተክለሃይማኖት ታዋቂ ደቀ መዛሙርት መካከል የደብረ ዐስቦውሦስተኛው ጸባቴ/ አስተዳዳሪ/ አቡነ ፊሊጶስ፣ የደብረ ብሥራቱ አቡነ ዜና ማርቆስ/ በሰሜን ሸዋ ሞረት/ እና አቡነ አኖሬዎስ ይገኙበታል (ያረጋል፣ 1993፣188-189፤መልአከ ሰላም፣1999፣173)፡፡

በ16ኛው ምእት ዓመት ደግሞ በጣም ታዋቂ የነበሩት የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪዎች አቡነ ንባቆምና አቡነ ዮሐንስ ናቸው፡፡ የሐይቅ እስጢፋኖስን ገዳምም ስናነሣ በሐይቅ የሚገኙትን የቅዱስ ጊዮርጊስና የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያንን የመሰረቱት አቡነ ሰላማ ዘ አዜብ ሁለተኛ እና አፄ ድልናኦድ ይጠቀሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ የነበረውን ቤተክርስቲያን ወደ ገዳምነት እንዲቀየር ያደረጉት በ13ኛ ክፍለ ዘመን የመጡት አቡነ እየሱስ ሞኦ ናቸው፡፡ (ዳንኤል 1999፡9-11) በዚህችም ገዳም በርካታ ቅዱሳን መንፈሳዊ ትምህርት ተምረዋል፡፡ ከተማሩት ቅዱሳን መካከል ተክለ ሃይማኖት፣ አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ ኂሩተ አምላክ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ አቡነ ገብረ ናዝራዊ፣ አቡነ ሕዝቅያስ፣ አቡነ እስጢፋኖስ ይጠቀሣሉ (ሥርግው 1977፡112-13)፡፡

የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አስተዳዳሪ የማዕረግ ስም “ዐቃቤ ሰዓት” ይሰኛል፡፡ ይህ ስም ተገቢነቱን እንደያዘ እስከ 16ኛው ምእት ዓመት ቆይቷል፡፡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ እንደ ኢትዮጵያ ትውፊት ከጻድቁ ከተክለ ሃይማኖት ዕረፍት በኋላ ወይም ከ16ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ “ዕጨጌ” ይባላሉ (ዳኛቸው ከሳሁን፣1999፣173-174)፡፡

በራሳቸው ተነሣሽነት በገዳማት ምሥረታ የታወቁ ሴቶች መነኮሳይያትም አሉ፡፡ ለምሳሌ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ /15ኛው ምእት ዓመት/፣ ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ፣ ቅድስት ቆራጣ ወለተ ጴጥሮስ /17ኛው ምእት ዓመት/ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 2.3. የገዳም ሕይወት የአኗኗር ሥርዓት (ደንብ)

በገድለ ቅዱሳንና በሌሎችም ምንጮች እንደተመዘገበው ማንኛውም ሰው የግል ፍላጎትና ውሳኔ ካለው ገዳም መግባት ይችላል፡፡ አንዳንድ በገጠር የሚኖሩ ወጣት ወንዶችና ሴቶች

በወጣትነት እድሜያቸው ገዳም ይገባሉ። በኢትጵያ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት የሚታወቀው ወደ ገዳም የሚገቡ ወይም በቤታቸው በምንኩስና ሥርዓት ጸንተው ለመኖር ቃል ኪዳን የሚፈጽሙ በዕድሜ የሸመገሉ ወንዶችና ሴቶች፣በአመዛኙ ባሎች የሞቱባቸው ሴቶች፣ሚስቶች የሞቱባቸው ወንዶች ናቸው። ወደ ሥርዓቱ ሲገቡ ጸጉራቸውን ተላጭተው፣ቢጫ ቆብ ደፍተው በምናኔ ሕይወት ይወሰናሉ።

በኢትዮጵያ ነገሥታትና አንዳንድ ባለርስቶች ገዳማውያን አበው በጸሎቶቻቸው እንዲያስቧቸውና በረከት ለማግኘት መሬት፣ የተለያየ ሀብት፣ ንብረት፣ የሃይማኖት መገልገያ ንዋያተ ቅዱሳትን ይለግሱ ነበር። ክርስቲያኖች ሁሉ እንደ ኑሮ ደረጃቸው የሚቻላቸውን በመስጠት ያገለግሉ እንደ ነበር ዳኛቸው ካሳሁን 1997፣174 በተለመደው መሠረት የሴቶች ገዳማት የሚቋቋሙት ከወንዶች ገዳማት ብዙ በራቀ ቦታ ላይ አይደለም። በመሆኑም ወንዶችና ሴቶች በአንድ ቤተ ክርስቲያን በአንድነት መንፈሳዊ አገልግሎት ይሳተፋሉ።

ገዳማዊ ሕይወት እያንዳንዱ እንደየችሎታውና ዝንባሌው በተለያየ ተግባርና አገልግሎት ውጤት የተገኘውን በማኅበር በመሳተፍ የሚኖሩበት ነው። ይህም የ"አንድነት" ወይም እያንዳንዱ በ "ቁሪት" ለየግል የተገኘውን በመመገብና በመሥራት የሚኖሩበት ይሁን እንጂ በጸሎትና መንፈሳዊ አገልግሎት ግን በአንድነት የሚካፈሉበት ሁለት ዐይነት የአኗኗር ሥርዓት አለው። እነዚህ ሁለት ገጽ ያላቸው የአኗኗር ሥርዓቶች በተመሳሳይ ገዳም ጎን ለጎን የሚኖሩበት አጋጣሚም ይኖራል (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣1997፣23)። ለአንድነት ኑሮ ምሳሌ ከሚጠቀሡ ገዳማትመካከል አንዱ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲሆን በተወሰነ ቦታ ተቀራርበው በስፋት በተሠሩ ጎጆዎች የሚኖሩበት የቁሪት ገዳም ምሳሌ የሚሆነው ደግሞ ዋልድባ ገዳም ነው።

በገዳማት አስተዳደር ኀላፊነት የሚሰጣቸው የተወሰኑ ሰዎች ይኖራሉ። የአንድ ገዳም አስተዳዳሪ፤ አበምኔት ወይም የአኀዛ መምህር ይባላል። አስተዳዳሪ ማለት ነው። የገዳሙን የዕለት ተዕለት ዝርዝር ተግባር ኀላፊነት የሚከታተለው "መጋቢ" ይባላል። በሥርዓቱ አስተዳደር ኀላፊነት ሰዎች የሚመደቡት በገዳሙ ማኅበር ምርጫ ነው። እንደ ደብረ ሊባኖስና ዝቋላ በመሳሰሉ ታላላቅ ገዳማት አስተዳዳሪው (አበምኔቱ)በማኅበር ይመረጣል፤ ሹመቱ በፓትርያርክ ይጸድቃል፣ በየሀገረ ስብከቱ የምርጫውን ውጤት ሊቀ ጳጳሱ ያጸድቃሉ። አብዛኛውን ጊዜ እንደ ዕጩዎቹ ልዩ ሁኔታ፣ በተለይ ለአረጋውያን ወይም እንደ ገዳሙ

መንፈሳዊ የቅደም ተከተል ሥርዓት ሊለዋወጥ የሚችል የሦስት ዓመታት የ "አመክሮ" ጊዜ አለ (ያሬጋል 1993፣193)።

በገዳማውያን የአለባበስ ልማድ ወይባ ሰማያዊ፣ ነጭ፣ ቀይ፣ ሐምራዊ፣ ቡናማ እና የመሳሰሉት ቀለማት ያሏቸው ልብሶች ይዘወተራሉ። እነዚህ ቀለማት ብዙውን ጊዜ ከመናንያን (ባሕታውያን) ጋራ የተያያዙ ናቸው። የቀለሞቹም ዓይነት እንደየ ምንኩስና ማዕረጋቸው ይለያያል።

የሚለበሰው ረጅም እጀ ሰፊ ቀሚስ ከቆዳ ቀበቶ (ቅናት) በመባል ከሚታወቅ ዝናር መታጠቂያ ጋራ ነው። መነኮሳት መካከሉ ድፍን የሆነ ዙሪያ ክብ ቆብ ያደርጋሉ። የምንኩስናን ሥርዓት ያስፈጸመ (ያመነኮሰ) አባት "የቆብ አባት ይባላል። ይህ አባት በወንዶችና ሴቶች የምንኩስና ሥርዓት አፈጻጸም (አመሠራረት) ላይ የሚጠበቅበት ልዩ መንፈሳዊ ተልእኮ አለው። እንዲሁም "አስኬማ" በሚል ስም የሚታወቅና ለየት ያለ ደረጃ ያለው ገዳማዊ የኑሮ ትውፊት አለ። ይህ ዐይነቱ ሥርዓተ ምንኩስና በጣም ለተወሰኑ ሰዎች የሚፈጸምና ከተወሰኑ ገዳማት ትውፊታዊ ውርስ ጋራ የተያያዘ ነው(ዳኛቸው ካሰሁን 1999፣175)።

አብዛኛውን ገዳማት ከከተሞችና መንደሮች በራቀ ቦታ ስለሚኖሩ በቀላሉ የሚደረስባቸው አይደሉም። የገዳማት ሕንጻዎች እንደ ሕዝቡ የገጠር ነዋሪ ቤቶች ሁሉ በድንጋይ ግንብ ወይም በጭድና ገለባ ተቦክቶና ተረግጦ በሚመረግ ጭቃ የሚሠሩ ቤቶች ናቸው። ኑሮ በገዳማት ውስጥ ሁልጊዜ መጠነኛ ነው። በአንዳንድ ገዳማት እንዲያውም ለቁመተ ሥጋ የሚያስፈልግ ምግብ እንኳን ለማግኘት ችግር አለ (ዳኛቸው ካሳሁን፣ 1999፡175)።

ለጠቅላላው መነኮሳትና መነኮሳይያት ምግብ በአንድ ማብሰያ ቤት ሊዘጋጅ ይችላል። ከሰኞ እስከ ዐርብ በማናቸውም ቀናት ከሰባት ወይም ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ይመገባሉ። በጣም መናንያን ካሉበት ገዳም በዐቢይ ጾም በጀንበር ጥልቀት አካባቢ ከሚቀርበው ምሳ በፊት ባለው ጊዜ ምንም ዐይነት ምሳ አይበላም። ወንዶችና ሴቶች መነኮሳትና መነኮሳይያት ከቅዳሴ በኋላ ጠዋት እህልና ውሀ የሚቀምሱበት ጊዜ ቢኖር ቀዳሚት፣ እሑድና ከትንሣኤ በኋላ ባሉ ኀምሳ ቀናት ውስጥ ብቻ ነው(ሰሎሞን ቶልቻ ፣1991፣106)።

የገዳማውያን የምግብ ዐይነት ከቦታ ቦታ ይለያያል፤ ግን በሁሉም ዘንድ ተራ ነው። በጣም የተለመደው የአብዛኞቹ ገዳማት ምግብ ከተለያዩ የእህል ጥራጥሬዎች ተቀላቅሎ የሚቀቀል ንፍሮ፣ ዳቦ፣ዳቤ እና በተራ ወጥ የሚበላ እንጀራ ነው።በአጽዋማት ጊዜያት በአብዛኞቹ

ገዳማት ዳቦና እንጀራ አይበላም፤ የሚበላው የቅይጥ እህል ንፍሮ ነው። በገጠሩ አካባቢ በገዳማት ነዋሪ የሆኑ አንዳንድ ባሕታውያን በአካባቢያቸው የሚገኙትን የተፈጥሮ ዕፀዋት ይመገባሉ። ሥራሥር፣ ቅጠላ ቅጠል፣ (ለምሳሌ፦ ቋርፍ) በገዳም ለምግብነት ያገለግላሉ (ሰለሞን ቶልቻ፣1991፣106)።

ከገዳማት በአብዛኞቹ የዕለት ተዕለት ተግባር የጊዜ ሰሌዳ ይብዛም ይነስ ተመሳሳይ ነው ከንጋቱ ዐሥር ሰዓት እስከ ጠዋት አንድ ሰዓት ድረስ የነግህ ጸሎት፣ የጠዋት ቅዳሴ ይከናወናል።ከቅዳሴ መልስ በየመስኩ የመማር-ማስተማርና የተግባረ እድ መርሐ ግብር ይካሄዳል። በ6 ሰዓት የቀትር ጸሎት በቤተ ክርስቲያን ይደረጋል፤ ከ7-11 ያለው ጊዜ እንደየ ቦታው የምሳ ሰዓት ነው። ከ11-12 የምሽት ጸሎት በቤተክርስቲያን በማኅበር ይጸለያል። ከዚያ በኋላ በሚኖረው ነጻ የምሽት ጊዜ ገዳማውያን በየግል በአታቸው የግል ጸሎትና ስግደታቸውን ይቀጥላሉ። በገዳማውያን ሕይወት ላይ ያለ ሥራ የሚባክን ለዕረፍት የሚቀረስ ጊዜ የለም። የግል ጸሎት አብዛኛውን ጊዜ የሚደረሰው ከመቁጠሪያጋራ ነው። የግል ጸሎት “መቁጠሪያ” ከመጠቀም ጋራ በቀን ሰባት ጊዜ ይደረጋል። የሰባቱ ጊዜያት ጸሎት በቤዛንታውያን ትውፊት ከሚወሣው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎት በከፊል የሚገኘውን ያካትታል። ይኸውም በመጀመሪያ “እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ”ሀ) 41 ጊዜ፣ ለ)“ኪርያላይሶን” 41 ጊዜ፣ ሐ)“ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ” 41 ጊዜ፣ መ)“በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አባሳነ” 41 ጊዜ ይደርሳል። ከዚያ በኋላ ሠ)“አቡነ ዘበሰማያት” እና ረ) “በሰላመ ገብርኤል” 12 ጊዜ ይደገማል። “እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ” እና ሰ)“በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ” በመቁጠሪያ ብቻ ሳይሆን በአራት ጣቶች አዕጹቅ ልክ ይቆጠራል፤ ይህም ኑዛዜ ይባላል። የጸሎትን ሥርዓት ጠንቅቀው የሚያውቁ ምእመናን ሁሉ በግል ጸሎታቸው ጊዜ ሁሉ ያደርሱታል። “የምናኔ ኑሮ በቁርጥ ውሳኔ ሕይወትን በእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ ማዋልን፣ እርቆ አሳቢነትን፣ የእምነትንና የእውነተኛነትን ስሜት ይጠይቃል።

ዕንቅልፍና ዕረፍት በሌለው ትጋት፣ ከሚደረግ የረጅም ጊዜ ጸሎትና ጾም በኋላ መነኩሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ ይሰጣቸዋል። ከዚያ በኋላ ሰዎች በጎምክር ለማግኘትና ቡራኬ ለመቀበል ወደነሱ ይመጣሉ” ማለት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ የገለጹትን በመጽሐፉ እናገኛለን (ዳኛቸው ካሳሁን፣1999:174-179)።

## 2.2. የተረክ ንድፈ ሐሳብ

ተረክ (Narrative) ይህ ቃል በኢትዮጵያ የመስኩ አጥኚ ከሆኑት መካከል ፈቃደ (1991፡52)፣ ተረት በሚል ሲተረጉሙት ዮናስ (1992፡84) ተረክ ብለውታል፣ ሰሎሞን (2007፡28) ደግሞ ቃለ ተረክ ሲለው ይስተዋላል፡፡ "ዐሥረኛንኩዋ? ሐዲስ አለማየሁ እና የማኅበራዊ ሒስ ሥልታቸው" በሚለው መጣጥፍ ውስጥ Narative የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ተረክ በሚል የተረገሙትን ትርጉም ይዤ እቀጥላለሁ፤ ከዚህም በመቀጠል የተለያዩ ምሁራን ስለ ተረክ የሰጧቸው ብያኔዎች በዝርዝር ዐያለሁ፡፡

ፈቃደ (1991፣53) ሰዎች ተረትን እንዴት ይገለገሉባቸው እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም በጥንት ዘመን ሰዎች ተረት በመተረት ጊዜ ያሳልፉ፣ ይዝናኑ፣ ይደሰቱ፣ ይማሩ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በተመስጦ ያነቧቸዋል፤ ያዳምጧቸዋል፤ ስለ አማልክትም፤ ስለ ቅዱሳንም፤ ስለ ነቢያትም… ወዘተ እንዲሁ በተመስጦ ያነባሉ፤ ያዳምጣሉ፡፡ ከእነዚህ ክንዋኔዎች ደስታን፣ ትምህርትን፣ ምግባርን ወዘተ ይቀስማሉ፡፡

እንደየሁኔታውም፤ የሕይወትን ምስጢራዊነት፣ የደፋር ገጸ ባሕርያትን፣ ጀግንነትን፣ የፈሪዎችን ቡርቅነት፣ የሰላውዴዎችን ከንቱነት፣ የቅኖችን የዋህነት፣ የአታላዮችን መሠርይነት ወዘተ ይመለከታሉ፡፡ ከእነዚህ ተረቶች የሚገኘውን ዕውቀት ሁሉም በየዘርፉ ይገለገልበታል፡፡

በተመሳሳይ መልክ Deign (1972:54): Oral narratives በማንኛውም ማኅበረሰብ እንደሚቀርቡ ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማኅበራዊ ሁኔታ (Social condition or climate) ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡

በሌላም በኩል የአንድን ማኅበረሰብ ተረክ ለማጥናት ሲፈለግ ትኩረት መደረግ ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ deign (1972፣54) ይገልጻሉ፡፡ እነርሱም በተረኮቹ አማካይነት የሚተላለፉት መልእክቶች ምንድን ናቸው? ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆኑት ምን እንደሆኑና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ተረድተው መልስ መስጠት እንደሚገባ ነው የገለጹት፡፡

ከእነዚህ ሐሳቦች በመነሣት ተረክ የአንድ ማኅበረሰብ መገለጫ የሆነ፣ በዝርው የሚቀርብ፣ የድርጊት ተሳታፊዎች ገጸ ባሕርያት ያሉት፣ ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመላክት፣ ረጅም ዘመን ያለው፣ ለሰው ስሜት ቅርብ የሆነ፣ ከነባራዊ ዓለም ጋራ

በሚስማማ መልኩ የሚቀርብ የሥነ-ቃል አካል ነው ማለት ያስችላል፡፡ Oring በበኩላቸው ተረኮች በድርጊቶችና በሁነቶች የተዋቀሩ የአንድ ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ልማድ ለማስተላላፍ የሚጠቅሙ መሣሪያዎች ናቸው በማለት ይገልጻሉ ይህም ተረት የአንድን ማኅበረሰብ ተከታታይ ድርጊት ቃላዊነቱ እንዳለ ሆኖ በተለያየ ቅርጽ የሚቀርብበት ነው ማለት ያስችላል፡፡

**የተረክ ዐይነቶች፡-** በተረክ ዐይነት ዙሪያ በርከት ያሉ ምሁራን የራሳቸውን ብያኔ ሲያስቀምጡ ይስተዋላል፡፡ ከነዚህም መካከል William Bascom ባስኮም እና ኦክፔውሁ ይጠቀሣሉ፡፡ ፈቃደ Okpewhu በመጥቀሥ የተረት ዐይነቶችን ሌጀንድ፣ ገላጭ ተረቶች እና ፋቡልስ በማለት እንደሚከፈሉ ያስረዳሉ፡፡ እንደ Bascom (1965፣4)፡፡ ገለጻ የተረክ ዐይነቶች ተብለው የሚታወቁት ሚት፣ አፈ ታሪክ እና ተረት ናቸው፡፡Bascom ለተረቶች ምደባ መሠረት ያደረጋቸውን ነገሮች ሲገልጹ አካባቢያዊ እንድምታ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በቀጣይም እነዚህን ሦስት ነጥቦች ከተለያየ ምልከታ አንጻር እንቃኛለን፡፡

2.2.1.1. **ሚት፡**. "የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህልዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት ፣እየተመሰቃቀለ በሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርአት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ ሚት የማህበረሰቡን የዕሴት ሥርአትም ነው"ቲዎድሮስ ፣XII፡፡ Finnagane (1992፣138) ሚት በማህበረሰቡ ዘንድ ከረጅም ዓመታት በፊት የተከሰቱና እውነት ናችው ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶች የሚነገሩበት የቃል ትረካ ዐይነት እንደሆነ ትገልጻለች:: :ችትገል ዐይነት እንድር :ችትገል ዐን :ችትገል ዐሳ:ችትገል ዐይነት እንድርጊቶጊዜችትገል ዐይነት እንድርበማህበረሰቡዐይነት እንድርጊቶች የሚነገሩ ቅዱስበረሰቡዐይነት እንድርጊገልጻሉ፡፡እንደ bascom (1965፣1) 965mቡዐይነት እንድርጊኮች965mቡዐይነት እንድርጊዙ ች965mቡዐሙሉ965mቡዐይነት እንድርጊቶች ጽማሉ65mቡዐ ማንዲፈጽሙዲፈጽ5mቡዐይነት እንድርጊቶችእንዲኖሩmቡዐይነሉ፡፡ዲኖሩmቡዐይነት እንድርጊቶች የሚነገሩበት የ ነገሮች ሲገልጹ አካባቢያዊ እንድምታ ላይ የተመሳሳ ሳዲኖሩ

ሚት ማኅበረሰቡ በአካባቢው የሚያስተውላቸው ተፈጥሯዊ ሁነቶች ያላቸውን ባሕርይ፣ አፈጣጠራዊ ሂደት፣ ከየት-መጣነት መልስ ለማግኘት የሚጥርበት ነው፤ የአካባቢውን የባህል ዕሴት መሠረት በማድረግ ለራሱ የአስተሳሰብ አድማስ ለዓለም ያለውን ግንዛቤ የሚገልጽበት የተረት ዐይነት ነው፡፡

ስለ ሚት ምንነት ከማጠቃለሌ በፊት የሚት ዐይነቶች ተብለው በተለያዩ ምሁራን ተመድበው ከምናገኛቸው መካከል ጥቂቱን ልጠቁም፡፡

ሐተታ ተፈጥሯዊ ሚት (creation myth)፣መንፈሳዊ ሚት (Deity myth)፣የባህል ታጋይ ሚት (myth of culture heroes and esoteriological)፣ ጊዜያዊና የዘላለማዊ ሚት (Myth of time and eternity)፣የዘመናዊ ማኅበረሰብ ሚት (Myth of modern society), ጂኦሚቲዮሎጂ geomethology  ወዘተ ይጠቀሣሉ፡ሰለሞን (2007፣101)፡፡

2.2.1.2. **አፈ-ታሪክ፡-** አፈ ታሪክ ባለፈ ታሪክ ተመሥርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታ በመውሰድ ሥነ-ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ እንደ ዘሪሁን አገላለጽ የአፈ ታሪክ ዐላማ አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ በታሪክ የተፈጸመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ለምን ተፈጸመ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሡ በአፈ ታሪክ መልስ ይሰጣል (2004፣31-32)፡፡

አፈታሪክ በማኅበረሰብ ውስጥ የተከሠተ እውነተኛ ታሪክ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ተስተላልፎ በአንድ ትውልድ ያልተገታ ነው፡፡ አፈ ታሪክ ቃላዊበሆነው  ተስተላልፎው አድማጩን በማስተማር፣ በማንቃት፣ወይም ለአድማጩመረጃ በመስጠት፣ ታሪክ በማሳወቅ ወዘተ… ረገድ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

እንደ Bascom (1965፣6) ገለጻ አፈ ታሪክበእውነት ላይ የሚመሠረት፣ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚመረመሩበት፣ ገጸ ባሕርያቱ ሰዎች የሆኑ፣ በእራሳቸው የሚቆሙ ሳይሆኑ እራሳቸውን አሳልፈው ሰዎችን ነጻ የማውጣት ባሕርይን የተላበሱ፣ ገጸባሕርያቱ የሚተውኑበትን መንፈሳዊ፣ሥጋዊ ጉዳይም የሚያነሣ፣ በዚህኛው ዓለም የተፈጸመ የቅርብ ኀላፊ ጊዜ ያለው፣ መቼቱ አንዳንዴ የሚታወቅ፣ እውነትነት ያለው፣ ስለ ሰዎች፣ ስለ ቦታዎች ስለ ታሪኮች እና የተለያዩ ክሥተቶች የሚተርክ ማለት ነው፡፡

2.2.1.3. **ተረት፡-** ተረቶች በሳይንሳዊ መንገድ ሊረጋገጡ የማይችሉና በሰዎች አእምሮ ውስጥ ተአማኒነት የሌላቸው ፈጠራዊ ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ፍሰታቸውን ጠብቀው የሚቀርቡበት የታሪክ ዐይነት ነው፡፡ ተረት በሴራ ያልተወሳሰቡ ልማድና ቀጥተኛ የሆኑ ታሪኮችን፣ ዓለም ዓቀፋዊ ባሕርይ ያላቸውን ታሪኮች የሚገልጽና በውስጡም የሚገኙትን ገጸ ባሕርያት፣ አጋጣሚዎች፣ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችና የድርጊቱ ገጽታዎች እንደ ዋና መሠረታዊ ጭብጥ የሚወስድ ነው፡፡

ከዚሁ ጋራ በተያያዘ Bascom (1965፣6) ተረቶች ብዙውን ጊዜ የራሳቸው የአቀራረብ ሥርዓቶች እንዳሏቸውና በሚተገበሩበት ጊዜም በተረቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መመሪያዎችን በማምጣት አድማጩም ተረቶቹ ተጀምረው እስኪጨረሱ ድረስ ሥርዓት ባለው መልኩ እንደሚከታተል ያስረዳሉ እንደ ባስኮም አገላለጽ የተረቶች በአንድ መደብ መመደብ ይዘትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

በተረቶች ላይ አጀማመርና አጨራረስ መኖር ካነሣን ፈቃደ (1999፣63) የተረቶች ዋና ዋና ውጫዊ ቅርጾች ብሎ ያነሣቸውን ነጥቦች ጠቁሜ ልለፍ፡፡

የተረት መግቢያ፣ የተረት አጀማመር፣ የተረት አጨራረስ፣ የተረት መዝጊያ እና የተረት ክዋኔ (ትረታ) ይጠቀሣሉ፡፡ ዐይነቶቹን በዝርዝር ማየቱ ከእኔ ጥናት ጋራ የሚያቆራኘው ነገር ስለሌለ ዐልፈዋለሁ፡፡ ተረቶች በሚተረቱበት ወቅት ታሪክ ውስጥ የሚቀርቡ ድርጊቶች የተከሠቱበትን ጊዜና ቦታ በግልጽ የማያሳዩ በሞራል የምንፈጥራቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ተረቶች እንደ እውነተኛ ታሪክ ከመውሰድ ይልቅ በሚፈጥሩት ደስታ የምንዝናናባቸው ናቸው በማለት Marvate (973፡95) እና Benemos፣ (1992፡102) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የዘረዘርናቸውን ሦስት ነጥቦች ስንመለከት ተረቶች ተቀራራቢ ባሕርይ እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡ ይህም የሆነበትን ምክንያት Finnegan (1970፣363) ስትገልጽ በአንድ ማኅበረሰብ አፈ ታሪክ ወይም ተረት ናቸው ተብለው የሚነገሩት በሌላ ማኅበረሰብ ሚት ወይም ተረት ተብለው መነገራቸው ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ ዮሴፍ ቦኪ የተባለ አጥኚ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ከፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥናቱን ባደረገበት ጊዜ በጥናቱ ወቅት ካጋጠሙት ችግሮች መካከል የጠቀሠውን ላንሣ፡፡ አጥኚው በሄደበት ማኅበረሰብ ተረክን በተረክነቱ ከመግለጽ ይልቅ እንደ ተረት የመተረት እና ተረክ የሚለውን ቃልም ከነጭራሹኑ ያለመረዳት ነገር እንደ ነበር ይገልጻል፡፡

## 2.2. የኦክፔውሁ የተረክ አከፋፈል

**2.2.1. አፈ-ታሪክ፦** ይህንን ቃል፣ ታዋቂ ግለሰቦችን እና ታዋቂ ድርጊቶችን፣ ሁኔታዎችን በማመልከት ተደጋግመው ለሚተረኩ ተረቶች ብቻ መጠሪያ Okpewhu መርጠውታል Okpewhu ሌጀንዶችን በሁለት ይከፍሏቸዋል ታሪካዊ አፈ ታሪክ እና ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ ታሪክ በማለት ይከፍሏቸዋል ታሪካዊ አፈ ታሪክ እና ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ ታሪክ በማለት Okpewhu ውስጠ ፈቃደ፣ (1991፣56)፡፡

- ታሪካዊ አፈ ታሪክ በዚህ ክፍል ውስጥ ማኅበረሰቡ በቀላሉ ሊያስታውሳቸው የሚችላቸውን ድርጊቶችና ግለሰቦችን አስመልክቶ የሚተርታቸውን ይመድባል፡፡ ትኩረቱ ሕይወት ቀመስ ዝርዝሮችን እውነታዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው፡፡ ጊዜው፣ ተራቹና አድማጮች የሚኖሩበት የአሁን ጊዜ ወይም በቅርብ ያለፈ ጊዜ ስለሆነ፤ አድማጮችም ሊተቹት ስለሚችሉ፤ ተራቹ የምናቡን ልጓም እንዳሻው ሊለቅ አይችልም፡፡
- ሮማንቲክ ወይም ሚቲካል አፈ ታሪክ ይኼኛው ለተራቹ ምናብ ሰፊ ነጻነት ይሰጣል፡፡ ድርጊቶቹም ሆኑ ግለሰቦቹ የጥንት የሚባሉ ስለሆኑ ተራቹን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ የሚደቅንበትም ሰው ብዙ ጊዜ አይገኝም፤ ቢገኝም ተራቹ የማምለጫ ቃላትን በመጠቀም ያመልጣል፡፡ ሌላው የዚህ የተረት ዐይነት ተራቹ ተረቱን ለእራሱ እንዲስማማ አድርጎ የሚተርትባቸውን አጋጣሚዎች የሰፉ ናቸው (Okpewhu ውስጠ ፈቃደ 1991፣57)፡፡

ከእነዚህ ሁለት ሐሳቦች የምንረዳው ምንም እንኳን የአፈታሪክ ተናጋሪዎች የሚናገሩባቸው መንገዶች ቢለያዩም መነሻቸው ግን እውነታን የያዘ ታሪክ መሆኑን ነው፡፡

**2.2.2. ገላጭ ተረቶች፦**Okpewhu በዚህ ክፍል የመደቧቸውን ተረቶች ሌሎች ምሁራን Origin story, Natursage, Pourquoistory, etiological tales በመሳሰሉ መጠሪያዎች ሲጠሯቸው ይገኛሉ፡፡ ገላጭ ተረቶች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚታዩትን ተፈጥሯዊ እና ሕይወታዊ ክሥተቶችና ሐሳቦች ከየት-መጣነት(ኦሪጅን) ለመግለጽና ለማብራራት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ እነዚህንም በአራት ንኡሳን ክፍሎች መድቦ መመርመር እንደሚቻል ፈቃደ ኦክፔውሁን ጠቅሠው ገልጸዋል፡፡ ገላጭ ተረቶች የዓለምን አፈጣጠርና ከዚያ ጋራ የተያያዘውን የሰው ልጅ ገጠመኝ የሚገልጽ ነው፡፡ በአካባቢው የሚገኙትን የልዩ ልዩ ነገሮችና ፍጥረቶች ባሕርይ የሚገልጹ ትረካዎችን ያካትታል፡፡

የማኅበረሰብን ልዩ ልዩ ጠባዮች፣ ዕሴቶችና እምነቶች ለመመርመር የሚተረቱትን በውስጡ ይይዛል፡፡ በተጨማሪም የሰዎችን አነጋገር፣ አለባበስ እና የልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶችከየት-መጣነት እና የመጡበትን ምክንያቶች እና ምንጮች ለመግለጽ የሚተረኩትን የሚያካትት ነው Okpewhu ውስጠ ፈቃደ( 1991፣56-61)፡፡

**2.2.3. ፋቡላ፡-** ከላይ እንደተገለጹት ሁለት የተረት ዐይነቶች ተራች ብዙ ጊዜ የራሱን የግል አስተያየትና መልእክት በተለያየ መንገድ ይጠቁማል ብሎ ያምናል ብዙዎቹ የአፍሪካ ተረቶች ግን ከነዚህ የበለጠ ክፍት ወይም ነጻ ናቸው፡፡ አድማጭ የራሱን አስተያየትና መልእክት እንዲቀርጽ ተራቹና ትረካዎቹ ይፈቅዱለታል ማለት ነው፡፡ Okpewhu ምክንያታቸውንሲገልጹ ብዙዎቹ የአፍሪካ ተረቶች እንደ ሌጀንድ እውነተኛም ይሁን ለሐሰተኛ ታሪክ ለመዘገብ ሆነ የማኅበራዊ ልምድን ኬት መጣ በመመርመር የተደዘኑ (ዲዛይን የተደረገ) ስላልሆነ ነው (Okpewhuውስጠ ፈቃደ1991፣62)፡፡

በተጨማሪም የተረት ዐይነቶችን ኦልሪክ አክሰል፡ ሌይ፣ ሳጋ እና ተረት በሚል ሲከፍላቸው፡፡Finnegan (1992፣137) ደግሞ ሚት፣ አፈታሪክ፣ አድባሬ ተረት፣ የቤት ተረት፣ ተረት፣ ሚሞሬት፣ ግለሰባዊ ትረካ፣ ኤፒክእንደሆኑ ትገልጻለች፡፡

## 2.4. ተረክን የማጥናት ጠቀሜታና የአጠናን ሥልት

አንድ አጥኚ የተረት ጥናት ለማድረግ ሲነሣ ሊከተላቸው የሚገቡ ነገሮች እንዳሉ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Oring ( 1986፣135-142) አንዱ ነው፡፡ እንደ ኦሪንግ ገለጻ በተረክ ላይ ጥናት የሚያደርግ አጥኚ ስለ ታሪኮቹ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖረው እና በተረኮቹም ላይ ዕውቀት-ዐዘል ትርጓሜን ለመስጠት እንዲያስችለው እነዚህን አራት ዐውዶች መረዳት እንደሚጠበቅበት ይገልጻል፡፡ እነርሱምባህላዊ ዐውድ፣ ማኅበራዊ ዐውድ፣ ግላዊ ዐውድእና ንጽጽራዊ ዐውድ ናቸው፡፡

**ባህላዊ ዐውድ፡-** ይህ የዐውድ ዐይነት በተረኮች ውስጥ ያሉ ሐሳቦችን፣ ትእምርቶችን እና በተረኩ የሚገለገሉትን ቡድኖች ባሕርይ የምንለይበት ነው፡፡

**ማኅበራዊ ዐውድ፡-** ተረኩን ማኅበረሰቡ እንዴት እንደሚገለገልበት፣ በተረኩና በሕዝቡ መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል የምናይበት ነው፡፡

**ግላዊ ዐውድ፡-** ተረኮች ከአንድ ግለሰባዊ ታሪክ ጀምረው እስከ ሰፊው ማኅበረሰብ ጉዳይ ድረስ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ግላዊ ዐውድም የአንድን ግለሰብ ግላዊ ብቃትና የሕይወት ልምድ ልናውቅበትና ልንገመግምበት እንችላለን፡፡ ይህንንም ስናደርግ በግለሰቡ በአብዛኛው የሚተረክልን ተረክ የትኛው ነው? ለምንስ ነው ይህን የመረጠው? የተራኪው ማንነትስ ከተረኩ ጋራ ያለው ግንኙነት ምንድነው? የሚሉትን ነገሮች በጥልቀት የሚያሳይ ነው፡፡

**ንጽጽራዊ ዐውድ፡-** ይኼኛው ዐውድ ከላይ ከጠቀሥናቸው ከሦስቱ የዐውድ ዐይነቶች በተወሰነ ደረጃ የሚለይ ነው፡፡ ይኸውም ንጽጽራዊ ዐውድ የዓለምን የፎክሎር ተረክ የሚያነሣ እና በትረካው ላይ ከሚታዩ ሁነቶች ውጪ በመውጣት ተረኩ ሌላ ተረክን የሚጠራ መሆኑን የምንቃኝበት ነው፡፡ ይህ ሲባልግን በሁሉም የተረክ ዐይነት ላይ ትንታኔ ለመስጠትና ትርጓሜለማምጣት ይረዳል ማለት አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ የተረኮቹን መዋቅርና ተምሳሌት በማየት ከሌላ ተረክ ጋራ ሊዛመድ የሚችል ከሆነ በማዛመድ መጠቀም የሚያስችል ነው፡፡ Oring (1986 135-42)፡፡ ይህንን ሐሳብ ሲያብራሩ ከንጽጽራዊ ዐውድ አንጻር ትንታኔ ለመስጠት የመጽሐፍቅዱስን ታሪኮች ማንሣት አንዱ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

## 2.5. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ላይ ትኩረቱን ያደረገው ይህ ጥናት የተመሠረተበት የምርምር ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሃይማኖታዊ እና ማኅበራዊ አገልግሎት፣ የቁሶችንም ተግባር ለመተንተን የሚያስችል ነው፡፡ በጥናቱ የሚካተቱት ተረኮችና ባህላዊ ቁሶች በገዳሙ ለምን ተግባር ይውላሉ? የተረኮቹ መነገር ለገዳሙ ምን ፋይዳ አላቸው? የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲያስችል ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ተመርጧል፡፡ ከተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ጋራ በተያያዘ በቀዳሚነት የሚጠቀሠው William Bascom ነው፡፡ እንደ Bascom ገለጻ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ አራት ተግባራት አሉት፡፡ በዝርዝር ለማየት እንመለስባቸዋለን፡፡ ከዚህ በፊት ግን ስለ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ሌሎች ጸሐፍት ያነሡትን ነጥቦች ላንሣ፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት ያደረገው ሃይማኖታዊ ተረኮችና ባህላዊ ቁሶች ላይ ነው፡፡ ከዚህም ጋራ ተያይዞ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው መስኮች አንዱ ሃይማኖታዊ ፎክሎር እንደሆነ Dorsen (1972፡25) ይገልፃሉ፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በአንድ ማኅበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች በፎክ ቡድኑ ወይም

በማኅበረሰቡ የሚሰጡትን ተግባርና በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን ትእምርታዊ ሆነ ዐውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። ወደ አራቱ ተግባራቶች ስመለስ የማስተማር፣ የማምለጥ፣ የመቆጣጠር እና የማረጋገጥ ወይም የማጽደቅ የሚሉት ይጠቀሣሉ።

**የማስተማር፡-** ይህ የተግባር ዐይነት ሰዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ማኅበረሰቡን መስለውና ሥርዓት ይዘው እንዲቆዩ ያደርጋቸው ዘንድ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚከናወኑትን እያንዳንዳቸውን ድርጊቶች የሚማሩበት ነው። ለምሳሌ ያቀማመጥ፣ ያለባበስ፣ ያወራር፣ ያመጋገብ፣ ያጠጣት ወዘተ. (ዝኒ ከማሁ)።

**የማምለጥ፡-** እንደ Smith(2005፡176)። ገለጻ የማምለጥ ተግባር ባህልና ልማድ በሰው ልጅ ላይ ከጫነበት ደንብ እንዲቀሰቀስ ከወሰነበት ባህላዊ ቁስ ድንበር በተለያዩ ፎክሎሮች በመዝናናት የሚያመልጥበት ነው የማምለጥንተግባር በጂኦግራፊ ከተተከለበት ከጠባብ መንደሩ፣ በጥቅሉም ከምድራዊው ቁሳዊ ዐጥርና ድንበር በምናቡ ያመልጣል። ባዮሎጂያዊ ባሕርዩ አልፈቅድ ብሎ ሊያደርግ የሚፈልጋቸውን፣ ግን ሊያደርግ የማይችላቸውን ድርጊቶች ሁሉ የሚፈጽምባቸው ሥነ ቃሎች አሉ (ፈቃደ 1991፡19)

በመሆኑም የሰው ልጅ በፎክሎሩ አማካይነት ውስጡ ያለውን ስሜት ለመግለጽ ያስችለው ዘንድ ለማምለጥ ይጠቀምበታል። ለምሳሌ ቅኔ ዘራፊው ስሜቱን በቅኔው ይገልጻል፤ የውስጡን ስሜትም በዚያ ውስጥ ይተነፍሳል፤ የማምለጫ መንገዱን በዚያ ትንሽ ቀዳዳ ውስጥ ይጠቀምበታል።

**የመጠበቅ፡-** ይህ የመጠበቅ ተግባር ዐላማቸው አንድ ጎሳ ወይም ማኅበረሰብ በተለምዶ የሚከተላቸውን የአኗኗር ልምዶችና ይትበሀሎች ግለሰቡ እንዲከተል ማድረግ ላይ ቢሆንም በተለይ የሚያነጣጥሩበት ዐላማግን አላቸው። ያም ማኅበሩ ምስጉንና ድንቅ ከሚላቸው ዕሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳርዳር የሚሉትን በ "አርፈህ ተቀመጥ" ግሣጼ ወደ ብዙኃኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው (1991፣20)። ይህ ተግባርም ማኅበረሰቡ በሥሩ ላሉት ትክክል አይደሉም ለሚላቸው ተግባራቶች እንዳይዳረጉ ማኅበረሰቡ የነበረውን ሥርዓት እንዳያጣ፣ ያለውንም ለማስጠበቅ እንዲረዳው የሚጠቀምበት የተግባር ዐይነት ነው።

**የማረጋገጥ፡-**Dorsen (1972፣22) ቡድናዊ ፎክሎር በሐተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶችን፣ ሥርዓቶችንና ባሕርያትን የማጽደቅ ተግባር አለው ሲሉ ይገልጻሉ። ፈቃደም

(1991፣18) ይህንኑ ሐሳብ ሲያጠናክሩ ሰዎች ራሳቸውንና ቁሳዊውን ዓለም ለመግለጽና፣ በጊዜው በነበራቸው ዕቅምም ለመረዳት እንደሞከሩ ጠቁመናል፡፡ ይህንኑ ፈር ተከትለው ማኅበራዊ ድርጊቶቻቸውን እና ልዩ ልዩ ባህሎቻቸውን በሥነ-ቃል አማካኝነት ያጠናክራሉ፡፡ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ ይላሉ፡፡

ይህ የፎክሎር ተግባር ማኅበረሰቡ በሚናገራቸው በሚሰማቸው ተረኮች በሚገለገሉባቸው ቁሶች ውስጥ ያሉት ታሪኮች እውነተኛ መሆናቸውን ተጠይቂያዊና ተጨባጭ በሆነ መንገድ የማረጋገጥ ተግባር አለው፡፡ፎክሎር በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ ጉዳዮች ጊዜያዊ ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታው እንዲቆዩ በተለያዩ ሁኔታዎች አማካይነት የሚያስቀጥል መሆኑን ነው፡፡ ሲቀጥሉም ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡ ሥርዓቱንም ሲያስተምሩ በሚያፈነግጡት ላይ ጨርሰው ወጥተው እንዳይቀሩ የሚያደርጓቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ በተረቶቻቸው አማካይነት ሰዎች ወደ ፈለጉት ዓለም ደርሰው ይመለሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ላይ አራቱም ተግባራት የማይካተቱ መሆኑን ልጠቁም እወዳለሁ፡፡ (Smith 2005፣176) ተግባራዊ ንድፈሐሳብ ፎክሎሮች በቡድን አባላት መካከል ዋጋ የሚሰጧቸው ዕሴቶች መረጃዎች የመለዋወጫ መንገዶች መሆናቸውን የሚያሳይ ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከገዳሚ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ለገዳሚ ያላቸው ፋይዳ ምንድነው? ባህላዊ ቁሶቹስ? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የተረኮቹንና የባህላዊ ቁሶቹን ፍቺ ለማወቅ ይረዳል በሚል በጥናቱ ተመርጧል፡፡

## 2.6. ቁሳዊ ባህል

የDorson (1964:10):: አከፋፈል ከሆነው አራቱ የፎክሎር ዘውጎች መካከል ቁሳዊ ባህል አንዱ ነው፡፡ በቁሳዊ ባህል ሥርም የምናገኛቸው ሀገረሰባዊእጅ ሥራ ሀገረሰባዊ ልብስ፣ ሀገረሰባዊ ምሕንድስና፣ ሀገረሰባዊ የምግብ አሠራርእና ሀገረሰባዊ ሥዕል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

Danielsan ( 986፣101) ሃይማኖታዊ ጉዳይን ለማጥናት የሚነሣ ተመራማሪ የሚያምንበትም ይሁን የማያምንበት ከውስጥ ተነሥቶ መሆን እንደሚገባ ያስረዳሉ፤ ስለዚህ በቅድሚያ ቁሶቹን ሃይማኖቱ ምን ይላቸዋል? እንዴት ይገለገልባቸዋል? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር ወደ ፎክሎር ገጽታቸው ማምጣቱ የተሻለ እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡

ይህም ጥናት በዋናነት ትኩረቱ እምነታዊ (በቤተክርስቲያን) ግልጋሎት የሚሰጡ ቁሶች ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የእምነታዊ አገልግሎት ሥርዓት ማከናወኛ ቁሶች ምን ይባላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ሊያጭር ስለሚችል እግረ መንገዴን መልስ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የቤተክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ማከናወኛ ቁሶች ንዋያተ ቅድሳት በመባል ይጠራሉ፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ማለት ቅድስና፣ንጽሕና፣ ሰማያዊ የሆነው የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባቸው፣ ሥርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው፣የተለዩና የከበሩ የቤተክርስቲያን ንብረቶች ወይም ሀብቶች ናቸው፡፡ የንዋያተ ቅድሳቱ ዐይነትና ቅርጽ እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየውና መጠናቸውንም ለክቶ በሰጠው መሠረት የሚሠሩ ናቸው (ዘፍ፡ 24-28)፡፡

ከብያኔው እንደምንረዳው ሰዎች በውስጣቸው ያለውን ነገር በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው እንደሚገልጹበት ሁሉ የዚህ ስሜት መግለጫ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ ቁሳዊ ባህል መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ይህም ቁሳዊ ባህል በሥሩ ምን ምን ነገሮችን እንደሚይዝ ወይም የቁሳዊ ባህል ዐይነት የምንላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ የተወሰኑ ግንዛቤዎችን ማስጨበጥ የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

ስለ ቁሳዊ ባህል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናትናና ዛሬ የተባለውን መጽሐፍ ሲገልጽ ለኢትዮጲያ የመጀመሪያው ጳጳስ የሆኑት አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያመጧቸውን ቁሶች፣ የከበሩ አልባሳት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ተግሣጻትና የቤተክርስቲያን ጌጣ ጌጥ፣ መስቀልና ጽንሓሕ ነበሩ፡፡

Glassie (1991፣1)እንዲሁየቁሳዊ ባህል ጥናት በተፈጥሮና በባህል መካከል ያለን ልዩነት በአእምሯችን በመሳል በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን በማስቀደም ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንለዋውጥበት፣ አዲስ አቅጣጫ የምናስይዝበት፣ መንገድ እና የምናጤንበት ዘዴ መሆኑንይገልጻሉ፡፡

ፈቃደም 1991፡5 ቁሳዊ ባህልን ሲገልጹ በዐይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሠሠውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህን ቁሳቁሶች የተሠሩባቸውን ዘዴዎች ወይም ቴክኒኮች፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር፣ የቅመም አቀማመን ብልኀት፣ የልብስን፣ የቤትን፣ የዐጥርን ወዘተ አሠራር፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎች የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል በማለት ነው፡፡

### 2.6.1.የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች

ቁሳዊ ባህልን በተለያየ መንገድ መተንተን ይቻላል፡፡ ይህንንም በተጨባጭ መረጃዎች በመደገፍ ማሳየት ጥናቱን የተሻለ ለማድረግ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ከዚህም በመነሣት የምሁራንን ምደባ ዋቢ በማድረግ ቁሳዊ ባህል የሚተነተንባቸውን የተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎች እንቃኛለን፡፡

Brown (1982፣2) ቁሶችን በምድብ በምድብ፣ ከፋፍሎ ማስቀመጥ አስቸጋሪ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ምክንያቶቻቸውን ሲያስቀምጡ የመጀመሪያው የቁሶች ዐይነትና ቁጥር ብዙ ሆኖ መገኘት ሲሆን ሌላው የሚያስማማ አንድ ወጥ የሆነ መስፈርት አለመገኘት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የእራሱን የመተንተኛ ሂደቶች ገለጻ (description፣ ትርጓሜ (deduction) እና ማመላከት (Speculation)ናቸው በማለት አስቀምጧል፡፡[1]

**ገለጻ፡-** በትንታኔያችን ወቅት የምናስቀድመው ተግባር ነው፡፡ ቁሱን እኛ እንዳየነው ሁሉ ያላዩ ሰዎች በአእምሯቸው እንዲሥሉት ማድረግን ይመለከታል፡፡ ይህንንም ስናደርግ፣ የቁሱን ቅርጽ፣ የተሠራበትን ንጥረ ቁስ፣ ክብደቱን፣ ርዝመቱን፣ መልኩን ወዘተ. ያካተተ መሆኑን እነሰረዳላን፡፡

**ትርጓሜ፡-**ይህን በናሙና ቁሱ ላይ የነበረውን ትኩረታችንን መለስ በማድረግ በቁሱና በባለቤት ማኅበረሰቡ መካከል ያለን መስተጋብር የምናጤንበት፣ ወዲያውም አንዳች ትርጓሜ የምንሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ትርጓሜ በገለጻ ወቅት ትኩረት የሰጠንባቸውን ጉዳዮች በድጋሚ እንድናስተውል የሚያደርገን፣ ከዚህም ጋራ ተያይዞ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ቁሱ አንዳች ውክልና ካለው፣ ውክልናው ምን እንደሆነ የትርጓሜ ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡

**ማመላከት፡-** አጥኚው የገለጻ እና የትርጓሜ ተግባሩን ከጨረሰ በኂላ የሚከተለው የትንታኔ ሂደት ሲሆን፣ በሁለቱ ተግባራት ያገኛቸውን መረጃዎች በመያዝ የሚወክለው ነው፡፡በተጨማሪም ቁሳዊ ባህል÷ባህሉን የሚያጠናው አካል ከላይ በተጠቀሡት ደረጃዎች ያገኛቸውን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ቁሱን መመርመር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

---

[1]ይህንን አስመልክቶ Brown (1982:2) እንዲህ ብለዋል "Material culture is the study through artifacts at the beliefs- values, ideas, attitudes and assumption at a particular community or society at given time" Brown (1982:2)

## 2.7. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ ዐሥራ አራት ተዛማጅ ጽሑፎች ተቃኝተዋል፡፡ ጥናቶቹ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዲግሪ፣ በታሪክ ትምህርት ክፍል እና በቅድስት ሥላሴ የሥነ መለኮት ኮሌጅ የተሠሩ ናቸው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ የጥናት ክፍል ሰፊ የሆነ ትንታኔ እና ሒስ የተሰጠባቸው ጥናቶች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሠሩት ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ትምህርት ክፍሉ መረጃን ከመሰነድም በላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማየት ሰፊ ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡

### 2.7.1. በቅድስት ሥላሴ የሥነ መለኮት ኮሌጅ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ

ሰለሞን ገብረ ሚካኤል 2007 ዓ.ም "The Brief History Entoto Hamere Noan Kidane Mihret Monstery of Addis Ababa" በሚል ርዕስ የሰሩት ጥናት አለ፡፡

ጥናቱ የገዳማትን ታሪክ ማወቅ ያለው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ፣ የመነኮሳቱ የአኗኗር ሥርዓት ምን እንደሚመስልና የገዳሙ ችግሮች ምን ዐይነት ገጽታ እንዳላቸው ማሳየት የሚሉ ነጥቦችን የጥናቱ ዐላማ አድርጓል፡፡ ሰሎሞን በጥናቱ የገዳሙንመልክአ ምድራዊ አቀማማጥ፣ የገዳሙን አመሠራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር እና የገቢ ምንጮቹን ተንትኗል፡፡ አጥኚው በጥናቱ የገዳሙን አመሠራረት፣ አስተዳደራዊ መዋቅር እና የገቢ ምንጮቹን ቢገልጽም ገዳሙ አሁን ያለበት ሁኔታ ከተነሣበት ዐላማ አንጻር በሰፊው አልተብራራም፡፡ በተጨማሪም ገዳሙ ምን ዐይነት የገዳም ሥርዓት እንደሚከተል ተጠቅሦ አናገኝም፡፡ እንዲሁም ገዳሙን ከሌሎች ገዳማት በተለየ ለጥናቱ የመረጠበትንአነሣሽ ምክንያት ለማሳየት አልሞከረም፡፡ ይህ ጥናት እስካሁን ከተቃኙት ጥናቶች በተለየ ከእኔ ጥናት ጋራ የሚያመሳስለው ነገር በተመሳሳይ ገዳም ላይ መሥራታችን፣ የገዳሙን አመሠራረት ማየታችን ነው፡፡ ልዩነቱ የእኔ ጥናት የገዳሙን ቁሳዊ ባህል እና ተረክ በሰፊው መመልከቱ ነው፡፡

ኃይለሚካኤል ወልደ ተክለሃይማኖት 2005 ዓ.ም "A brief History of Debrahayk Saint Stephen Abuna Iyasus Moa Communal Monastery in South Wollo".

የጥናቱ ዐላማ የሐይቅ ደብረ እግዚአብሔርንና የቅዱስ እስጢፋኖስን ገዳም ታሪክ በማስተዋወቅ፣አባ ኢየሱስ ሞአ ለገዳሙ ያደረጉትን አስተዋፅኦ በማሳየት የገዳሙን

አስተዳደራዊ ሁኔታ ቃኝቷል፡፡ ገዳሙ በመንፈሣዊ ትምህርትያደረገውን እና እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል በጥናቱ ላይ አንስቷል፡፡

ኃይለሚካኤል በጥናቱ ስለ ምንኩስና ሕይወት፣ የደብረ ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስና ደብረ እግዚአብሔርንገዳም አመሠራረት፣ የገዳሙን መልከአ ምድራዊአቀማመጥ፣ የአቡነ ኢየሱስ ሞአን ወደ ሐይቁ መምጣት፣የዘጠኙ ቅዱሳን አመጣጥ እና የገዳሙን አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርዝሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በገዳሙ ያለውን ዘመናዊ የቀሳውስት ማሠልጠኛ ተቋም ገጽታና ቀሳውስቱን አስገብቶ ለማስተማር የሚጠቀሙበት የመመልመያ መሥፈርት ምን ምን እንደሆነ በጥናቱ ላይ አሳይቷል፡፡ ኃይለሚካኤል የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አመሠራረት እና የምንኩስና ሕይወት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ቢጠቅሥም በገዳሙ ላይ ያሉ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን አለመመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ተግባሩ አዳነ በ2002 ዓ.ም “A Breif history of Dima Giorgis Monastry” በሚል ርእስ 2001 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል፡፡ በጥናቱም የገዳሙን አመሠራረት፣ ገዳሙ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የፈጸመውን ተግባር፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የገዳማውያኑን የገቢ ምንጭ እና ገዳሙ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ በዝርዝር አቅርቧል፡፡

የጥናቱ ዐላማ የገዳሙ ቅርሶች በአግባቡ እየተጠበቁ ባለመሆናቸው የሚጠበቁበትን መንገድ ማመላከት፣ በገዳሙ እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የሁለት ገዳማውያንን ታሪክ በመጻፍ ለበጎ ሥራቸው ዕውቅና መስጠት ነው፡፡ እንዲሁም ገዳሙ በኢኮኖሚ የሚያድግበትን ሁኔታ ማመላከት እና ወደ ከተማ የሚፈልሱትን ገዳማውያን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማመላከት ናቸው፡፡ ጥናቱ የገዳሙን አመሠራረት እና ገዳሙ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ ማሳየቱ ከዚህ ጥናት ጋራ ያመሳስለዋል፡፡ ልዩነቱ የእኔ ጥናት ተረኮችን እና ቁሳዊ ባህሎችን መቃኘቱ ነው፡፡

ዘላለም አሰፋ 2001 ዓ.ም “A Brief history of Activities of Zeway Debre Tsion Monastry በሚል ርዕስ) ጥናቱ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዐላማ የደብረ ጽዮን ገዳም አመሠራረት እና በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ ነገሮች ለባህል እና ቱሪዝም ያላቸውን ፋይዳ አጉልቶ ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱ በኢትዮጵያ የገዳም ሕይወት አጀማመር ምን ይመስል እንደነበር፣ ገዳሙ የሚገኝበት አካባቢ መልከአ ምድራዊ እና አጠቃላይ ገጽታ ምን ዐይነት መልክ እንዳለው እና ገዳሙ በውስጡ የያዛቸው ታሪካዊ

ቅርሶች ምን እንደሆኑ አሳይቷል፡፡ የዘላለም ጥናት የገዳሙን አመሠራረት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ በመግለጹ ከእኔ ጥናት ጋራ ይመሳሰላል፡፡ የጥናቱ ስፍራ፣ የተካሄነበት የምርምር አቅጣጫ እና በጥናቱ ያገኘናቸው ግኝቶች ልዩነታችን ናቸው፡፡

መንግሥቱ ከበደ 1999 ዓ.ም The role of Debre Libanos Monastery in the Ethiopian orthodox Tewahedo Church በሚል ርዕስ ይህ ጥናት ዐላማ አድርጎ የተካሄው የደብረ ሊባኖስን ገዳም አመሠራረት እና ገዳሙ ለኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ያለውን ሚና ማሳየት ነው፡፡ መንግሥቱ የደብረ ሊባኖስን ገዳም መንፈሳዊ ግልጋሎት ከመግለጽ ባሻገር ከቅርስ ጥበቃ እና ከልማት አኳያ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እና በኢብን ኢብራሂም ወረራ ወቅት በገዳሙ ላይ የደረሱ ጉዳቶችን በጥናቱ ላይ ተንትኖ አቅርቧል፡፡ የገዳሙን አመሠራረት ማንሣቱ እና ገዳሙ ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን አስተዋፅኦ መግለጹ ከዚህ ጥናት ጋራ ያመሳስለዋል፡፡

### 2.7.2. በታሪክ ትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ

ጥጋቡ በዜ 2001 ዓ.ም “The Ethiopian Clain in the Monastery Deires- Sultan In (Jerusalem 1850-1994)” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ ተቃኝቷል የጥናቱ ዋና ዐላማ ከ1850-1994 ዓ.ም ድረስ በገዳሙ ላይ የተከሰቱ ልዩ ልዩ ችግሮች በዝርዝር ማሳየት ነው፡፡ በሥሩ የገዳሙን አመሠራረት እና ከገዳሙ ጋራ ግንኙነት ያላቸውን የንግስተ ሳባን እና የንጉስ ሰሎሞንን ግንኙነት ታሪክን መሠረት በማድረግ ቀርቧል፡፡

ጥናቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስራኤልን እና የኢትዮጵያን ግንኙነት፣ የንግሥተ ሳባን እና የሰሎሞንን ግንኙነት፣ በኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረገውን መንፈሳዊ ጉዞ፣ የጉዞውን ፈታኝነት በመረዳት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት በቋሚነት እንዴት መኖር መጀመራቸውን፣የጼር ሡልጣን ገዳም አመሠራረት እና በኋላ ላይ በግብጾች የመነጠቃቸውን ምስጢር ዘርዝሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግብጽ እና የኢትዮጵያን መልካም ግንኙነት መቋረጥ፣ ዐፄ ዮሐንስ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ችግር ለመቅረፍ ያደረጉትን ሙከራ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሣት ትንተና ሰቶበታል፡፡ ጥጋቡ በጥናቱ ላይ የተጠቀሡትን ነጥቦች አንሥቶ ቢተነትንም ከጥናቱ ጋራ ተዛማጅነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ቅኝት አላደረገም፡፡ ይህ ጥናት ከጥጋቡ ጥናት ጋራ የሚለየው የእኔ ጥናት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተተረኩ ተረኮችን እና ቁሳዊ ባህሎችንመሠረት ማድረጉ

ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ ከጥናቱ ቦታ፣ ከተነሣንበት ዐላማ እንዲሁም ከደረስንለት ግኝት አንጻር እንለያያለን፡፡

*ሀብታሙ መንግሥቱ* (1998 ዓ.ም)"A history of Monastry of Mertulamariame (c1500-1974)"በጥናቱ *መርጡለ ማርያም* ቤተክርስቲያን ከመመሥረቷ በፊት የነበረው አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ቤተክርስቲያኑ የተቋቋመበትን ዘመን እና ቤተክርስቲያኑ ወደ ገዳምነት ያደገበት ሒደት በጥናቱ ላይ በሰፊው አቅርቧል፡፡ ጥናቱበኢብን ኢብራሂም አልጋዚወቅት በገዳሙ ላይ የደረሰው ጥፋት ምን ይመስል እንደነበር ተንትኗል፡፡ ሀብታሙ በጥናቱ የገዳሙን አመሠራረትጋራቢገልጽም በገዳም አመሠራረት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ቁሳዊ ባህሎች የሚኖራቸውን ፋይዳ አለመዳሰሱ የጥናታችን ልዩነት ነው፡፡

### 2.7.3. በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ

የዮሴፍ ቦኪ 2009 ዓ.ም"የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ታሪክ ጥናት"ጥናቱ ይዞት የተነሣው ዐላማ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ውስጥ የሚነገሩ ተረኮችን መመርመር፣ መፈከር እና መተንተን እና  የተረኮቹን ፋይዳ ማብራራት ነው፡፡ አጥኚው በጥናቱ ምልከታን ቃለ መጠይቅን እና የመረጃ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፤እነዚህንም ዘዴዎች ምንነት በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ለጥናቱ እውን መሆን የተሰበሰቡት መረጃዎች በተግባራዊ  እና በሥነ ተረክ ንድፈ ሐሳብ መታገዚያነት ተንትነው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱም የቀረበበት የቋንቋ ብልነት ገላጭ ተንታኝ ነው፡፡

እነዚህን ንድፈ ሐሳቦች የተለያዩ የዘርፉን ምሁራን ዋቢ በማድረግ በሰፊው ተብራርተው በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ቀርበዋል፡፡ አጥኚው ጥናቱ በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ላይ ብቻ የሚገደብ መሆኑን በጥናቱ ወሰን ላይ ገልጿል፡፡ ተረኮቹንም ወሰኑን መሠረት በማድረግ የተነተነበት መንገድ በጥናቱ የትንታኔ ክፍል ላይ ታይቷል፡፡ እነኚህ የጥናቱ ጥሩ ጎኖች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ ላይ የተመለከትኩት የመደጋገም ነገር አለ፡፡ይኸውም አጥኚው በጥናቱ ዳራ ላይ ስለ ምንኩስናና ምናኔ መስፋፋት ተጠቃሽ የሆኑ ምክንያቶችን ዘመናትን የጠቀሰውን በድጋሚ የገዳማውያን ጅማሮ በሚል በምዕራፍ ሦስት ላይ በተወሰነ መልኩ ቀርቦ እናገኛለን ይኸም ባንድ በኩል ቸልተኝነት በሌላ በኩል ለመረጃ ቅርብ አለመሆንን ያሳያል፡፡

ሌላው ብዙ ጊዜ የመስክ መረጃዎች ሲሰበሰቡ በዕድሜ የገፉ ማለትም በምናጠናው ነገር ብዙ ልምድ ያላቸውና ለጉዳዩ ቅርብ የሆኑ ቢሆኑ ይመረጣል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ላይ መረጃውን በመስጠት የተባበሩት ግለሰቦች በአርባዎች ዕድሜ ውስጥ ያሉ ናቸው። ለምን? ከዚያ ዕድሜ በላይ ያሉ ሰዎችን ባለማግኘቱ ነው? ወይስ ሌላ ምክንያት አለ? ካለ ምክንያቱን ሊያስፈር ይገባ ነበር። ሌላው እንደ ተጨማሪ ክፍተት ያየሁት የተሰበሰቡት ተረኮች ብዛታቸው ዘጠና ሰባት ቢሆንም የመረጃ አቀባዮቹ ቁጥር ግን ሰባት ብቻ ሆነው መገኘታቸው ነው። ይህ ማለት አንድ መረጃ አቀባይ ከዐሥር በላይ ተረክን ተናግሯል ማለት ነው ይህም የጥናቱን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የዮሴፍ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ የሚያመሳስለው አንድም ገዳም ላይ መሠራቱ፣ ስለ ገዳማውያን ታሪክ መዳሠሡ በተጨማሪም ተረኮች ላይ ማተኮሩ ነው። የጥናቱ ስፍራ እና በእኔ ጥናት ቁሶችን በተጨማሪ ግብአትነት ማየቱ የጥናታችን ልዩነት ነው። እራሷ የምታስተካክለው።

ፍጹም ኩራባቸው (2006 ዓ.ም)። "የዝዋይ ደሴያት ገዳም እና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" ጥናቱ ዐምስት ምዕራፎች አሉት።አጥኚው የጥናቱን አነሣሽ ምክንያቶች ሲገልጽ ከዚህ ቀደም በደብረ ሲና፣ ገሊላና ደብረ ጽዮን ደስያት መጓዙ እና በጉዞውም ደስያቱ የተለያዩ ቅርሶች መገኛ መሆናቸውን መገንዘቡ ነው። ይህም ወደ ፎክሎር ትምህርት ተማሪነት በመጣበት ወቅት በዚህ ዙሪያ የተሠሩ የፎክሎር ጥናቶች አለመኖር ለጥናቱ እንዳነሣሣው ይጠቅሣል። ሌላው የአጥኚው ዐላማ በዝዋይ ደስያት ገዳማትና አድባራት መመሥረት የተገኙ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን ምሳሌ፣ ዘይቤና ትእምርት አንድምታ መርምሮ በማብራራት ተምሳሌታዊ ፍቺያቸውን በመፈከር የተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን ፋይዳ ማብራራት ነው። ከዚህም ዐላማ በመነሣት ጥናቱ ይመልሳቸዋል ያላቸውን ጥያቄዎች በትንታኔው ክፍል ተግባራዊ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህም የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው።

ለርእሰ ጉዳዩ መመረጥ እንደ ዐቢይ ምክንያት የሚጠቀሡት ምን ምን እንደሆኑ በጥናቱ ላይ ሲገልጽ የዝዋይ ሐይቅ ደስያት በታሪክ አጋጣሚ የታቦተ ጽዮን መሸሸጊያ መሆናቸውን የሚናገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች መኖራቸውና የገዳማውያኑን ሕይወትከገዳማቱ አድባራቱ ጋራያቆራኙ ማኅበረሰቦች መገኘታቸው ነው። ለጥናቱም ግብ መምታት የምርምር ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲያገኙ ቃለ መጠይቅንና ምልከታን በመጠቀም መረጃ የሰበሰበ መሆኑን በጥናቱ ላይ ተገልጾ እናገኛለን። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹንም የተለያዩ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ በምን እንደመረጣቸው በቂ ማብራሪያ ሰጥቷል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተረክ ንድፈ

ሐሳብ፣ በቁሳዊ ባህል ፅንሰ ሐሳብ ሞዴሎችንና ተረክንም ሆነ ቁሳዊ ባህልን ለመፈከር በሚያስችለው ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ፣ተተንትነው፣ በገለጻና ትንተና ሥርዓት ተብራርተው ቀርበዋል። እነኚህ የጥናቱን ጠንካራ ጎኖች አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ ጥናት የተወሰኑ ክፍተቶች አሉት። ተዛማጅ ጥናቶች ብሎ የጠቀሳቸውን ስራዎች ስንመለከት ከእርሱ ጥናት በፊት የትምህርት ክፍሉ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ቢሆንም አጥኚው ግን ሦስት ብቻ ማየቱ በተጨማሪም በስነ-ልሳን ትምህርት ክፍል የተሰራ ብሎ የገለፀውና ሰፊ ማብራሪያ የሰጠበት የእንደሻው ወ/ሚካኤል2007።“A Study of Ethincity Relationship Among zay” የተሰኘውን ጥናት ስንመለከት በምን መንገድ ከጥናቱ ጋራ ተገናኝቶ ይህንን ሁሉ ማብራሪያ እንደተሰጠበት መረዳት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም የፍጹም ጥናት የገዳማትን የአድባራትን ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ማጥናት ነው። የእንደሻው ጥናት ደግሞ ትኩረት ተሰጥቶበት የምናገኘው ነጥብ በስደትና ቋንቋ ቅየራ ዐውድ ውስጥ የዚያን ቋንቋ ተናጋሪ አሁን ያለውን የጎሳ ሥነ-ልሳን ሁኔታ መመርመር ነው።

ይህም በጥናቱ እንደ ክፍተት የሚታይ ነው። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ ተረኮችን እና ቁሳዊ ባህሎች ማየቱ፣ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ መጠቀሙ ሲያመሳስለን፣ ልዩነታችን ጥናታችንን ያደረግንበት ስፍራ እና በጥናታችን የደረሰንበት የመጨረሻ ግብ ይጠቀሣሉ።

ተስፋዬ ተገኝ 2003 ዓ.ም“በደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ እየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሠራረት ቁሳዊ ባህል ጥናት” የቀረበው ሌላው የተዳሰስኩት ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዐላማ የሆነው የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአን አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ማጥናት ነው። በዚህም ሥር አራት ዝርዝር ዐላማዎች ተካተዋል። በጥናቱ ላይ በተግባር መታየታቸው የጥናቱ አንዱ ጠንካራ ጎን ነው።

ምዕራፍ ሁለት ስለ ገዳማዊ ሕይወት አጀማመርና መስፋፋት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል እንዲሁም ዐይነታቸውን በዝርዝር በጥናቱ ላይ መካተቱ የጥናቱ ሌላው ጠንካራ ጎን ነው። ጥናቱ በርካታ ክፍተቶች የተስተዋሉበት ነው። ጥናቱ ዳራ የለውም። የጥናቱ ወሰንም የዳራውን ቦታ ይዞ ነው የምናገኘው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹን የገለጸ ቢሆንም ሰፋ ያለ ትንታኔ ሲሰጥበት አንመለከትም። የመረጃ ዘዴዎቹን እንዴትና ለምን እንደተመረጡ የሚገልጹ ምሁራዊ መረጃዎች በጥናቱ ላይ አይታዩም። የተዛማጅ ሥራዎችን በሚቃኝበት ወቅትም ዘርዘር ያሉ ሐሳቦችን ሲያነሣ አይስተዋልም፤ከእርሱ ጥናት ጋራ ያላቸውን ልዩነትና አንድነት ከመግለጽ ውጪ ጥናቶቹ ያለባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎን በሰፊው አይቃኝም፤ ወደ

ትንታኔው ክፍል ስንመጣ ተረኮቹን በተከታታይ ከማስፈር ውጪ ምንም ዐይነት ትንታኔ ሲሰጥ አይታይም፡፡

በተጨማሪም ትንተና የተሰጠባቸው ቁሶች በፎቶ ተደግፈው አልቀረቡም፡፡ ጥናቱ ቁሳዊ ባህል ላይ እንደማተኮሩ ሁሉም ባይሆኑ እንኳን የተወሰኑት በጥናቱ ላይ ሊሰፍሩ ይገባ ነበር፡፡ከዚያ ይልቅ ግን አጥኚው ያስቀመጠው ቁጥሩም የለም ላለመባል የሚመስል ነው፡፡

የተስፋዬ ጥናት በገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ላይ መሠራቱ ከእኔ ጥናት ጋራ ያመሳስለዋል፡፡ ልዩነታችን የእኔ ጥናት ተረኮቹ ከቁሶቹ ጋራ ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል በተረኮቹ መፈጠር የቁሶቹ አስተዋፅኦ እምን ድረስ እንደሆነ በሰፊ የዳሰሰ ነው፡፡ በተጨማሪም የፎክሎር መተንተኛ ንድፈ ሐሳቦች በስራዬ ተዳሰው ተግባራዊ የተደረጉ መሆናቸው ጥናቴን ከተስፋዬ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

በሞገስ ጀምበሩ2003 ዓ.ም “ከደጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ሥርዓቶች” የቀረበው ጥናት ስድስት ምዕራፎች ያሉት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፎችም ጥሩ የሚባል ትንታኔዎችን አድርጓል፡፡ የአጥኚው ትኩረት የሆነው በገዳሙ የሚከበሩ ትረካዎች እና ፋይዳቸው ላይ በመሆኑ ለጥናቱ የመረጠው ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ዐላማውን ያሳካለት ነበር፡፡ የዚህ ጥናት ይመለሳሉ ያላቸው እያንዳንዱ ዐላማዎች ከግብ ደርሰዋል፡፡ ከጥናቱ መግቢያ ስንጀምር ጥናቱ ላይ ምንምን ነገሮች እንደተካተቱ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጧል፡፡

ሌላው የገዳማዊ ሕይወት አጀማመርን ከጣና ሐይቅ ደሴያት ጋራ በተያያዘ ያቀረበው መረጃ ጥሩ ገለጻየሚታይበት ነው፡፡ በጥናቱ የዐባሪ ክፍሎችም ፎቶዎች እና የቃለ መጠይቅ መረጃዎች በሥርዓት ዋቢ መደረጋቸው የጥናቱን ጥንካሬ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በጥናቱ እንደ ደካማ ጎን የሚታዩ ዳራው እጅግ ከመስፋቱ የተነሣ አንዳንድ ቦታ ላይ የጥናቱን አነሣሽ ምክንያቶች የምናገኝበትና የዳራውን መንፈስ የሳተበትን ነገር እንመለከታለን፡፡ የተዛማጅ ሥራዎችን በሚቃኝበት ወቅት በበቂ ሁኔታ የአጥኚዎቹን ጥናካሬና ድክመት አለማካተቱ በትንታኔው ወቅት አረጋጋጭ የሆኑ ቃላት አለመጠቀሜ ለምሳሌ ይመስለኛል፤ ምናልባት ወዘተ የሚሉ ቃላት ይጠቀሣሉ፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የታተሙ ጽሑፎች እንደሆኑ ቢገልጽም የተብራራ

ነገር አናገኝበትም፡፡ በጥናቱ ቃላዊ ተረኮችና የአምልኳዊ ሥርዓቶች (ሀገረሰባዊ ልማዶቹ) የተገኙበትን ነገር ሲያስቀምጥ አይታይም፡፡

የሞገስ ጥናት የገዳሙን አመሠራረትና ተረኮችን መቃኘቱ፣ በተጨማሪም ጥናቱን ለማሳካት የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን መጠቀሙ ከዚህ ጥናት ጋራ ያመሳስለዋል፡፡ የሚያለያየው ሞገስ በጥናቱ ላይ አምልኳዊ ሥርዓቶችን የቃኘ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ከዚህ ይልቅ ከተረኩ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ቁሶች በመቃኘትና ቁሶቹንም በፎቶ በማስደገፍና በማብራራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

የምሕረት ተስፋዬ 2003 ዓ.ም "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" የጥናት ዐላማ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳማውያኑ ዘንድ እምነትን በመትከልና በመጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱ የተገለጹት ዐላማዎች በጥናቱ የውስጥ ክፍል ተግባራዊ መሆናቸው እና ጥናቱ የገዳማዊ ሕይወትን አጀማመር በሰፊውና በተተነተነ መልኩ ማቅረቡ አጥኚው የሚጠቀሡ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡ ሌላው ጠንካራ ጎን ቁሳዊ ባህልን በመተንተን እያንዳንዱን ቁስ በፎቶ ማስደገፉ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ጥናት የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖችም ያሉት ነው፡፡ ለምሳሌ የመረጃን መሰብሰቢያ ዘዴ በምክንያትና በመረጃ ያለመቅረብ፣ የመረጃ አቀባይና የናሙና አመራረጡ በምሁራን ሐሳብ የታገዘ አለመሆን፣ ስለ ተጠቀመው ተምሳሌታዊ መስተጋብራዊ ንድፈ ሐሳብ ምንነት የተብራራ ነገር አለመግለጽ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሚያደርግበት ወቅት የጠለቀ ዕይታን አለማሳየት ይጠቀሣሉ፡፡ በምዕራፍ ሦስት የቀረበውንም መረጃ ስንመለከት የተዘበራረቁ ነገሮች ያሉበት ነው፡፡ በተረኮቹም ላይ እንዲሁ በቂ የሆነ ማብራሪያዎች ሲሰጥባቸው አይታይም፡፡ በምዕራፍ አራትም ላይ ያስፈራቸውን የገዳማውያኑን አመጋገብ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች በተመለከተ ሥርዓታቸውን ከመዘገብ ያለፈ ተምሳሌታዊ ፍቻቸውንም ሆነ ፋይዳቸውን ሲያነሣ አይታይም፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ ክፍል ውስጥ ምንም ዐይነት የፎቶ መረጃዎችን አናገኝም፡፡ ለምን ይህ እንደሆነ በጥናቱ ላይ ባጋጠሙ ችግሮች አልተገለጸም፡፡ በዐባሪም ላይ ቢሆን እንዲሁ አንድ የቁሳዊ ባህል ጥናት ሊኖረው የሚገባውን ያህል የፎቶ መረጃ ተካቶ አይታይም፡፡ እነኚህም የጥናቱ ክፍተቶች ሆነው ታይተዋል፡፡

የእኔ ጥናት ከምሕረት ሥራ ጋራ ሙሉ በሙሉ በርእሰ ጉዳዩ አንድ ዐይነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጥናታችን ስፍራ፣ ያገኘናቸውን መረጃዎች የተነተንበት መንገድ፣ የተጠቀምናቸው ንድፈ ሐሳቦች ይለያያሉ፡፡ የእነዚህም መለያየት በደረንበት የጥናት ግኝት መለያየት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡

ታደሰ አይችሉህም 1999 ዓ.ም "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ሥርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ከትምሕርታዊ አንጻር በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም" ጥናቱን በዐምስት ምዕራፎች ከፋፍሎ አቅርቧል፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዐላማ፣ ወሰን፣ አነሣሽ ምክንያት፣ ዘዴ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች በሚል ዘርዝሮ ለማየት ሞክሯል፤ በሁለተኛው ምዕራፍ የኢትዮጵያን የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊ አጀማመር፣ የገዳም እና የምንኩስና ሕይወት ዓለም ዐቀፋዊና ኢትዮጵያዊ ታሪኮች ጽፏል፤ በሦስተኛው ምዕራፍ ተዛማጅ ጽሑፎችን ዳስሷል፡፡ በምዕራፍ አራት እና ዐምስት የገዳማቱን አስተዳደርና የሥራ መዋቅር፣ የምንኩስና አቀባበል ሥርዓት፣ የግጭት አፈታት ዘዴ፣ የመነኮሳቱን የአመጋገብ ሥርዓትና ጊዜ እና የአለባበስ ዐይነት እና ሌሎችም ላይ ትንተና ሰጥቷል፡፡ አጥኚው የጥናቱ ዐላማ በአንድነት ገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳት መሆኑን ገልጿል፡፡ መረጃውንም የመስክን ምልከታና ቃለ መጠይቅን በመጠቀም የሰበሰበ ሲሆን ለመረጃ ትንተናው ትእምርታዊ-መስተጋብራዊ ንድፈ ሐሳብን እና ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በመግቢያው ላይ የወንዶችንና የሴቶችን ገዳም እንደሚያይ ቢነግረንም በትንታኔው ላይ ግን የሴቶችን ገዳም በመረጃ አለማግኘት ዕጥረት እንደማያካትት የገለጸበት መንገድ በጥናቱ ያለውን ተአማኒነት የሚያሳይ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ ድክመት የሁለተኛ ዲግሪ የተሠሩ ጥናቶች ቢኖሩም እነርሱን አለማካተቱ ይታያል፡፡ በመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ላይ ብቻ መወሰኑ እንዲሁም እነዚህንም ጥናቶች ቢሆን ሰብስቦ እንዳለ ከማስፈር ውጪ የእርሱ ጥናት ከእነርሱ ጥናት የሚለይበትን መንገድ ግልጽ በሆነ መንገድ አለማስቀመጥ ይታይበታል፡፡

የታደሰ ጥናት የገዳማትን የአስተዳደር የሥራ መዋቅር፣ የአበምኔትን አመራረጥና የሥራ ኀላፊነት፣ የምንኩስናን አቀባበል ሥርዓት፣ የግጭትን አፈታት .... ወዘተ. ጉዳዮች

ማንሣቱከእኔ ጥናት ጋራ አያገናኘውም፤ ከዚህ በተጨማሪም ከገዳሙ አመሠራረት ጋራ የተያያዙ ጉዳዮችንና ታሪካዊ ፅንሰ ሐሳቦችን አለመዳሠሡ ከዚህ ጥናት ጋራያለያየናል። ከጥናቱ ጋራ የሚያመሳስሉት ጉዳዮች ስለገዳም የተወሰኑ ዳሠሣዎችን ማድረጉና የፎክሎር አንዱ ክፍል የሆነውን ቁስ ማየቱ ነው።

ከእነዚህ ዐሥራ ሦስትጥናቶች ከአብዛኛው ጋራ በዋናነት የሚያመሳስሉን በኢትዮጵያ ሥነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የገዳማት አመሠራረት፣ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህልን እና ፎክሎራዊ ገጽታን መሠረት አድርገው የተሠሩ መሆናቸው ነው። ዋንኞቹ ልዩነቶች ለማጥናት የተመረጡት ስፍራዎች የተነሡበት የምርምር አቅጣጫዎችና በጥናቶቹ የተገኙ ግኝቶች ናቸው። በዚህ ጥናት በተዳሠሡት ሥራዎች ውስጥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በተብራራ መንገድ አለመጥቀሥ፣ ተዛማጅ ሥራዎች ላይ በሚካሄድ ቅኝት ላይ የእነርሱ ጥናት ከቀደሙት ጥናቶች የሚለዩባቸውንም ሆነ አዲሱ ጥናት ይዞት የመጣውን የተለየ ነገር ምንነት በሰፊው አለመግለጽ፣ (ሒሳዊ ግምገማ አለመስጠት) ጥናቱ የሚቀነበብበትን ንድፈ ሐሳብ አለማካተት ቢያካትቱም፣ ተገቢውን ገለጻ አለማቅረብ እና በጥናቱ ውስጥ የሚገኙ ትእምርቶችን አለመተርጐም በአብዛኛዎቹ ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች ናቸው።

## ምዕራፍ ሦስት

# 3. ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራና የተያያዥ ጉዳዮች ዳራዊ ገለጻ

## 3.1. ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራ መልክአ ምድራዊ ገለጻ

የእንጦጦ ከተማ በዐፄ ዳዊት አማካኝነት በ1330 ዓ.ም ነው የተመሠረተችው፡፡ አሕመድ ግራኝም በ1521 ዓ.ም ወደ እንጦጦ ከተማ በመምጣት የእንጦጦ ማርያምን ሲያቃጥል ህዝቡ ንዋያተ ቅድሳቱን በመደበቅ ሸሸ፡፡ በዚህም ጊዜ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተደርምሳና ቤተክርስቲያኗምተሸፍና ሳያያት እንዳለፈ የቃል አስረጂዎች መርጌታ ነቅዐ ጥበብ መምሬ ልሳነ ወርቅ ይገልጻሉ፡፡ ግራኝም የእንጦጦ አካባቢን በሙሉ በመቆጣጠር የቀድሞ መጠሪያዋን ዲላ ዲላ ወደሚባል መጠሪያ በመቀየሩ በዚሁ ስም ለ200 ዓመት ያህል ስትጠራ ቆይታለች፡፡ ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላም በዝዋይ ደሴት ይኖር የነበረ መነኩሴ አባት በገዳሙ ያገኘውን የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ለዐፄ ምኒልክ በማሳየቱ፣ እርሳቸውም መጽሐፉን በሊቃውንት በማስተርጐም የጥንቷን የዐፄ ዳዊትን ከተማ ፈልገው የድንግል ማርያምንና የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን ቢያሠሩና ከተማቸውን ቢመሠርቱ መንግሥታቸው እንደሚጸና እና ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ታላላቅ ታሪኮችንእንደሚሠሩ ስለተነገራቸው እርሳቸውም ይህን ከተማ እስከሚያገኙ ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ቆይተው በኋላም ከሱሉልታ ወደ ወጨጫ ሲሄዱ "የእንጦጦ ከተማ ፍርስራሽ ተገኝቷል፡፡" ተብለው ወደ እንጦጦ በመምጣት ምልክቱን በማየታቸው እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በእኛ ጊዜ ከተገለጠ ከተማውን እንደገና እንመሠርታለን በማለት የእንጦጦን ከተማ ቆርቁረዋል ዲላ ዲላ የሚባለውን ስሟን ትተውበቀድሞ ስያሜዋ እንጦጦ ብለው ጠርተዋታል (ፀሀፌ ትዕዛዝ፣ 283)፡፡

በ1870 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ የተመሠረተችው የእንጦጦ ከተማ እድገት በእጅጉ በመፋጠኑ በውስጧ የሰፈረው ሕዝብ ብዛት 50,000 ያህል ደርሶ ነበር፡፡ ለመኳንንቱ እና ለመሳፍንቱ ቋሚ የቤት መሥሪያ ቦታ በመሰጠቱከተማዋ ስትቆረቆር የነበሩት የድንኳን ቤቶች ወደ ጎጆ ቤት ተቀይረዋል፡፡ እንጦጦ በከተማነት እንድትመረጥ ካደረጓት ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ የቦታው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣በመሀል ሀገር የምትገኝ መሆኗ፣ ከፍታዋ ለጦር ዕቅድ አመቺ ሆኖ መገኘቱ እና በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ በፈዋሽነቱ ይዘወተር የነበረው የተፈጥሮ ፍል ውሃ መኖር ይጠቀሣሉ፡፡ ዐፄ ምኒልክም እንጦጦ ላይ ከተማ

ከመሠረቱ በኋላ በዙሪያው ቤተ መንግሥታቸውን፣ እንጦጦ ማርያምንና የራጉኤልን አብያተ ክርስቲያን የሚያካትት ክብ ቅርጽ ያለው ዋሻ አስቆፍረው ነበር፡፡ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳምም ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ ሲሆን ገዳሟ በተራራ፣ በሸለቆና በወንዞች የተከበበች ናት፡፡ ይህችም ገዳም በአሁኑ ጊዜ የኪዳነምሕረት እና የቅዱስ ሚካኤል ጽላቶች ይገኙበታል፡፡ አሁን ያለው ቤተክርስቲያን የተሠራው በንግሥት ዘውዲቱ ትእዛዝ ሲሆን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዐልጋ ወራሽ በነበሩበት ወቅት ከባለቤታቸው ከወ/ሮ መነን አስፋው ጋራ እየተመላለሱ ግንባታውን አስፈጽመዋል (መሪጌታ ነቅዐጥበብ የካቲት20፣2009 ዓ.ም)

የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት ገዳም ጥንታዊትና ታሪካዊት ስለመሆኗ በገዳሟ ሙዚየም ውስጥ በሚገኙት ቅርሶች የሚነገሩት ተረኮች ይመሰክራሉ፡፡ እስቲ ስለ ገዳሟ አጠቃላይ ገጽታ እንመልከት፡፡ወደ ገዳሟ ቅጥር ግቢ ከመግባታችን በፊት በተወሰነ ደረጃ ከገዳሟ ቀርቦ የሚገኘውን በተረኮች አማካኝነት ለገዳሟ መመሥረት ቀዳሚውን ስፍራ እንደሚይዝ የሚነገርለትን የጠበል ቦታ እናገኛለን፡፡ እዚህ ግቢ ስንገባ በመጀመሪያ ቀልባችንን የሚይዙት የተለያዩ ያማሩ ዕፅዋት ናቸው፡፡ ከበሩ ፊት ለፊት ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ የሚያሳይ ሥዕል በትልቁ ተሰቅሎ እናገኛለን፡፡ ግቢው ግራና ቀኝ የከበቡትን የአበባና ዕድሜ ጠገብ የጥድ፣ የዋርካ ዛፎች እያየን ድንጋይ በተነጠፈው የእግረኛ መንገድ ወደ ውስጥ ስንዘልቅ በቀኝ በኩል ወደ ውስጥ ገባ ብሎ የመጸዳጃ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል፣ የመረጃ ክፍል፣ምእመናን የሚሰጧቸው ምስክርነት የሚመዘገቡባቸው እና ሌሎች በርካታ መረጃዎችን እንደያዘ የሚነገርለትን ክፍል ዐልፈን ስንሄድ በቅርቡ የተሠሩትን የጸሎት እና የመጠመቂያ ክፍሎች እናገኛለን፡፡ የመጠመቂያዎቹ ክፍሎች በሁለት አቅጣጫ የተሠሩ ናቸው፡፡

አንደኛው በቀጥታ ወደ ጠበሉ ቅጥር ግቢ ስንገባ ፊት ለፊት ላይ የሚታየው ሲሆን ሌላው በውስጡ አራት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ይህ ክፍል አንድ ቀን ወንዶች አንድ ቀን ሴቶች በመቀያየር የሚጠመቁበት ነው፡፡ ሌላው አንድ የአባቶች፣ አንድ የሠራተኛ በሚል የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ የመጠመቂያ ክፍሎችም ተመሳሳይ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡ በእነዚህ የመጠመቂያ ክፍሎች በቀን ከዐምስት ሺህ እስከ ሀያ ሺህ ሰዎች እንደሚጠመቁ በማጥመቅ ሕይወት ሀያ ሰባት ዓመት የቆዩት አባት (ኣባ ገ/ሚካኤል መጋቢት 20፣2009) ይናገራሉ፡፡

የጠበሏን ግቢ የግራ መሥመር ይዘን ስንጓዝ የምናገኘው ምእመናኑ ጠበል ለመጠጣት የሚሰለፉበትን ከላይ በቆርቆሮ ፀሐይንና ዝናብን እንዲከላከል ተደርጎ የተሠራውን የመቆሚያ ቦታ ነው፡፡ እርሱን ስናልፍ ዐምስት መቶ ሊትር ጠበል እንደሚይዝ የተነገረን የጠበል መያዣ ገንዳ እናገኛለን፡፡ ከዚያ ከፍ ሲል በግንብ የታጠረው ጫካ፣ቅዱሳን በውስጡ እንደሚኖሩበት የሚነገረው ዋሻ ይገኛል ወደዚያም ማንም ሰው አልፎ አይገባምይህንን ተመልክተን ወደ ዋናው የገዳሚ ግቢ ለመድረስ የተወሰኑ የእግር መንገዶችን እናደርጋለን፡፡

ከጠበሉ ግቢ አንሥቶ እስከ ዋናው ግቢ ድረስ የታጠረውን የግንብ ዐጥር ስናልፍ በገዳሚ በር ላይ የተደረደሩትን የንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቆች፣ ትንንሽ የምግብ አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶችን ዐልፈን ወደ ግቢው እንዘልቃለን፡፡ከውስጥ በስተቀኝ በኩል ያለ አንድ ፎቅ እናገኛለን፡፡ በሥሩም የስለት ገንዘብ መቀበያ ክፍል፣ ሌሎች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች አሉት፡፡ እሱን ዐለፍ እንዳልን፣ የምእመናን የጸሎት ስፍራ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ይገኛል፡፡ ከፊት ለፊት የኪዳነ ምሕረትን ሥዕል የያዘች፣ በመስታወት የተሠራችውን የጸሎት ቤት፣ ከጎኗገዳሚ የምትገለገልበትን ጥንታዊ ደወል፣ ትላልቅ የጥድ ዛፎን፣ ወደ ግራም ስንመለከት በቆርቆሮ የተሠሩትን ሁለት ክፍሎች ዐልፈን የስለት መቀበያውን እናገኛለን፡፡

ከጎኑም የጸሎት ማድረጊያ፣ በደረጃ ወደ ታች ስንወርድ የወንዶች መጠለያ የሆኑትን፣እና በቀይ ሸክላ የተሠሩትን በርካታ ክፍሎች ዐይተን ስንመለስ ሰፋፊ ለምእመናኑ ለጸሎት ማድረሻ እንዲሆኑ ተብለው የተሠሩ ሰፊፊ መጠለያዎች ይታያሉ፡፡ ከጎኑም ሰፊውን የዕቃ ቤት እናገኛለን፤ ወደ አዲሱ ሕንጻ ስናልፍ በላይኛው ፎቅ ፊት ለፊት ያለው ሙዚየም ይታያል፡፡ ወደ ታች በደረጃው ስናልፍ ክርስትና ቤት፣ የተለያዩ ቢሮዎች፣ የመቃብር ቦታ እና ሌሎች በርካታ ክፍሎች በውስጡ ይገኛሉ፡፡ በዚህ በዐዲሱ ሕንጻ ላይ የሚገኘው ሙዚየም በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ችግሮች የተነሣ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን አባ ኪዳነ ማርያም በሙዚየሙ የሚገኙትን ቅርሶች ባስጎበኙኝ ወቅት ገልጸውልኛል(መጋቢት 20 2009 ዓ.ም)፡፡ ከሁሉም በላይ ወደ ገዳሚ ግቢሲገባ እጅግ ገዝፎና አምሮ የሚታየው ውብ እና ትልቁ ቤተ መቅደስ ነው፡፡ ዙሪያውንም በተለያዩ አበቦች በመከበቡ ወደ ግቢው የሚገባን ሰው ልብ ይሰርቃል፡፡

## 3.2. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት

የዐፄ አልዐሜዳ ቀዳማዊ ዘመነ መንግሥት ተስዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በአክሡም ዙሪያ የሚኖሩበት ዘመን ነበር፡፡ በዚሁ ዘመን የሮም ተወላጅ የሆኑት መንፈሳዊ አባት አባ ሊባኖስም መንነው፣ዓለምን ንቀው ከሮም ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ በኋላም በአባ ጳኩሚስ ሥርዓተ ምንኩስናን ተቀብለው በጾም እና በጸሎት ብዙ ትሩፋት እየሠሩ ኢትዮጵያ እንደቆዩ ገድላቸው ይመሰክራል፡፡ ጻድቁ አባት አባ ሊባኖስ በኤርትራና በትግራይ እየተዘዋወሩ ጠበል በማፍለቅና ተአምራት በመሥራት ብዙ ገዳማትንና አድባራትን በመጎብኘትናበማቅናት ብዙ ትሩፋት ሠርተዋል፡፡ በኋላም ደብረ ሊባኖስ ገዳምበተቀመጡበት ወቅት ይህቺ ቦታ የአንተ አይደለችም ስለተባሉ አሁን ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተብሎ ወደሚጠራው ቦታ በመምጣት በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ገዳም መሥርተውባት እንደነበር መምሬ (ልሳነ ወርቅ የካቲት 26፣2009 ዓ.ም ዲያቆን ፋንታሁን የካቲት፣26፣2009 ዓ.ም ዲያቆን ዳንኤል የካቲት 1994፣25 ዓ.ም)ይገልጻሉ፡፡

አባ ሊባኖስ በዚህች ቅድስት ቦታ እንደተቀመጡ በአንድ ዕለት በአቅራቢያቸው ያለ የሾላ ዛፍ በንብ ተከቦ ብርሃን ሲበራበት ዐዩ፡፡ በመደነቅም ተጠግተው ሲመለከቱ በሾላዋ ዛፍ ግንድ ላይ በሳንቃ የተዘጋ ክፍል ይመለከታሉ፡፡ ያንን የተዘጋውን ክፍል ከፍተው ሲመለከቱት “ዝ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት (ይህ የኪዳነ ምሕረት ታቦት)ተብሎ የተጻፈበት ጽላት ያገኛሉ፡፡ አባ ሊባኖስም ይህን በማግኘታቸው ተደስተው ለእግዚአብሔር ከፍ ያለ ምስጋና በማቅረብ፣ ለታቦቷም የሚሆን መቃኞ በመሥራት ታቦቷን አክብረዋል፡፡ አባሊባኖስ በርካታ ትሩፋቶችን እየሠሩ ብዙ ዘመን ሲቀመጡ ብዙ መናንያን ከዓለም እየመጡ በገዳሚ ተቀምጠዋል”፡፡ ከዚህም በኋላ የሣር ክዳን ያለው ቤተ ክርስቲያን በመሥራት የእመቤታችን የኪዳነ ምሕረትን ታቦት ቅዳሴ አክብረዋል፤ጠበሏንም ባርከዋል፤ ከዚህ ጋራ በማያያዝም የአንድነት ገዳም አቋቁመዋል ሲሉ (ገብረ ሚካኤል፣ የካቲት 17፣2009 ዓ.ም መሪጌታ ነቅዐጥበብ፣ አባ ኪዳነ ማርያም፣ የካቲት 26፣2009 ዓ.ም እና መርሶ ሕይወት መጽሔት) ያስረዳሉ፡፡

አባ ሊባኖስ በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ገዳሚን ካቋቋሙ በኋላ አባ ዘክርስቶስ የሚባሉ መነኩሴ ለመናንያኑ እንዲሾሙላቸው፣ እንዲህ የሚል ትንቢትም እንደተናገሩ መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ይናገራሉ፡፡[2]

*ልጆቼ ሆይ! በሉ ይህችን ቅድስት ቦታ አደራ ሰጥቻችኋለሁ፡፡ በኋላ ዘመን ታላቅ ቦታ ትሆንላችኋለች፤ አጋንንት ይወገዱባታል፤ የብዙ ቅዱሳን ዐጽም ያርፍባታል፤ ታላላቅ ነገሥታትና ጳጳሳት ይሰግዱባታል፤ ብዙ መናንያን መጠጊያ ያደርጓታል፤ ቤተ መቅደሷም በወርቅና በብር ታጌጣለች፡፡ ያንድነት ገዳም ተሻሽሎ ይቋቋምባታል፤ ብለው ተንብየው እግዚአብሔር ወዳዘዛቸው ቦታ ሄደዋል፡፡*

አባ ዘክርስቶስ ከጻድቁ ከአባ ሊባኖስ በተሰጣቸው መመሪያ ገዳሚን በመልካም ሲያስተዳድሩ እንደቆዩ ይነገራል፡፡

*በ9ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ አንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት ዮዲት የአክሱም ጽዮንን ለማቃጠል መዝመቷ በተሰማ ጊዜ ንጉሥ አንበሳ ውድም ታቦተ ጽዮንን በምስጢር አሲዞ ወደ ሸዋ በስደት መጥቶ እንደ ነበር ይተረካል (መምሬ ልሳነ ወርቅ፣ የካቲት 29፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

ይህችም ገዳም በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት ከኖረች በኋላ የተለያዩ ጻድቃን፣ የተለያዩ ነገሥታት በቦታዋ በመገኘት፣ ጠበሏንም በመጠመቅና በመጠጣት ታላቅነቷን መስክረዋል፤ የተለያዩ ስጦታዎችንም አበርክተውላታል፡፡

ይህችም ታላቅ ገዳም ስብሐተ እግዚአብሔር እየተፈጸመባት፣ በምእመናኑና በመነኮሳቱ የመንፈስ ቅዱስን በረከት እየሰጠች፣ ብዙ ተአምራት እየተፈጸሙባት ለረጅም ዘመናት ቆይታለች፡፡ አሕመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ ገዳሚ በመነኮሳቱ አማካይነት ንብረቶቿ በአጠቃላይ ተቀብረው ስለነበረ ምንም ሳያደርጋት እንደሄደ ይነገራል፡፡ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን

---

[2]ስለ አባ ሊባኖስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የተለያዩ መረጃዎች በተለያየ መንገድ ይገልጻሉ፡፡ ተሰዓቱ ቅዱሳን (9 ቅዱሳን) በመጡ በ7ኛው ዓመት በ5ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ የሚጠቁመን ዳንኤል ክብረት ትንሣኤ መጽሔትን በመጥቀሥ ነው፡፡ አባ ሊባኖስ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ የሚገልጹት መንግሥቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ ናቸው፡፡ መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ፣ አባ ኪዳነ ማርያም፣ መምህሬ ልሳኑ ከአባ ሊባኖስ ገዳሚን ከመመሥረታቸው ጋራ በተያያዘ በ6ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ይናገራሉ (ካሴት ቁጥር 1A እና 3B የካቲት 2009 ዓ.ም፣ ይህንኑ ዓ.ም ገዳሚ በሳተመቸው መርሶ ሕይወት፣ 1500 ዘመን እና የገዳሚ የልማት መጽሔት ላይ ተጠቅሦ እናገኛለን፡፡

በፊት በዚያ ቦታ ላይ አሽክላ የሚባል ወንዝ የነበረ በመሆኑ ገዳሟ አሽክላ ኪዳነ ምሕረት በመባል ስትጠራ ቆይታለች። ገዳሟም ጠፍ ሆና ለብዙ ዓመታት ከቆየች በኋላ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ገዳሟ እንደገና ተቋቁማለች። የአሁኑን የገዳሟን ቦታ ቀደም ሲል በርስትነት ይዘውት የነበሩት አቶ ኢኮ የተባሉ ገበሬ ነበሩ። በ1904 ዓ.ምእርሻ እያረሱ እያለ ያርሱበት የነበረው በሬ ያልተለመደ ባሕርይ ያሳያቸዋል፤ እርሳቸውም ግራ ገብቷቸው በሬውን ቸብ ሲሉት እንቢ ይላል፤ በኋላም ቦታ ሲቀይሩለት ያርሳል ከዚያ በሬው እንቢ ያለበትን ቦታ ሲፈነቅሉት ጸናጽል ያገኛሉ። መምሬ ልሳነ ወርቅ ሲያስረዱ፡-

> *ጸናጽሉ የተገኘው ያኔ የገዳሟ ንብረቶች አባ ዘክርስቶስ የወይራ ዛፍ ቆርጠው፣ የሰው ቁመት የሚያህል ቆፍረው፣ርብራብ በመሥራት እውስጥ በመጨመር በላዩ ላይ ሌላ ርብራብ አድርገው አፈር አልብሰውት ሲሄዱ በድንገት ይህች (አሁን) የተገኘችው ጸናጺ መረሳቷን ይመለከታሉ። በኋላም ጉድጓዱን እንደገና መክፈት አልሆነላቸውምና ለብቻዋ መሬት ቆፈር፣ ቆፈር አድርገው ቀብረዋት ይሄዳሉ። ስለዚህ ነበር ጸናጺ ብቻዋን የተገኘችው (መምሬ ልሳነ ወርቅ፣ የካቲት 7፣ 2009 ዓ.ም)።*

በኋላም ገበሬው ጸናጽሉን ወስዶ ከበረቱ ያስቀምጠዋል። ከዚያም በማያውቀው ምክንያት ቤተሰቦቹ በሕመም እየተሠቃዩበት ስለተቸገረ ማርያም ቤተክርስትያንየሚገኙትንንስሓ አባቱን ጠበል እንዲረጩለት በመጠየቅ ወደ ቤት ያመጧቸዋል። ገበሬው ይህንን ነገር አግኝቼ ነበር ብለው ጸናጽሉን ስለሰጧቸው ቄሱም በበርኖሳቸው ጠቅልለው በመውሰድ ለእቴጌ ጣይቱ አሳዩዋቸው። ጣይቱም ባገኛችሁበት ቦታ ላይ ትረፍ ብለው ስላዘዙ በገበሬው መሪነት በቦታው ጽላቷ ለሦስት ዓመታት ያህል በድንኳን ተቀምጣለች። በ1908 ዓ.ም ሥሪቷ የንፍሮ ገዳም ነበረች። እቴጌ ጣይቱ ለንፍሮና ለገዳሟ አባት መተዳደሪያከልዩ ልዩ አካባቢዎች ጋሻ መሬት ሰጥተዋል። በተጨማሪም የመገልገያ መጻሕፍትን እንደ ግንዘት፣ ስንክሳር፣ ሃይማኖተ አበው፣ ተአምረ እየሱስ የመሳሰሉትን አበርክተዋል (ስርግው 1971፡112-13)።

በ1909 ዓ.ም ሐምሌ 28 ቀን ቋሚ መቃኞ ቤት ተሠርቶ በዚያ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየች በኋላ መቃኞውአሁን ባለው ትልቅ ቤተ መቅደስ ተተክቶ ለምእመናኑ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። ዛሬ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን የተሠራው በ1923 ዓ.ም በእቴጌ መነን አማካይነት በራስ ደስታ ተቆጣጣሪነት ነው። (መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ለገሠ፣ መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም ዳንኤል ክብረት 1999፡25)።

ይህችም ገዳም ቀደም ሲል የአንድነት ገዳም ሆና የተመሠረተች ሲሆን በተለያየ ዘመን ከነበሩ ነገሥታትና መሪዎች ለመተዳደሪያ የሚሆናት ከ120 ጋሻ መሬት በላይ በስጦታ አግኝታ እንደነበር ያሉት መዛግብት ያስረዳሉ።

ከእነዚህም ስጦታዎች መሀል 80 ጋሻው ግንደ በረት ነበር። ቀሪው በአዲስ አበባና አካባቢዋ ይገኝ የነበረ ነው። ይኸውም የአሁኑ መስቀል አደባባይ ያረፈበት ቦታ ጭምር ነው። በደርግ ሥርዓት እስከተወረሱ ድረስ እነዚህ ቦታዎች በገዳሟ ይዞታ ሥር እንደነበሩ ከነዚህ ቦታዎች በገዳሟ የሚገባውን አበል ሲሰበስቡና ገዳሟን ለ45 ዓመታት ሲያገለግሉ የቆዩት(መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ለገሠ መጋቢት 4፣2009 ዓ.ም)ያስረዳሉ።

ገዳሟ በንግሥት ዘውዲቱ በምኒልክና በአቡነ ማቴዎስ ተጠንቶ ከአሸክላ ኪዳነ ምሕረት መጠሪያዋ ወደ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት መጠሪያነት ተለውጣለች። ሐመረ ኖኅ ማለት የጻድቁ የኖኅ መርከብ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደተጻፈውአባታችን ኖኅ ከጥፋት ውሀ ፍጥረታትን ያዳነበትን መርከብ ሠርቶ ነበር። ይህች ገዳምም እንደሚነገሩላት ትንቢቶች "መጀመሪያ ላይ ትጠፋለች፤ በኋላም በሐይቅ ትከበባለች። ሊጠፉ ያሉ ሕዝቦቿ ሁሉ በእርሷ ተጠልለው ይድናሉ" የሚለውን ትንቢት የያዘ እንደሆነ (አባ ኃይለ ማርያም መጋቢት 14፣2009) ዓ.ም ያስረዳሉ። እርሳቸው እንደሚገልጹት ከዚህም በተጨማሪ የዚህች ገዳም መቅደስ ጠበሏ ከፈለቀበት ቦታ ላይ የተሠራችና አንዱ ወንዝ ለሁለት ተከፍሎ በገዳሟ ዙሪያ ካለፉ በኋላ እንደገና ተመልሶ በመገናኘት የመርከብ ቅርጽ ይዞ ስለሚገኝም ጭምር ነው ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት የተባለቺው። በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ውስጥ ካሉ ታቦታት መካከል የካቲት 16 ቀን የኪዳነ ምሕረት ክብረ በዓል፣ ግንቦት 1 ቀን የልደታ ክብረ በዓል ዕለት ታቦታት ወጥተው በድምቀት ይከበራሉ። የቃና ዘገሊላ ቅዱስ ሚካኤልና ሌሎች ታቦታትም በየዕለታቸው በልዩ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይከበራሉ። ለጥምቀት በዓል ጊዜም የኪዳነ ምሕረት ታቦት በጥምቀተ ባሕሩ በመቆየት በቅዱስ ሚካኤል ዕለት ወደ መቅደስ እንደሚገባ አባቶች ያስረዳሉ።

## 3.3. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የሰንበት ትምህርት ቤት አመሠራረት

ከ1957 ዓ.ም በፊት ያለውን የሰንበት ትምህርት ቤት ታሪክ ሊነግሩ የሚችሉምንም ዐይነት መረጃዎች ባለመኖራቸው ከ1957 ዓ.ም በኋላ ያለውን የሰንበት ት/ቤት ታሪክ በዝርዝር እንመለከታለን። የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር እየተባለ የሚጠራው የሰንበት ትምህርት ቤት

የተቋቋመው በ1957 ዓ.ም በነሐሴ ወር ነው፡፡ ሰንበት ትምህርት ቤቱ የተቋቋመው በወቅቱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለ ሥልጣናት በየአድባራቱና ገዳማቱ የወጣቶች መንፈሳውያትማኅበራት እንዲቋቋሙ በማዘዛቸው እንደነበር (ዲያቆን ፊቃደማጋቢት፣4፣2009 ) ይገልጻሉ፡፡ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለ ሥልጣናት በየሁሉም አድባራት መምህሮችን ይልኩ ስለ ነበር÷ ጥበቡ የተባሉ መምህር ወደ ገዳሚ ተልከው ለበርካታ ጊዜያት ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ ያስተምሯቸው የነበሩት ወጣቶችም ቁጥራቸው ሠላሳ ይደርሱ እንደነበር ይገለጻል (ዲያቆን ፊቃደ መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም)፡፡

መንፈሳዊ ማኅበሩ በአብዛኛው ይመራ የነበረው በሴቶች በመሆኑ በርካታ ችግሮች ገጥመውት ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪበአንዳንድ አባቶች ዘንድ ሴት ቤተ መቅደስ ገብታ ልትቀድስ ነው የሚል አመለካከት በመፈጠሩ ችግሩ ተባብሶ ነበር፡፡ የእራሱ የሆነ በጀት እንኳን ያልነበረው የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርም ችግሮቹን ለመቋቋም ሲል ከአባላቱ መዋጮን በመሰብሰብ የተወሰኑ ጊዚያትን ለማሳለፍ ተገዷል፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤቱ ሲነሣዐብራ የምትነሣው ፋንቱ ወሊቃም የአባላቱ ሰብሳቢና ገንዘብ ያዥ በመሆን አገልግላለች፡፡

የዚህ መንፈሳዊ ማኅበር ዐላማ ወንጌልን መማርና ማስተማር ነበር፡፡መንፈሳዊ ማኅበሩለአካባቢው ኅብረተሰብወንጌልን በስብከትና በትያትር መልክ በማስተማር ረገድ እጅግ ታዋቂ እየሆነ መጣ፡፡ ቤተ ክህነትም ይህንን መልካም ሥራ ተመልክታ የላከቻቸው ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ወጣቶቹን ጥበቡ ከተባሉት መምህር ጋራ በመሆን እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ ሲያስተምሩ ቆይተዋል (መርሶ ሕይወት መጽሔት፣ ነሐሴ 2003 ዓ.ም)፡፡

ከ1960-1966 ዓ.ም ድረስ ሰንበት ት/ቤቱ በመምህር ዕጦት ምክንያት ተዘግቶቆይቷል፡፡ ከስድስት ዓመት በኂላም ቀድሞ ከነበሩት ሠላሳ አባላት ውስጥ ስምንት ብቻ በመገኘት ፣ ግን በፊት ያልነበረውን የመተዳደሪያ ደንብ አሁን ላይ በመቅረጽ በድጋሚ ሰንበት ት/ቤቱን ከፈቱ፡፡ እንደ ቀድሞ ሁሉ ቤተ ክህነትን ይህን መልካም ተግባር ታበረታታ ነበርና የማነእና ብርሃን የተባሉ ሁለት መምህራንን እንዲያስተምሩ ወደ ገዳሚ ላከች፡፡

የአባላቱም ቁጥር እየተበራከተ በመምጣቱ ሰንበት ት/ቤቱም በቤተ ክህነት ቃለ ዐዋዲ መሠረት ሕግና ደንብ አውጥቶ የአመራር አባላትን በመምረጥ መተዳደር እንደ ጀመረ በአሁኑ ሰዓት የሰንበት ት/ቤቱን የሚያገለግለው (ቀሲስ ብርሃኑ ኢሳይያስ መጋቢት 1፣

2009 ዓ.ም )ይገልጻል። በወቅቱ የተመረጡት አባላትም ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀ መንበር እና ጸሓፊ ነበሩ።

የአባላቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እና ንቃተ ኅሊና እያደገ በመምጣቱ በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ ካላቸው ተሳትፎ በተጨማሪ በእመቤታችን የንግሥና የጥምቀት በዓል ላይ ታቦታቱን በዝማሬዎች በማጀብ በጥምቀት በዓል ላይ የተለያዩ ነገሮችን ለሽያጭ በማቅረብ ከፍተኛ ገቢ ለቤተክርስቲያኗ ያስገቡ ነበር። ይሁን እንጂ ይላሉ ቀሲስ ብርሃኑ ኢሳይያስ በ1970 ዓ.ም እንደገና ጥቂት አባላት ውስጥ ዲያብሎስ የዘራው ክፉ ዘር በቅሎ ከቤተክርስቲያናቸው ለይቶ ወደ ምንፍቅናው ዓለም ቀላቀላቸው። በዚህም የሰንበት ትምህርት ቤቱን መረጃዎች በአጠቃላይ አጠፏቸው። በዚህም ምክንያት ሰንበት ትምህርት ቤቱ ያለ በቂ መረጃ እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል(ዲ/ንፈቃደ መጋቢት 29፣ 2009 ዓ.ም)።

ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ እንደገና በመጠናከሯና ከሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች ባላነሰ ሁኔታ የተለያዩ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመደረጉ የአባላት ቁጥር ከቀድሞ እየተሻለ ሄዷል። ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከተመሠረተበት ትንሽዬ የሸክላ ቤት ተዘዋውሮ ግቢ ውስጥ በሚገኘው ፎቅ ላይ ሥራውን እየሠራ ቢቆይም አሁን ላይ ግን የአባላቱ ቁጥር ከመጨመሩ ጋራ ተያይዞ አሁን ሰንበት ትምህርት ቤቱ ያለበትን አዳራሽ ገዳሟ በመሥራት ለአገልግሎት በመስጠቷ ለሰንበት ትምህርት ቤቱ መስፋፋት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ካሉት መርሐ ግብሮች በተጨማሪ የሕፃናትና ማእከላውያን ክፍል በማቋቋም ለወጣቶች መርሐግብር ግብአት የሚሆኑ ልጆችን ከሕፃንነታቸውጀምሮ በማስተማርና በሥነ ምግባር በማነጽ ብቁ ለማድረግ ይችል ዘንድ የእራሱን ኮሚቴ በማዋቀር እየሠራ ነው። በዚህም ምክንያት ሰንበት ትምህርት ቤቱን ሊረከቡ የቻሉ ጠንካራ አባላትን ማፍራት እንደቻለ አሁን ላይ የሰንበት ትምህርት ቤቱን በተለያዩ ደረጃዎች በመምራት ላይ ያሉ አባላት ይገልጻሉ (ዲያቆን ፈቃደ፣ መጋቢት 1፣ 2009 ዓ.ም)።

በ1970ዎቹ በሰንበት ትምህርት ቤቱ ተከሥተው የነበሩትን ችግሮች ለመርሳት በማሰብ በ1984 ዓ.ም ለሰንበት ት/ቤቱ መርሶ ሕይወት የሚል ዐዲስ ስም በመስጠት፣ መረጃዎችንም ዐዳዲስ መርሐ ግብሮችን በመቅረጽ በአግባቡ በማቀናጀት፣በወግ በመሰነድ አሁን ድረስ እየተገለገሉበት ይገኛሉ።

“መርሶ ሕይወት” ማለት “የሕይወት ወደብ” ማለት ነው፡፡ ይህም ከገዳሚ ስያሜ ጋራ ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ስያሜውን ሊሰጡ ችሏል፡፡ “ሐመረ ኖኅ” ማለት የጻድቁ አባታችን “የኖኅ መርከብ” ማለት ነው፡፡ መርከብ ደግሞ ወደብ ያስፈልጋታል፡፡ ስለዚህም ሰንበት ትምህርት ቤቱ “መርሶ ሕይወት” ተብሎ ተሰይሟል (መርሶ ሕይወት መጽሔት ነሐሴ 2003 ዓ.ም)፡፡ በ1984 ዓ.ም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ቀድመው ይሰጡ ከነበሩት የቅዳሜና እሑድ መርሐ ግብሮች (የወጣቶች፣ የሕፃናትና የማእከላውያን) በተጨማሪ በአካባቢው በሚኖሩ የጋሞ ብሔረሰብ ተወላጆች አማካይነት ተመሥርቶ የነበረውን ማኅበር ወደ ገዳሚ በማስገባት የሰኞ ጉባኤ በሚል ተቋቁሞ አገልግሎት ጀምሯል፡፡ ይህ ጉባኤ እስከ አሁን ድረስ በማኅበረሰቡ ቋንቋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ ማኅበሩ ሲመሠረት ይዞት የመጣውን መጠሪያ ለዐሥራ ስድስት ዓመት ሲገለገልበት ከቆየ በኂላ ሰኞ የሥራ ቀን በመሆኑ፣ የጉባኤው አባላትም መገኘት ባለመቻላቸው መርሐ ግብሩ ወደ እሑድ ተዛውሮ ከጠዋቱ 3፡30 እስከ ረፋዱ 6፡30 በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ስያሜውም ከቀኑ ጋራ ተያይዞ የመጣ በመሆኑ አሁን ላይ “የጋሞኛ ጉባኤ” በሚለው ስያሜ ተተክቷል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቱም የበለጠ አገልግሎቱን በማጠናከር ከ1989 ዓ.ም የቀዳማይ ኮርስ በመጀመር እስከ አሁን ድረስ ባሉት ዓመታት ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ተማሪዎችን በማስተማር ማስመረቅ ጽሑፋዊ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቱን ከ1966 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ሲመሩ ከነበሩና ካሉ ሊቀ መናብርት መካከል እንግዳ አፈወርቅ፣ ሔዋን ሀ/ገብርኤል፣ ፋናዬ መስፍን፣ ቀሲስ ብርሃኑ ኢሳይያስ፣ ሙሉጌታ በትእዛዙ፣ ወ/ሮ ጠጅቱ መና፣ ቀሲስ ሰሎሞን ገ/መድኅን፣ ዲ/ን አለማየሁ ፋንታሁን፣ አቶ መስፍን ገብሩ፣ አቶ ፈቃዱ ፋንታሁን፣ ወ/ሪት መሠረት ሳሙኤል፣ አቶ ሰሎሞን በየነ፣ ዲ/ን ጌታቸው ሜላ፣ አቶ ታጋይ ዘለቀ፣ አቶ አበራ ካፊታ እና አቶ ዐባይነህ ካፊታ ይጠቀሣሉ (መርሶ ሕይወት መጽሔት ነሐሴ 2003 ዓ.ም)፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና

### 4.1. ከእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ተረኮች ትንተና

በዚህ ጥናት በትንታኔ የሚቃኙት ቃላዊ ተረኮች ሚታዊ ገጽታን የተላበሱ፣ አንዳንዴም አፈ ታሪካዊ አተራረክን የያዙ ናቸው፡፡ በእርግጥ እነዚህ የተረክ ዐይነቶች አንዱ ባንዱ ውስጥ መገኘታቸው እና ለአንድ ወጥ ክፍፍል የተመቹ አለመሆናቸው እውን ነው፡፡ በጥናቱ አሰባሰብ ወቅት የተወሰኑ መረጃ አቀባዮች ተረኩን "ከአባቶቻችን ሲባል የሰማነው አፈ ታሪክ ነው" በሚል ሲገልጹት፣ ከፊሎቹ ደግሞ በዐይናችን ያየነው ተአምር ነው የሚሉት፡፡ ይህም ተረኮቹ ግለሰባዊ ዕውቀት ላይ የተመሠረቱ እና የግለሰባዊ ገጠመኝ ተረኮች ሊባሉ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎችም ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚጠቁም ነው፡፡ ስለዚህ ለተሰበሰቡት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ቁርጥ ያለ ዘውጋዊ ትንተና መስጠት ባይቻልም ዋና የሆኑት ንፅንስ ሐሳቦች በመምዘዝ እና የጭብጥ ትንተና በማድረግ ተረኮቹን በይዘት ከፋፍዬ አቅርቤያቸዋለሁ፡፡

ከገዳሚ የተሰበሰቡት ተረኮች በይዘት ሲከፈሉ የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ፣ የስፍራዋን ቅድስና የሚዘክሩ፣ የተአምሯን ኀያልነት የሚያሳዩ፣ ቃል ኪዳኗን እና ፈውሷን የሚዘክሩ የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡

#### 4.1.1 የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩ ተረኮች

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ከሚነገሩ በርካታ ተረኮች መካከል የገዳሚን ጥንታዊነት የሚዘክሩት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደ በርካታዎቹ የመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ የገዳሚ ታሪክ የሚጀምረው ኢየሱስ ክርስቶስ "ይህች ቦታ ያንተ አይደለች እናም ያንተ የሆነውን ቦታ ታገኛለህ" በተባሉት መሠረት ከአባ ሊባኖስ ወደ እዚህች ገዳም መምጣት ጋራ ተያይዞ ነው፡፡ በቀጣይም የምንመለከታቸው ተረኮች ከአባ ሊባኖስ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከታቦተ ጽዮን ጋራይያያዛሉ፡፡ ቀጣዩ ተረክ የሚያስረዳን የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተመሠረተው ከተክለ ሃይማኖት መወለድ በፊት እንደሆነ ነው፡፡ አብዛኞቹ የቃል አስረጂዎችም በዚህ ተረክ የሚስማሙ በሚመስል ሁኔታ ይተርኩታል፡፡ ቀጥሎ የሚቀርበውም ተረክ ይህንኑ የሚያጠናክርልን ነው፡፡

*አባ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ እያሉ ጌታ በመልአኩ ይገለጥና ይህ ቦታ ያንተ አይደለም፡፡"እዚህ ቦታ የሚቀመጥ ከፀሓይ ሰባት እጅ የሚያበራ ልጅ ይወለዳል" ሲላቸው እንዴ እኔ 7 ዓመት ሙሉ ደጅ እየጠናሁ በአቴን እንዴት አድርጌ እለቃለሁ? ቢሉ ላንተ አልተፈቀደም፤ በስምህ ግን ይጠራልሃል ስላላቸው አባ ሊባኖስ ረጅም ጉዞ አድርገው የአሁኗ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቦታ እንደደረሱ እና ገዳሟን እንደገደሟት ይነገራል (መሪጌታ ነቃዐ ጥበብ እና ሌሎች የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

ከተረኩ የምንረዳው የገዳሟ ታሪክ የሚጀምረው ተክለ ሃይማኖት ከመወለዳቸው በፊት እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም ዙሪያ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮች እና የተመለከትኳቸው መዛግብት ምላሻቸውተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም የገዳሟን ጥንታዊነት ሊያሳዩ ከሚችሉት ነገሮች መካከል አንዱ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ሌላውም ተረክ ገዳሟ በ12ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ታላቅ የነበረች መሆኗን የሚያጎለብት ነው፡፡ ይህም ተረክ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከንጉሥ ላሊበላ ጋራ በመሆን ወደ ገዳሟ መምጣታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

*በ12ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የግብጽ ተወላጅ የሆኑት ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት÷ከንጉሥ ላሊበላ ጋራዐብረው በመሆን ወደ ገዳሟ መጥተው፣ከጠበሏ ተጠምቀው፣በእንግድነት ዐድረው፣ ቦታዋንም ባርከው፣"ይህች ገዳም ከዚህም በላይ ታላቅ እና ስመጥር ትሆናለች፤ ከዚህ ወደ ታች የሚታየው ጫካ መናገሻ ከተማ ይሆናል" ብለው ተንብየዋል (ዲያቆን ፈቃደ፣ መጋቢት 7፣ 2009 ዓ.ም እና መርሶ ሕይወት መጽሔት)፡፡*

ይህ ቃላዊ ተረክ የሚነግረን የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በ12ኛው ክፍለ ዘመን እጅግ ታዋቂ እንደነበረች ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተናግረውታል የተባለውን ትንቢት ስንመለከት ጥንት እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በጫካ የተከበበች፣ ሰዎች እንደ ልብ ሊሄዱ የማይችሉባት ስፍራ እንደነበረች  መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ያለችበትን ሁኔታ በምናይበት ወቅት ትንቢቱ በእርግጥም እውነት ነው እንድንል የሚያደርገን ነው፡፡ ያ ሁሉ ጫካና ሰው የማይገባበት ስፍራ አሁን ላይ መናገሻ ከተማ ሆኗል፤ ምክንያቱም ስለ ገዳሟ የቀድሞ ሁኔታ መምሬ ልሳኑ የካቲት 5፣2009 ዓ.ም ሲናገሩ ትንቢቱ ገዳሟን አሁን ላለችበት ሁኔታ የእራሱ የሆነ ያበረከተው ነገር ሊኖረው ይችላል፡፡ ጥንት ገዳሟ አሁን ሽሮ ሜዳን ዐልፈን ለጥምቀት ታቦት ከሚወጣበት ስፍራ በኋላ

ሴቶች በፍጹም ዐያልፉም ነበር፤ ወደ ገዳሟ የሚመጡትም ሕዝቦች በአብዛኛው በጠበሏ ለመዳን በመሆኑ ብዙ ጊዜ ሲቆዩ የሚያርፉበት ቦታ ስላልነበራቸው ገዳሟ የነበራትን ጥቅጥቅ ያለ ጫካ በመቁረጥ፣ እዚያም ላይ ቤት በመሥራት ይቆዩ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሕመምተኛዎቹ ጤናቸው ሲመለስላቸው ወደየመጡበት ከመመለስ ይልቅ መኖሪያቸውን እዚያው በማድረጋቸው፣ ሕዝቡም እየተዋለደ በመሄድ፣ ቤተሰብም በመመሥረታቸው፣ እንዳይገቡ ይባል የነበረውም ነገር እየቀረ በመሄዱ ገዳሟ አሁን ያለውን ሁኔታ ለመምሰል ችላለች (መምሬ ልሳኑ የካቲት 4፣2009 ዓ.ም)፡፡

የስፍራዋን ጥንታዊነት ከሚዘክሩ ተረኮች በመጨረሻነት የምመለከተው ከታቦተ ጽዮን ወደ ገዳሟ መምጣት ጋራ ተያይዞ የሚነገረውን ነው፡፡ ይህ ተረክ ከላይ የዘረዘርናቸውን ጥንታዊነት የሚገልጹ ተረኮች በእጅጉ የሚያጎለብት ነው፡፡ ተረኩም ንጉሥ አንበሳ ውድም ከዮዲት ጉዲት (አስቴር) ሸሽቶ ወደ እዚህች ገዳም እንደመጣ የሚተርክ ነው፡፡

> *በዘጠነኛው (9ኛው) ክፍለ ዘመን ዮዲት የአክሱም ጽዮንን ቤተ መቅደስ ለማቃጠል መነሣቷ በታወቀበት ወቅት ንጉሡ አንበሳ ውድም ታቦተ ጽዮንን በምስጢር አሲይዘው ወደ ሸዋ በስደት በሄዱበት ወቅት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም እንዳረፉ እና ታቦተ ጽዮንንም በቦታዋ (በገዳሟ) አሳድረው ሲሄዱ ለገዳሟ በርካታ ስጦታዎችን እንደሰጡ ጽሑፋዊ መረጃዎችና የቃል ማስረጃዎች እንዳሉ ይነገራል (አባ ኪዳነ ማርያም፣መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም፣ መርሶ ሕይወት መጽሔት፣ ነሐሴ 2003 ዓ.ም)፡፡*

ቃላዊ ተረኮች እንደሚገልጹት ታቦተ ጽዮን በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከእስራኤል መጥታ በአክሡም ውስጥ እንደተቀመጠች ይነገራል፤በአክሡም በተቀመጠችበት ወቅትም በተለያዩ የፖለቲካ ችግሮች ምክንያት ታቦቷን ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይዘዋት እንደተሰደዱ ይተረካል፡፡ ከእነዚህ ተረኮች መካከል በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረትም ገዳም እንዳረፉ የሚነግረን፣ አንዱ ነው፡፡ ይህም ተረክ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረትን ገዳምጥንታዊነት ይነግረናል፡፡

### 4.1.2. የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች

ከእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ጋራ ተያይዘው በሚነሡ ተረኮች ውስጥ አባ ሊባኖስ በፈጣሪ ፈቃድ መሠረቷት መባሉ፣ ቅድስት ድንግል ማርያም በተአምሯ ጠበሏን

ማፍለቋ መነገሩ፣ሌላው አባ ኤልያስ በመልአኩ መሪነት በዚህች ገዳም መገኘታቸው፣ በጌታም ቃል ኪዳን እንደተገባላቸው መነገሩ፣ በመቶ ሠላሳ ሁለት ዓመታቸው በቦታው መሞታቸው፣ ሲሞቱም መቃብራቸው ስውር ሆኗል መባሉ የሚነሣ ነው፡፡

ንጉሥ አንበሳ ውድም፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታቦተ ጽዮን በገዳሚ ዐርፋ እንደነበር ተረኩ እንጦጦ ላይ ዐርፎ የነበረውን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ያጥኑ የነበሩት አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል በአፄ ዘርዐ ያቆብ ዘመነ መንግስት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ናቸው የተባሉት ካህናት በኪዳነምሕረት ጠበል መጠመቃቸው እና ቦታ መባረካቸው፣ የገዳሚን ክብር ከፍ የሚያደርግ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም በገዳሚ መገኘት እና ገዳሚን መመረቃቸው መተረኩ እና ዐፄ ምኒልክ የቦታውን ትልቅነት መመስከራቸው ይጠቀሳሉ፡፡

በመጨረሻም ንግሥት ዘውዲቱ ገዳሚ አሁን ባለው ሁኔታ እንድትሠራ ማድረጋቸው፣ እቴጌ ጣይቱ ገዳሚን እንደገና መመሥረታቸው፣ ስሟንም ከአሽካላ ኪደነ ምሕረት ወደ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት እንዲለወጥ ማድረጋቸው መነገሩ ወዘተ.በገዳማውያኑ እና በምእመናኑ ዘንድ የቦታው ክብር ከፍ ያለ መሆኑን እንዲያምኑ የሚያግዟቸው ናቸው፡፡ እምነታቸውንም ለማጠናከር እነኚህ ጻድቃን እና ነገሥታት በቦታው ተገኝተው ተናገሯቸው የተባሉት ትንቢቶች፣ሰጧቸው የተባሉት ስጦታዎች ምርቃቶች እና ተቀበሩባቸው የተባሉባቸውመቃብሮች ሁሉ በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

እነኚህ ሁሉ ድርጊቶች መፈጸማቸው የሚነገረው ገዳማውያኑ ድርጊቱን ፈጽመውታል የሚባሉትን አባላት በቀላሉ የሚያምኑ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህም ተአምሩም፣ ትንቢቱም፣ ተግሣፁም፣ ቃል ኪዳኑም፣ ሥርዓቱም ሁሉም በእነዚህ አካላት ስም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን ሐሳቦች ያጠናክሩልናል የምንላቸውን የተወሰኑ ተረኮች በቀጣይ እንመለከታለን፡፡ ተረኮቹ በገዳሚ ከታተሙ መጽሔቶቹ እና ቃለ-መጠይቆች አማካይነት የተገኙ ናቸው መምሬ ልሳኑ የነገሩኝ ተረክ ይህንን ይመስላል፡፡

ይህም የቦታዋ ክብር ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ የሚከላከል የሚመስል ነው፡፡ ከእዚህም በላይ እነዚህ ተረኮች የገዳሚን ህልውና በማስጠበቅ ረገድ ያላቸው ሚና ተራ ነገር አለመሆኑን ሊያሳዩ ስለሚችሉ ነው፡፡ በቅድስናቸው በሃይማኖቱ ውስጥ ከሚታወቁት ውስጥ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተቀምጠው፣ ከጠበሏም

ተቀብተው መሄዳቸው ይተርካል፡፡ከዚህ በተጨማሪም አባ ኤልያስ በዚህች ገዳም ዕድሜያቸውን ሙሉ እንደተቀመጡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት ከሞቱ በኋላ መቃብራቸው ስውር እንደሆነ የሚተርከው ተረክ አንዱ ነው (መጋቢ ገ/ሚካኤል መጋቢት 20፣2009 ዓ.ም)፡፡ ሌላውና ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው አባ ሊባኖስ በመልአኩ መሪነት ገዳሚን እንደ ገደሚት የሚተረከው ተረክ ነው፡፡

*አባ ሊባኖስ ለበርካታ ዘመናት ታቦቷ በሾላ ዛፍ ውስጥ ተሰውራ የቆየችበት አካባቢ በንብ ተከቦ እና ብርሃን በርቶበት በማየታቸው ጠጋ ብለው ይመለከታሉ፤ ከሾላው ዛፍ ላይም በሳንቃ የተዘጋ ክፍል ያስተውላሉ፡፡ በኋላም ያንን ሳንቃ ሲከፍቱ "ዝ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት" የሚል ጽሑፍ ያገኛሉ (መምሬ ልሳኑ፣ የካቲት 20፣ 2009 ዓ.ም፣ መርሶ ሕይወት መጽሔት)፡፡*

ከዚህ ተረክ በዋንኛነት የምንመለከተው አባ ሊባኖስ ገዳሚን የገደሙበትን እና የገለጹበትን መንገድ ነው፡፡ ለገዳሚ መገደም የኪዳነ ምሕረት ታቦት መገኘት ዋናው ነገር ነው፡፡ ይህችንም ታቦት ያገኙበትን መንገድ ስናይ በንብ ተከቦ ብርሃን ሲበራበት የሚለውን ቃል እናገኛለን፡፡ [3]

ንብ ጥሩ ነገርን የምትሰጥ የመልካም ነገር ምሳሌ ነች፡፡ ብርሃንን ስንመለከት ሰዎች የተደበቀን ነገር በብርሃን አማካይነት ያገኛሉ፡፡ ብርሃን ለሰው ልጆች ስሜት ቅርብ የሆነና ለዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያለ ነው፡፡ ምናልባትም የታቦቷ መገኘት በእነዚህ ሁለት ነገሮች አማካይነት ታጅቦ መቅረቡ÷ሁኔታው በሰዎች ስሜት ውስጥ የማይጠፋ መሆኑን ለማሳየት ታስቦ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም የፈጣሪን ጸጋ በብርሃን መስሎ ለጻድቁ አሳይቷቸው ሊሆን ይችላል፡፡

ስለ ብርሃን ስናነሣ ብዙ ጊዜ በዚህች ገዳም ቅድስት ድንግል ማርያም የብርሃን ልብሷን ለብሳ ብዙ ተአምራትን እንደፈጸመች ይነገራል፡፡ለምሳሌ ያህል የብርሃን ልብሷን ለብሳ በራእይ ጠበሉን ያፈለቀችበት፣ ዲያቆኑ ቅዳሴውን እንዲጨርስ ከፊት ለፊቱ ቆማ የመራችበት፣ የዕቃ ቤቱን ጠባቂ ያነቃችበት እና ሌሎችም ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋራ ተያይዘው የሚተረኩ ተረኮች ይጠቀሣሉ፡፡ ይህም ተረክ የገዳሚን ክብር ከፍ ለማድረግ አገልግሎት ላይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንደሚኖረው የታመነ ነው፡፡

---

[3]አባ ሊባኖስ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በኤርትራና በትግራይ በመልካ መዐዛ እየተዘዋወሩ ጠበል በማፍለቅ፣ ብዙ ተአምራት በመሥራት፣ ገዳማትንና አድባራትን በመገብኘት እና በማቅናት ብዙ ትሩፋትን ሠርተዋል፡፡

### 4.1.3. የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ ተረኮች

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ከተሰበሰቡት ተረኮች የስፍራውን ቅዱስነት የማስጠበቅ ተግባር ያላቸው ይገኛሉ፡፡ በገዳሟ ከሚተረኩትተረኮች መካከል በዚህ ሥር ይካተታሉ ያልኳቸውን የተወሰኑ ተረኮች አነሣለሁ፡፡ ተረኮቹ ንዋያተ ቅድሳትን ከገዳሟ ሰርቀው ለመውጣት የሞከሩትን ሰዎች የገጠሟቸውን ነገሮች የሚያሳይ ነው፡፡

> *በአንድ ዕለት ነው በርግጥ ሰውዬው መነኩሴ መስሎ በገዳሟ ሲንቀሳቀስ ሰንብቷል፡፡ ሁሉም ደግሞ መነኩሴ ስለመሰላቸው ያዋሩታል፤ አብረውት ይውላሉ፡፡ በኋላ ላይ ግን ወደ ዕቃ ቤት በመግባትንዋያተ ቅድሳትን፣ የወርቅ መስቀሎችን በወገቡ ደብቆ ሊወጣ ሲል÷የገዳሟ የውጪ በር አሳስወጣ ይለዋል፡፡ ይኹን እንጂ ብዙ ጊዜ እየተመላለሰ ለመውጣት ሲሞክር የተመለከቱት ሰዎች ሁኔታውን ለበላይ አካላት በማሳወቃቸው ሰውዬው ተይዞ፣ የደበቃቸውን ንዋያተ ቅድሳትም እንዲመልስ ተደርጎ ንዋያተ ቅድሳቱ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመልሰዋል፡፡ ይገርማል እኮ!ሰውዬው ወደ ገዳሟ ውስጥ ሲገባ መራመድ ይችላል፤ ሊወጣ ሲፈልግ ግን እግሩ አልራመድ እያለው ይቸገር ነበር፤ ይገርማል- የፈጣሪ ሥራ!*

*(ሊቀ ዲያቆን አበበ፣ ሚያዚያ 2፣ 2009 ዓ.ም)፡፡ ከዚሁ ተረክ ጋራ ተመሳሳይነት ያለው ሌላው ተረክ*

> *የዕቃ ቤት ጠባቂው እንደ ወትሮው የመኝታ ሰዓት በመሆኑ ተኝቷል፡፡ዕቃ ቤቱ ግን በተመሳሳይ ቁልፍ ተከፍቶ ባንድ ሰው እየተዘረፈ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጠባቂው ይሄንን አላየም፡፡ በዚህም ወቅት እርሱእንደሚለው ቅድስት ድንግል ማርያም በብርሃን ልብሷ ተገልጣ ትከሻውን እየነካካች ተነሥ! ተነሥስ! ስትለው እንደነቃ እና ወደ ዕቃ ቤቱ ሲያመራ የዘረፈው ሰው ለመሄድ ሲል የዕቃ ቤት ጠባቂው ስለደረሰበት የሰበሰባቸውን ንዋያተ ቅድሳናት ትቶ መሮጡ ይነገራል፣ (መምሬ ልሳኑ ሚያዚያ 2፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

የተረኮቹን ተግባር ስንመለከት ገዳሟን የሚዳፈር አልያም በየትኛውም መንገድ ቢሆን ንዋያተ ቅድሳትን ለመስረቅ የሚያስብ ሰው ቢኖር በጭራሽ እንደማይሳካለት ለመንገር የታሰበ የሚመስል ነው፡፡ የመጀመሪያው ተረክ ላይ ሰውዬው ምንም እንኳን መነኩሴ መስሎ በገዳሟ ተገኝቶ እና ተመሳስሎ ይህንን ነገር ቢፈጽምም በገዳሟ ውስጥ ያሉት ገዳሟንየሚጠብቋት አካላት ብቻ ሳይሆኑ ፈጣሪም ከላይ ሆኖ የሚጠብቅ መሆኑን ለማሳየት የተነገረይዘትየተላበሰ

ይመስላል። በሁለተኛነት የተመለከትነውም ተረክ እንዲሁ ምንም እንኳን ጠባቂው ኃይለኛ ዕንቅልፍ ጥሎት የንብረቱን መዘረፍ ለማየት ባይችልም በቅድስት ድንግል ማርያምእርዳታ ንብረቱ ሊተርፍ መቻሉን የሚያሳየን ነው። የሰውዬው ከፉኛ እንቅልፍ ላይ ሆኖ ንብረቱን መጠበቅ አለመቻሉም ምናልባት ሰዎች እንዲህ ዝንጉ ከሆኑ አንዳንድ ነገሮችን በራሳቸው ማዳን ሊያቅታቸው እንደሚችል ያሳያል። ስለዚህም ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሌም ንቁ ሆነን መጠበቅ እንዳለብን ሊያስተምሩ ተብለው የተነገሩም ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ልንወስድ እንችላለን። ሌላው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብርሃን ልብሷ ተገልጣ በሰውዬው ትከሻ ላይ እጇን ስታሳርፍ የሚለውን ሐሳብ ስንወስድ ሰዎች የሰዎችን ትከሻ ሲነኩ የሚያሳየው የቅርብ መሆናቸውን እና የአለሁልህ ስሜትን መፍጠሪያም ነው፤ አልያም አልነቃ ያለን ሰው የሚያነቁበት መንገድም ነው። ስለዚህም ይህ ተረክ እነዚህን ሁለት ሐሳቦች መሠረት አድርጎ የተተረከ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ሌላው በብርሃን ልብሷ የሚለው መገለጹ ምናልባትም "ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም የዮሐንስን ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው፤ በፊታቸውም ተለወጠ፤ ፊቱም እንደ ፀሓይ በራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋራ ሲነጋገሩ ታያቸው /ማቴ፡17፡1-3/ የሚለውን በማሰብ ሊሆን ይችላል።

> *ጢሞቴዎስ እጅ በመጫን መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደተቀበለ እናውቃለን። ቅዱስ ጳውሎስ "በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋራ የተሰጠህን በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል" ሲል ያስታውሰዋል (2 ጢሞ. 14፡18)።*

ይህንን ጥቅሥ ስንመለከት  ቅድስት ድንግል ማርያም በሰውዬው ላይ  አደረገች ተብሎ የተነገረውን ተረክ ስናይ አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር እንዳለ እንረዳለን። ይኸውም ድንግል ማርያም ያላትን መንፈሳዊ በረከት በሰውዬው (በዕቃቤት ጠባቂው) ላይ በማሳደር ንብረቱን ማትረፍ እንዲችል አድርጋዋለች የሚለው ሲሆን ሌላው ያሉንን መንፈሳውያት ስጦታዎች ለሌሎች ማካፈላችን መልካም ነገር ይፈጥራል የሚል ነው።

ሌላው ደግሞ ዕንቅልፍ በሽታ ነው የሚለውን የተለመደ አነጋገር የተከተለ ይመስላል፤ ምክንያቱም (በማር. 16፡13) እና (ያዕ 5፡13-16) ላይ እጅ በመጫን ሰዎች ከበሽታ እንደሚፈወሱ ተስፋ ተሰጥቶአል። የቅድስት ድንግል ማርያም በሰውዬው ላይ እጇን መጫኗ ሰውዬውን ከያዘው የዕንቅልፍ በሽታም አዳነችው የሚለውን ለመንገር በማሰብ የተተረከ ሊሆን ይችላል።

### 4.1.4. የገዳሚን ቅድስና የሚዘክሩ ትንቢት ነክ ተረኮች

በሃይማኖት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የልዕለ ተፈጥሮ በረከት ዐደረበት ተብሎ መታመን ለስፍራው መቀደስ እንደ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ስፍራ የተቀደሰ ነው ሲባል መላእክት የነበሩበት፣ ቅዱሳን የተወለዱበት፣ የጸለዩበት፣ ያረፉበት፣ስማዕታት ዋጋ የከፈሉበት፣ ድንቅ የሆኑ ተአምራት የተፈጸሙበት እና ሌሎችም ድርጊቶች የተከናወኑበት ሲሆን ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ የሃይማኖቱ ተከታዮች የሃይማኖቱን ዶግማ ለመፈጸም፣ ነፍስን ለማስደሰትና የሥጋን በረከት ለመቀበል ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ እኒህን ሁሉ ነገሮች ለማጉላትና ለመዘከር ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት የሚተረኩት ተረኮች ናቸው፡፡

ተረኮች በተለያዩ የመባያ ጉዳዮች የስፍራውን ቅድስና ይሰብካሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች እንደሚናገሩት ከቅዱሳን አበው በተጨማሪ የተለያዩ ነገሥታት ወደ ስፍራው እንደመጡ፣ ከሕመማቸው እንደ ዳ፣ ትንቢት እንደተናገሩ ለምሳሌ ንጉስ አንበሳ ውድስ፣ ንጉሥ ላሊበላ፣ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ ዐፄ ልብነ ድንግል፣ ዐፄ ሚናስ፣ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ፣ ዐፄ ምኒልክ፣ እቴጌ ጣይቱ፣ ንግሥት ዘውዲቱ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን መዘርዘሬ ያለ ምክንያት አጥደለም "ይልቁንም ስለ ገዳሚ ቅድስና የተተረኩትን ተረኮች ስናነሣ ዐብረው የሚነሡ ጉዳዮች በመሆናቸው እንጂ፡፡ ለዚህም ማሳያ እንዲሆን ወደፊት በትንቢት መልክ ቦታዋ ምን ያህል ቅድስት እንደምትሆን የተናገሩ፣ በቆሙበት ዘመንም ቢሆን የስፍራዋን ቅድስና የመሰከሩ ለእውነተኛ ቅድስትነቷም ያላቸውን ሁሉ በስጦታ ያበረከቱ በርካቶች ምእመናን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህንንም ጉዳይ ያጠናክሩልኛል ያልኳቸውን ትንቢቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ትንቢት በራሱ ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሣ ስለሚችል የተለያዩ ምንጮችን በመውሰድ ምላሽ ሰጥቼ ወደ ተረኮቹ እመለሳለሁ፡፡

ቀጥሎ ትንቢትን በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሥርቼ÷ አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሣት እሞክራለሁ፡፡ ትንቢት ማለት በሐዲስ ኪዳን በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚመጣን መልእክት ለተሰበሰቡት ማኅበረ ምእመናን መናገር ማለት ነው፡፡ ትንቢት ብዙውንጊዜ ከቤተክርስቲያን አባሎች አንዱ በቤተክርስቲያን ውስጥ በተመሥጦ በተቀመጠ ጊዜ የሚመጣለትና በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት የሚናገረው ዐጭር መልእክት ነው፡፡ ስለዚህ ትንቢት ያለ ሰው ሐሳብ ወይም ጥናት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የመንፈስ ስጦታ ነው ልንል እንችላለን፡፡

ቅዱስ ጳውሎስስለ ትንቢት ስጦታ ይናገራል፡፡ ነቢዩ የሚናገረውን ሰዎች ይውቁታል፡፡ነቢይ አንድን ነገር ዝም ብሎ አይተነብይም፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደ ተጻፉት ትንቢቶች የቤተክርስቲያንን ተጨባጭ ችግር የሚመለከት ነገር ነው የሚናገረው፡፡ "ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል" (1ኛ ቆሮ.14፡34)፡፡ ትንቢት የሚሰጠው ከፍተኛ ጥቅም ቤተክርስቲያን ለማነጽ ነው፡፡ ቅዱሳን በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የሚናገሯቸውን (የተናገሯቸውን) ትንቢቶች ገዳሚ አሁን ያለችበትን፣ወደፊት የምትሆነውን ዐልፎ ተርፎ በፊት የነበራትን ሁኔታ ለመግለጽ ተጠቅመውባቸው እንመለከታለን፡፡ በዚህም የእምነቱ ተከታዮች በዚህ ትንቢት አማካይነት ይታነጻሉ፤ ይመከራሉ፤በእምነቱም እንዲጸኑ ይደረጋሉ፡፡

በዚህች ገዳም ትንቢት እንደተናገሩ ከሚጠቀሡቅዱሳን መካከል አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ አንዱ ናቸው፡፡ እርሳቸውም ለነበሩት መነኮሳትና ለንጉሥ ላሊበላ "ከዚህች ወደ ታች የሚታየው ጫካ መናገሻ ከተማ ይሆናል" ብለው ተንብየዋል፡፡አባ ሊባኖስ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረትን ገዳም ካቋቋሙና ካደራጁ በኋላ አባ ዘክርስቶስን በሾሙበት ወቅት አንድ ትንቢት ተናግረው እንደነበር ይተረካል መምሬ ተዘራ ይገልጻሉ፡፡

> *ልጆቼ ሆይ! በሉ! ይህችን ቅድስት ቦታ አደራ ሰጥቻችኋለሁ፡፡ በኋላ ዘመን ታላቅ ቦታ ትሆናለች፤ አጋንንት ይወገዱባታል፤ የብዙ ቅዱሳን ዐጽምያርፍባታል፤ ነገሥታትና ጳጳሳት ያርፉባታል፤ ብዙ መናንያን መጠሪያ ያደርጓታል፡፡ ቤተ መቅደሷም በብርና በወርቅ አጊጣ ትታነጻለች፤ የአንድነት ገዳም ተሻሽሎ ይቋቋምባታል" (መምሬ ተዘራ፣መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም እና መርሶ ሕይወት መጽሔት)፡፡*

ሌላው ትንቢታዊ ተረክ የላይኛውን ሐሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በሥራ ጉዳይ ወደዚች ገዳም በመጡበት ወቅት የገዳሚን አቀማመጥ እና የጠበሏን ፈዋሽነት ተመልክተው በማድነቅ "ዳሯ እሳት መሀሏ ገነት ትሁን" ብለው ብዙ ማደሪያ እንደሰጡ ይነገራል፡፡ ከ40 ዓመት በላይ በገዳሚ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ያገለገሉት አባት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የእኅታቸውን ልጅ ጻድቁን አባ ኤልያስን አግኝተው ከተጨዋወቱ በኋላ የሃይማኖት አባት፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ሐዋርያ ሆነህ፣ ተሾመህ እንድታስተምር ወደ ደብረ ብርሃን ልውሰድህ ባሏቸው ወቅት ጻድቁ "ሕይወቴ ብሕትውና ነውና አልሄድም አሏቸው"፡፡ ንጉሡ ግን አይሆንም" በማለታቸው መልአከ እግዚአብሔር በክንፉ ወስዶ መናገሻ ማርያምእንደሰወራቸው ፣ንጉሡም ሊወስዷቸው እንዳልቻሉ ዐውቀው ወደ ከተማ እንደተመለሱ

ይነገራል፡፡በኋላም የቦታዋ ቅድስና ኀያል ነውና ጻድቁ በመልአኩ መሪነት ወደ ገዳሚ ተመልሰው ብዙ ትሩፋትሠርተዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ገዳሚን ባርኮ÷

> *"ወዳጄ ኤልያስ ሆይ! ስምህን ጠርቶ ለጸሎት በቆምክበት በዚህች ቦታ የሚጸልየውን ፣ዝክርህን የሚዘክረውን፣የቆምክበትን መሬት የሚረግጠውን ዐስራት ሰጥቼሃለሁ፤ እንደ ወዳጄ ነቢዩ ኤልያስም ክብርህን አበዛዋለሁ፤ይህችንም ቦታ ጠለ ምሕረቴ አይለያትም፡፡ ብዙ አስደናቂ ተአምር እንዲሠራባትም አደርጋለሁ፡፡ ገዳሚንም ታላቅ እና ስመጥር ካደረካት በኋላ በዚህች ገዳም እንደ ሙሴ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ መላእክት ይቀብሩሃል መቃብርህም ስውር አደርግልሀለሁ ሲል ቃል ኪዳን መግባቱ ይነገራል(መምሬ ተዘራ፣ መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

ከታሪኩ የምንረዳው ለእነ ነቢዩ ኤልያስ፣ ለእነ ሙሴ የተሰጠው ክብር ለጻድቁ ለኤልያስም እንደሚሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን እንደገባላቸው ነው፡፡ የትንቢቱ አቀራረብ የእኒህን ክርስቶስ የፈጸማቸውን ሁነቶች ዐስበው፣ አንድም የገዳሙን ከፍታ፣ አንድም በጻድቃኑ ክብር ገዳሚ በቃል ኪዳን መታሰሯን ተገንዝበው እንዲድኑ የማድረግ ሚናን የተሸከመ የሚመስል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገዳሚ ልቃ እንድትታይ የማድረግን ተግባር የተከተለ ተረክ ነው ማለትም ይቻላል፡፡

የገዳሚን ትንቢታዊ ተረኮች በአብዛኛው የሚተርኩት ከሃይማኖቱ ቅዱሳን እና ነገሥታት ጋራ በማያያዝ ነው፡፡ በእነዚህም አካላት ወደፊት ገዳሚ የምትመስለው ይህን ነው፤ የምትተዳደረውም በዚህ መንገድ ነው፡፡ በውስጧ የሚገኙትም አሁን ላይ ካሉት መነኮሳይያት በተለየ የበቁት አባቶች ብቻናቸው በሚል የሚነገሩ ትንቢታዊ ተረኮችን እናገኛለን፡፡ አሁን ላይ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የንፍሮ ገዳምነቷን በማጣቷመነኮሳይያቱ በእየራሳቸው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ብቻ እንመለከታለን፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ገዳሚ ጠፍ ሆና ስትመለስ ቀድሞ የነበራትን በጀት በማጣቷ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ከዚህም ጋራ ተያይዞ እቴጌ ጣይቱ ገዳሚን የንፍሮ ገዳም አድርገዋት የነበረ መሆኑን፣ምኞታቸውም ይህ እንደነበር፣ ወደ ኋላም አሁን ያለው ነገር ተቀይሮ ወደ ቀድሞው እንደምትመለስ የሚናገሩ ትንቢታዊ ተረኮች ይተረካሉ፡፡ በሌላ በኩል ይህቺ ገዳም ወደ ፊት በሐይቅ እንደምትከበብ ፍጹማንብቻ የሚኖሩባት እንደምትሆን ይተረካል፡፡ እንዲያውም አካባቢው አሁን ላይ ምልክት እያሳየ ነው፡፡ ወደ ጫካው ያሉ ቤቶች እየተሸረሸሩና ውሃ እየፈለቀ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ይናገራሉ፡፡ እኔም ብሆን በቦታው ተገኝቼ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህች

ገዳም ለገዳማውያኑም ብቻ ሳይሆን ለኅብረተሰቡም ኀያልነቷን፣ ጥንታዊነቷን፣ ክብሯን የምትገልጽባቸውን ተረኮች በሰፊው የምትገለገል ናት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቿ እውነትነት ሊኖራቸው ይችላል እንድንል የሚያስችሉን ክስተቶች እንመለከታለን ይህም በሐይቅ ለመከበብ መንገድ ላይ መሆኗ፣ የጥንቱ የገዳሚ ስፍራ መናገሻ ከተማ ለመሆን መብቃቱ፣ ገዳሚ በብርና በወርቅ እየተለበጠች አሁን ላይ መገኘቷ የሚሉት እና በሌሎችም የተረክ ትንታኔ ክፍሎች ውስጥ የተጠቀሡት ተረኮች ይመሰክራሉ፡፡

### 4.1.5. ከተአምር ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

*"መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ፤*

*መልካሙን ያዙ፤ ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ" (1ኛ ተሰ. 5፡19-20)፡፡*

መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጠው ታላላቅ አገልግሎቶች መካከል ለወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር ለፃድቃን በራእይ ለቤተክርስቲያን መግለጽ ነው፡፡ በብዙ መንገድ የሕይወታችን መከናወንም ሆነ ህልውናችን ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው መገለጽ ላይ ይደገፋል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻዎቹ ዘመናት ሁኔታ ከኖኅ ዘመን ሁኔታ ጋራ ተመሳሳይነት እንደሚኖረው ተናግሯል (ሉቃ 17፡26-27)፡፡ ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተሰቦቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፣ በዚህም ዓለምን ኮነነ፣በእምነት የሚገኘውን ጽድቅ በፈጣሪ ተአምር ወራሽ ሆነ" (ዕብ 11፡7)፣በማለት ይገልጻል፡፡ ተአምራት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ (ዮሐ 9፡1)፡፡ (ዘፍ 1፡2)፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውሀዎች ላይ መንሳፈፉ"፡፡ (ዘፍ 1፡2)፣ ንእማን በዮርዳኖስ ተጠምቆ ከነበረበት ለምጽ መዳ (1ነገ፡6)፣ በቤተ ሳይዳ የእግዚአብሔር መልአክ ውሀውን ሲያናውጠው ቀድሞ የገባ ይፈወስ የነበረ መሆኑ (ዮሐ፡5)፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ማየት ተስኖት የነበረውን ሰው በሰሊሆም መጠመቂያ እንዲጠመቅ ማዘዙ (ዮሐ 9፡1) እና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች በጠበል የሚገኘውን ፈውስ ይመሰክራሉ፡፡ በሃይማኖታዊ ተረኮች የቦታውን ስብእና ለማላቅ ከሚጠቀሙባቸው እጅግ የተለመዱ የመባያ ጉዳዮች መሀል ተአምራት እና ፈውስ ይገኙበታል፡፡ ተአምራት እና ፈውስ የቦታውን ቅድስና እና መንፈሳዊ ብቃት የሚያረጋግጡ ከመሆናቸው ባሻገር ፈጣሪ ለቅዱሱ ቦታ ሲል በየሁነቶቹ ጣልቃ እየገባ ፈውስ እና ተአምራት ይገኙበታል፡፡ ተአምራት እና ፈውስ

የቦታውን ቅድስና እና መንፈሳዊ ብቃት የሚያረጋግጡ ከመሆናቸው ባሻገር ፈጣሪ ለቅዱሱ ቦታ ሲል በየሁነቶቹ ጣልቃ እየገባ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ፈውስ እና ተአምራት በተፈጸሙባቸው ጊዜያት ወይም ሲከወኑ የገዳሟን ማንነት፣ ተራዳኢነት፣ ችሮታ ወዘተ ከማስታወቅ አንጻር ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ ይኸም ይሁነኝ ተብሎ ብቻ የሚደረግ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን የፈጣሪ ቸርነት ታክሎበት ነው፡፡ ቀጥሎ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተፈጸሙትን ተአምራት እና ፈውሶች ነጣጥለን እናያለን፡፡

**ተአምራት፡-** “ክርስቶስ በክፉው ላይ ሥልጣን አለው፡፡ የባሕር ማዕበል የሚታዘዝለትን እርሱን ብታምነው ጌታህ ነው” (ማቴ.8፥27) እንዳለው ሁሉ÷ተአምራት በተለያዩ የእምነት ቦታዎች ሁሉ የሚታዩ እንዲሁም ለቅዱሳኑ የተቸረ ትልቅ ጥበባት እናለምእመናኑ የተሰጡ ያስተምሮ ብልኀቶች ናቸው፡፡ በገዳሟ ውስጥ ብዙ ተአምራት ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል አዎንታዊነትን አሉታዊነትን የተላበሱ ተአምራትይገኙባቸዋል፡፡

**አዎንታዊ ተአምራት፡-** ለመልካምና ለበጎ የተደረገንተአምር ሲወክል ቅዱሱ የተነሣበትን እና የሚያቀነቅነውን ሃይማኖታዊ ግዳጅ ተቀብሎ ተከታዮችን፣ አማኞችን ለማዳን፣ ለበሽተኞች ፈውስ ለመስጠት እና የተለያዩ በጎ ተግባራትን ለመፈጸም ወደእራሳቸው የሚጠሩበትን መንገድ ይወክላል፡፡ አዎንታዊ ተአምራትን ሰማያዊና ምድራዊ በማለት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

**ሰማያዊ ተአምር፡-** ከፈጣሪ ጋራ በተለያየ መንገድ ቅዱሳኑ ሲገናኙ የሚታይበት፣ የረቀቁና ለማመን የሚያዳግቱ ክሥተቶችን በውስጡ ዐቅፎ የያዘ ክፍል ነው፡፡

ለዚህም አንድ ምሳሌ ወስደን እንመልከት፡፡ ይህ ተረክ አባ ሊባኖስ ወደዚህች ገዳም እንዴት እንደመጡ ነበር፡፡

> *አባ ሊባኖስ ወደዚህች ገዳም ሲመጡ ባለ ወይባ 1000፣ ባለ ማቅ 1000፣ ባለ ደበሎ 1000 በአጠቃላይ 3000 ቅዱሳን አጅበዋቸው ነበር የመጡት፡፡ የተክለ ሃይማኖት መወለድ ራዕይ ተነግሯቸው ሲሄዱ 1000ዎቹ ቅዱሳን አጅበዋቸው እንደሄዱ ይነገራል (መምሬ ልሳነ ወርቅ መጋቢት 2009 ዓ.ም)፡፡*

ሌላኛውም ተረክ እንዲሁ ስለ ተአምር የሚተርክ ነው፡፡

*ኀይለ ሥላሴ አንድ ባህታዊን ወደ ኢየሩሳሌም ይዤህ ልሂድ ይሏቸዋል አይ ያንተ ቆርቆሮ ይጥለኛል የእኔ (በኢትዮጵያ) ፈረስ ይሻለኛል ይሏቸዋል (ፈረስ መልዐክ ነው) ከዛም በመንፈስ ቅዱስ ቀድመው እየሩሳሌም እንደደረሱና ዳዊት ይደግማሉ፡፡ ጃንሆይም ከአየር ወርደው ሲደርሱ ያገኟቸዋል ይደነግጣሉ በኋላም ሊመለሱ ሲሉ አሁንስ ይዤህ አልሄድም ቢሏቸው አይታክትህም እንዴ ብለው አሏቸው፡፡ (መምሬ ልሳነ ወርቅ ካሴት ቁጥር 4B መጋቢት 2009 ዓ.ም)፡፡*

**ምድራዊ ተአምር፡-** ምድራዊ ተአምራት ብዙ ጊዜ ከሚኖሩበት ማኅበረሰብ መልክአ ምድራዊ ሁኔታ ጋራ ይቆራኛል፡፡ መፈወስን፣ ማብላን፣ ማጠጣትን፣ ለአካባቢ የሚበጁ፣ ሰዎችን የሚረዱ ተረኮች መከሠትን ይመለከታል፡፡ በገዳሚ በዚህ ዘርፍ የሚነሡ በርካታ ተአምራትተፈጽመዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በቅድስት ድንግል ማርያም አማካይነት ጠበል የፈለቀበት፣ ጣሊያናዊው ጣቱን ያጣበት፣ ሌባው መጥቶ ሳይሰርቅ የሄደበት፣ የገበሬው ጎተራ ሞልቶ የተገኘበት የሚሉ በርካታ ተአምራትን እናገኛለን፡፡

በዚህ ስር የምናገኘው ተረክ እቴጌ ጣይቱ በገዳሚ አካባቢ በሚጓዙበት ወቅት የተደረገላቸውን ተአምር የሚተርክ ነው፡፡

*እቴጌ ጣይቱ በአንድ እለት ከአሽከሮቻቸው ጋራ በበቅሎ ሆነው ሲሄዱ ቦታው አሁን ሸቦ ግቢ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነው በጣም እረግረግ ስለነበር ከበቅሎ ወርደው በገረዶቻቸው እረዳትነት በእግራቸው በሚጓዙበት ወቅት እግራቸው ላይ ትርፍ ጣት ሆና ዘወትር ታማቸው የነበረችው ጣታቸው መቆረጧ እና ከህመማቸው መዳናቸውን በማየታቸው ጠበሏን እግረግጬ ነው የዳንኩት በማለት ግብር ጥለው ሰንጋ አርደው ካህናቱን አብልተዋል፡፡ በአካባቢው ያለው ውሃ ሰዎች አሁን የተለያዩ ግልጋሎት ይጠቀሙባቸዋል እንጂ ጠበል ነው (መምሬ ልሳነ ወርቅ መጋቢት 6፣2009 ዓ.ም)፡፡*

ቀጣዩም ተረክ በተመሳሳይነት የቆመ ነው፡፡

*ዲያቆን በሚያስቀድስበት ጊዜ ኀደኛውን በሚያይበት ጊዜ ቅዳሴውን በመርሳቱ የያዘው መስቀል ከግድግዳ አጣብቀው ከዚያም ከፍተኛ ጸሎት ተደርጎለት*

*ከተላቀቀ በኋላ መነኮሳት እንዲቀድሱ ሆነው ቅዳሴው አበቃ ከዚያ በኋላ ግን ይህ ዲያቆን ቀራኒዮ የሚባል ቦታ ሄዶ ጫካ ውስጥ እራሱን እንዳጠፉ ይነገራል (መምሬ ልሳነ ወርቅ ካሴት ቁጥር 4A መጋቢት 2009 ዓ.ም)፡፡*

**አሉታዊ ተአምራት፡-** በዚህ ክፍል የሚነሣው የተአምራት ዐይነት ብዙ ጊዜ እነዚህ ቅዱሳን በተፈጥሮ ለሰው ልጆች ዘብነት፣ ለመምህርነት፣ ለጠባቂነት፣ ለምልጃ፣ለጸሎት የሚተጉ ቢሆኑም ቅሉ የዚህ ዕሳቤ ተቃራኒ እና በእነሱ ዕሳቤ የሰይጣን መንፈስ ያደረባቸው የእነሱ ተቃራኒ በገጠማቸው ጊዜ የሚሠሯቸው አሉታዊ ተአምራት ናቸው፡፡ ይህንንም ተአምር በቁጣ መልክ የተነገሩ ተረኮች በሚለው ሥር በማካተት በዝርዝር እመለከታለሁ፡፡

በዚህም ጥናት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በተአምር መልክ የተተረኩትን ተረኮች ስንመለከት ተአምራቱ በተለያዩ መንገዶች እንደሚገለጹ እንረዳለን፡፡ ከዚህም መካከል በቁጣ መልክ፣ በመግለጽ እና በፈውስወዘተ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

### 4.1.5.1. በቁጣ (በራእይ) መልክ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

ቁጣ ልዕለ ተፈጥሮን ወይም ነገረ መለኮታዊ ብሂልን ከመቃረን ሊመነጭ ይችላል፡፡ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በርካታ ተአምራት እንደተፈጸሙ ተጠቅሟል፡፡ በቁጣ መልክ ከሚጠቀሡት መካከል ለአብነት ያክል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ እነዚህ ሦስት ተረኮች ከአባ ኪዳነ ማርያምና በገዳሟ ከሚገኙ መዛግብት ላይ የተገኙ ናቸው፡፡

*ይኼኛው ተረክ በገዳሙ አካባቢ የልማት ሥራን ሊሠሩ የመጡ ጣልያኖች በኪዳነ ምሕረት ዕለት ሲሠሩ ምእመናኑ ተው ቢሏቸውም ሥራቸውን በመቀጠላቸው ሥራውን ይሠሩ ከነበሩት መካከል አንዱ በድንገት መሞቱ ተተርኳል (አባ ኪዳነ ማርያም፣የካቲት 22/ 2009 ዓ.ም)፡፡*

*ሌላኛው ተረክ እንዲሁ ጣልያኖች ወደ ገዳሟ በመግባት እና ከቤተክርስቲያኗ ጫፍ ላይ ምፍ ዐርፋ በማየታቸው አንደኛው ይህችን ወፍ እገድላለሁ ብሎ በመተኮሱ አንድ ጣቱ ተቆርጣ መሬት ላይ መውደቋ ወፏም ምንም አለመሆኗ ይነገራል (አባ ኪዳነ ማርያም፣ የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

በተመሳሳይም ቅዱሳን ይኖሩበታል ተብሎ የሚታመነውን ዋሻ የአካባቢው ወጣቶች ጣልያን ወርቅ ደብቆበታል ብለው በተለያዩ መሣሪያዎች ሊያፈርሱ ሲሞክሩ ያመጧቸው መሣሪያዎች

እንደተበላሹባቸው፣ ከመሀላቸውም አንደኛው ሰውዬ አደጋ እንደደረሰበት ይጠቀሣል (አባ ኪዳነ ማርያም፣የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)፡፡

ተረኮቹ የኪዳነ ምሕረትን ተአምር ሠሪነት የሚዘክሩ ሲሆኑ በሌላም አቅጣጫ ስንመለከት የተቀደሱ ናቸው ተብለው በሚታመኑ ስፍራዎች ላይ ሕገጋትን መተላለፍ የሚያስከትለው ነገር እንደሚኖር እንዲሁም ለቅጣት እንደሚዳርግ የሚሰብክ ነው፡፡ በተረክ ዐሥራ አራት የተመለከትነው ደግሞ ፈጣሪ እርሱን ላመኑ ሁሉ ዘብ እንደሚቆም፣ ከተለያዩ ነገሮች እንደሚጠብቅ ሊያጠቁን እደጃችን ድረስ ቢመጡ እንኳን እንደሚያድነን የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚሁ ጋራ ተያይዞ የሚነሣው ተረክ ለእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በአሕመድኢብን ኢብራሂም ዘመን ተሰውራ ብዙ ዘመናትን ካስቆጠረች በኋላ በአካባቢው ገበሬ አማካይነት ከተቀበሩት ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጸናጽል ካገኙት ገበሬ ጋራ ተያይዞ የሚነገረው ተረክ ይጠቀሣል፡፡ እንደ አባ ኪዳነ ማርያም ገለጻ ተረኩ ይህንን በሚመስል ሁኔታ ቀርቧል፡፡

> *ይህቺ ገዳም ክርስትናን ለማጥፋት በተነሣው በአሕመድ ኢብን ኢብራሂምዘመን ምክንያት ተደርምሳ ስለነበር አሕመድ ኢብን ኢብራሂምሳያያት ነው ያለፈው፡፡ በኋላም ጠፍ ሆና ከቆየች በኋላ በገበሬው አማካኝነት  በተገኘችበት ወቅት ገበሬው ወደ ቤቱ ወስዶ በበረት ካስቀመጠው በኋላ የቤተሰቦቹ ጤና ሁሉ እየታወከ በበሽታ ስለተጠቁበት የክርስትና አባቱን ከእንጦጦ ማርያም አስጠርቶ ቤቱን እንዲረጩለት አደረገ፡፡ በኋላም ክርስትና አባቱ ሊወጡ ሲሉ አንድ ነገር ሣርስ ውስጥ አግኝቼ ከበረት አድርጌዋለሁ፡፡ የእናንተ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አሳያቸው፡፡ እርሳቸውም በበርኖስ ጠቅልለው ወደ እንጦጦ ማርያም ወሰዱት (አባ ኪዳነ ማርያም የካቲት፣20 2009 ዓ.ም)፡፡*

ከዚህ ተረክ መምዘዝ የፈለግነው በቁጣ መልክ የሚለውን ሐሳብ ሊያጠናክርልን የሚችለውን የተረክ አካል ነው፡፡ ይኼውም አንደኛው ቤተሰቦቹ ሁሉ ከዚህ በፊት ይዟቸው በማያውቁት በሽታ መጠቃታቸው ነው፡፡ የላይ፣ የላይ ትርጓሜውን ስንመለከት ሰዎች በድንገት ሊታመሙ ይችላሉ፤ ከሕመማቸውም ለመዳን ዘመናዊውን፣ ሃይማኖታዊውን የመዳኛ መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ ተረኩም ሰውዬው ቤተሰቦቹ ከሕመማቸው ይድኑለት ዘንድ ሃይማኖታዊውን የመዳኛ መንገድ በመጠቀም ጠበል ማስረጨታቸውን እንመለከታለን፤ ጠበል÷ አንደኛው

ድኅነትን የምናገኝበት መንገድ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ጠለቅ ብለን ስንመረምር ደግሞ ሊሆን ይችላል የሚለውን ሐሳብ እንድንሰነዝር ያስችለናል፡፡ ይኸውም የሰውዬው ቤተሰቦች መታመም ጸናጽሉን ገበሬው በቤታቸው ማስቀመጣቸው የገዳሚን ታሪክ ማጥፋት ነውና ፈጣሪም ይህ እንዳይሆን ገዳሚ በአማኞቿ ዘንድ እንድትታወቅ ለማድረግ ሲል የፈጸመው በራእይ መልክ የተደረገ ተአምር ነው ማለት እንችላለን፡፡ ሰዎች ሁሌም ለሚሠሩት ጥፋት በሚወዷቸው ሰዎች እንደሚቀጡ ሁሉ ይህም ሰው እርሱ በሠራው ሥራ ቤተሰቦቹ እንደተቀጡ የሚጠቁም ነው፡፡ ጸናጽሉን ከበረት ወስደው አስቀመጡ መባሉ ከጌታ በበረት መወለዱ ጋራ የተያያዘ ነው ልንል እንችላለን፡፡ በመጨረሻም በተግሣጽ መልክ የሚቀርበው ተረክ ልክ እንደ ላይኛው ሁሉ ከአንድ ገበሬ ጋራ የተያያዘ ነው፡፡

> *ሰውዬው በሚያርስበት ወቅት ሃይማኖታዊ ቁስን በማግኘቱ ለአንድ አባት በሚያሳይበት ወቅት ውሰድና እጎተራህ ውስጥ ክተተው ባሉት መሠረት እዚያ ውስጥ ይከተዋል፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ገበሬው በጎተራ ያለውን እህል ቢዝቀው፣ ቢዝቀው አይጎድልም፡፡ ይህንን በተከት በሠከረበት ወቅት ከጓደኛው ጋራ ሲጣላ እየተከራራ እና እየጮኸ እኔ እንዳንተ እንዳልመስልህ፡፡ ጎተራዬ እኮ! ብዝቀው፣ ብዝቀው የሚያልቅ ነው ብሎ ወደቤቱ ተመለሰ፡፡ ፈጣሪም በሰውዬው ተግባር በመቆጣቱ ጎተራውን ባዶ አደረገበት (መምሬ ልሳነ ፣ መጋቢት 4፣2009 ዓ.ም)፡፡*

ተረኩ በአንድ በኩል የፈጣሪን ቸርነት ሲዘክር በሌላ በኩል እንዲሁ የፈጣሪን ተአምር እና ለጋሥነት ሌሎችን ለማንቋሸሽ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከሚፈቅደው ውጪ ለማድረግ የምንገለገልበት ከሆነ እና ከመልካም ተግባር በተቃርኖ የምንቆም ከሆነ ለቅጣት እንደምንዳረግም ተረኩ ይሰብካል፡፡ "ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ" እንዲል (ሮሜ 13፥7)፡፡ በዚህም ተረክ በፈጣሪ የተደረገለትን ከማክበር ይልቅ ሌሎችን አሳንሶ ለማየት እንደተጠቀመበት ከተረኩ እንረዳለን፡፡ ከላይ የተዘረዘረው ዐይነት ቁጣ መሠረት አድርገው የተነገሩት ተረኮች እንዲህ ባለ መንገድ መቅረባቸው በአማኒውም ሆነ በሰሚው ላይ የሚያሳርፉት ተጽዕኖ ይኖራል፡፡ በተለይ ከሃይማኖቱ ውጪ የሆኑ ተግባራትን የሚፈጽሙ ከስፍራው ዕድል ፈንታ የሚያሳጣ መሆኑን በማስገንዘብ በዚህ ውስጥ ያሉትን የማንቃትና የማስጠንቀቅ ተግባር የተላበሱ ይመስላሉ፡፡

በእነዚህ ሦስት ተረኮች የሰዎችን ጥፋት ለማሳየት የተሞከረባቸውን ሁኔታዎች ስንመለከት ሰዎች  በሞት፣ በአካል መጉደልና በሕመም መቀጣታቸውን እንገነዘባለን፤ ተረኮቹም ሁሉም

ሰዎች እንደየሠሯቸውየጥፋት ደረጃዎችቅጣታቸው በዚያው ልክ ይሆናል የሚል አንድምታ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በእርግጥ ከዚህም በተጨማሪ የሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ እንዲህ ዐይነቱ ነገር እንዳይፈጸም ቀድሞ ለማስጠንቀቅ የሚውሉ ይመስላሉ፡፡

### 4.1.5.2. በራእይ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

ይህ ተረክ በአሽክላ ወንዝ ዙሪያ (የቀድሞ የኪዳነ ምሕረት ገዳም ቦታ ስያሜ) ታቦተ ማርያምን እና ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ተሸክመው ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ ተዘጋጅተው የነበሩ ካህናትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ካህናቱ ካረፉበት በመነሣት ጉዟቸውን ለመቀጠል ታቦቱን ሊያነሡ ሲሞክሩ የመድኃኔዓለም ታቦት እሺ ይላል፡፡ የኪዳነ ምሕረት ታቦት ግን እንቢ ስላላቸው ተጨንቀው ምህላ ይይዛሉ፡፡ ከዚያም ቅድስት ድንግል ማርያም የብርሃን ልብሷን ለብሳ እኔ ከዚህች ቦታ አልሄድም፤ ይህቺ የተአምራቴ መገለጫ ናት ብላ እንደቆመች፣ በኋላም እመቤታችን የቆመችበትን ቦታ ሦስት ጊዜ ብትረግጠው ፈዋሴ ደውያን የሆነው ጠበሏ እንደፈለቀ ይነገራል፡፡ ካህናቱም ይህንን ተአምር በዐይናቸው ዐይተው ካደነቁ በኋላ ለእመቤታችን በግንባራቸው ተደፍተው እንደሰገዱ የሚተርክ ነው (መምሬ ተዘራ የካቲት 20፣2009 ዓ.ም)፡፡

እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ኢየሱስ ክርስቶስበቃና ዘገሊላ ሰርግ ላይ ተገኝቶ የመጀመሪያው የሆነውን ውሀውን ወደ ወይንጠጅ በተአምር በመቀየሩ "ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" (ዮሐ. 2፡11) ተብሎ እንደተጠቀሠ ሁሉ በድንግል ማርያም የተሠራው ደረቁን መሬት ወደ ጠበልየመቀየር ተአምርም በካህናቱ ላይስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ታላቅ አድናቆትንና እምነትን ማሳደራቸውን እንመለከታለን፡፡ በተረኩ ላይ ሦስት ጊዜ መሬቱን ብትረግጠው ፈዋሴ ድውያን የሆነው ጠበሏ ፈለቀ የሚሉ ቃላትን እናገኛለን፤ ሦስት ጊዜ የሚለውን ቃላት መዘን ስንመለከት የሦስትነት ምሳሌን እናገኛለን፤በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ" የሚለውን በሦስትነት ውስጥ አንድነትን እናያለንሦስት ቁጥሮች መገኘታቸው ምክንያቶች ይሆናሉ ብዬ የገመትኳቸውን መላ ምቶች ላንሣ፡፡

የመጀመሪያው የሦስት አካላት

- ግዙፍ የሆነ፣ግን የማይታይ ደማዊ ነፍስ ያለው የሥጋ አካል ፈራሽ እና ምድራዊ ነው፡፡

- ረቂቅ የሆነ፣ የማይታይ፣ ግን መኖሩ የታወቀ፣ በልባዊነቱ የሕይወት እስትንፋስ ያለው የነፍስ አካል አፍራሽ እና ሕያው ነው።
- ድብቅ የሆነ፣ አስተዋይ፣ በእምነት ተስፋ ያለው የመንፈስ አካል ለዘለዓለም ነዋሪ እና መንፈሳዊ ነው። እነዚህ ሦስት አካላት አንድ አድራጊ፣ አንድ ሰው በመሆን እና በመወሐድ በእግዚአብሔር መልክ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው (ዲ/ን አሸናፊ 2000፣37)።

ሌላው መላምት በፍጥረት ዘመናት ሦስት መለኮታዊ ኃይላት መጥተዋል። የመጀመሪያው ይህ ዓለም የተከናወነበት የመፈጠር ኃይል ሲሆንሁለተኛው ይህዓለም እንደ ብራና ተጠቅልሎ የሚያልፍኃይል ነው፤ሦስተኛው ኃይል ግን ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ የተነሣበት ኃይል ነው።

ከእነዚህ ከሁለት ኃይሎች ይልቅ ክርስቶስ ሞትን ያሸነፈበት ኃይል ይበልጣል። ምስክርነትን በዚህ ተረክ ላይ ሞትን የማሸነፍ የሚል ነጥብ ባናገኝበትም የሐሳብ መቀየርን ምስክርነትን እንመለከታለን። ሌላኛው መላምቱ ይህንኑ የሚያሳይ ነው። ምስክርነት በሦስት ይጸናል፣ ቅዱስ ጴጥሮስ እስከ ዶሮ ጩኸት ድረስ ኢየሱስ ክርስቶስን ሦስት ጊዜ ስለ መካዱ፣ ስለ ሥላሴ ቅዱስ ሦስትነት እና ስለ አንድነት የመለካት ባህርይ ስለ ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሦሰው እናገኛለን። “ዮናስ ለተርሴስ ሕዝቦች የንስሐ ጥሪ እንዲነግር ሲላክ በእንቢተኝነት በመኮብለሉ ፈጣሪ ባዘጋጀለት ዓሣ ሆድ ውስጥ ለሦስት ቀን እንቢ ያለውን ተልእኮ እስኪፈጽም ድረስ ቆይቷል (ዮ፡1ቁ) ሐሳብን የማስቀየሪያም ቀን ሆኖ እናገኘዋለን”። ምናልባትም ለዚህ ተረክ ሦስት ጊዜ ተብሎ መነገሩ ከእነዚህ ዕሳቤዎች የመነጨ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ካህናቱ የኪዳነ ምሕረትን ታቦት ይዘው ለመሄድ የነበራቸውን ሐሳብ እመቤታችን ባደረገችው ተአምር ሊቀይሩ ችለዋል። ይኸውም ዮናስ የነበረውን እንቢተኝነት በሦስተኛ ቀን የመቀየሩን እና የካህናቱም ታቦቷን ይዘው የመሄድ ሐሳባቸውን የቀየሩበትን ሁኔታ በተረኩ ውስጥ በተመሳስሎነት የቆመ ይመስላል። ሌላውሦስትነትን ምሳሌ ብንመለከት በመልክ፤በግብርሦስት ናቸው፤ በመለከት፣ በፈቃድ አንድ ናቸው የሚለውን የሥላሴን ምስጢር በማሰብ ሲሆን ይህንንም በተረኩ ላይ በተመሳስሎ ቀርቦ እናገኘዋለን።

ሌላውን ከራእይ ጋራ ተያይዞ የሚነሣውን የተረክ ዐይነት እንመልከት።ይህ የተአምር ዐይነት የተፈጠረው፡-

*በ544 ዓ.ም ጥር 11 ቀን በዓለ ጥምቀትን ለማክበር የበረከት ኪዳነ ምሕረትንና የዐቢዩ መድኀኔዓለም ገዳም አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን በዋዜማው ዕለት ጥር 10 ቀን ታቦቶቻቸውን በረከት ላይ አውርደው፣ በድንኳን አስቀምጠው በሠሩት ዳስ ውስጥ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ፣ ሲበሉና ሲጠጡ፣ የማይገባ ሥራ ሲሠሩ የሰብሐተማሕሌቱ አጀማመርና የቅዳሴው መግቢያ ሰዓት በማለፉ የበቁ ባሕታዊ ተገልጸው የተናገሩት ይጠቀሣል (መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ሚያዚያ 2፣2009 ዓ.ም)።* ተረኩ የሚነግረን ሰዎች ስሕተትን ይሠራሉ፤ ከስሕተታቸውም ይድኑ ዘንድ ስሕተታቸውን የሚነግራቸው ሰው ይሻሉ፤ መዳኛውን ለማግኘት የታዘዙትን ሁሉ ይፈጽማሉ። ወዘተ የሚለውን ነው።

ይህንንም በተረኩ ውስጥ እንመለከታለን። ሌላው በጎልጎታ ሄዳችሁ ካላለቀሳችሁ አትድኑም የሚለው ነው። በርግጥ ፈጣሪ ሁሉም ቦታ ይገኛል፤ ሁሉንም ያያል፤ ይሰማል። ታዲያ ለምን በጎልጎታ ሄደው ማልቀስ አስፈለጋቸው? ምሕረትን ለማግኘት ባሉበት ሆነው ለምን አላለቀሱም? የሚለውን ጥያቄ ሊያጭርብን ይችላል። ይሁን እንጂ ሰዎች ከጥፋታቸው ይማሩ ዘንድ ሊቀጡ ይገባልና ቅጣታቸው ሩቅ ተጉዘው ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ለፍተው ምሕረትን ከማግኘት ይጀምራል በሚል ይመስላል። ሌላው ጌታ በጎልጎታ ከሞት እንደተነሣ ሁሉ እናንተም እዚያ ቦታ ከተገኛችሁ ከፈጣሪ ምሕረትን ታገኛላችሁ በሚል ታስቦ የተነገረ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ሥር የምንመለከተው ሌላው ተረክ በዘመነ መሳፍንት በገዳሟ ላይ በተከሠተ ኃይለኛ ወረርሽኝ የተነሣ መነኮሳቱ ታቦቱን በሦስት ሣጥን አድርገው፣ ከመቅደሱ ውስጥ ደብቀው ያቆዩበትን፣ በኋላም አባ ልብነ ድንግል ለሚባሉ መነኩሴ በራእይ ተገልጦላቸው ገዳሟን በድጋሚ ወደነበረችበት እንድትመለስ ያደረጉትን እና የተረኩትን የተረክ ክፍል ነው።

> አባ ልብነ ድንግል ከጎጃም መንገድ ከዋሻ ሚካኤል ከሚባል ቦታ መጥተው በገዳሟ (በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት) ከተሾሙ በኋላ ታቦታቱ ተቀብረውበታል የተባለውን ቦታ ሲያስቆፍሩ ታቦተ ልደታን ብቻ አገኙ። በዚህም ጊዜ ታቦተ ኪዳነምሕረትን እና ታቦተ ሚካኤልን ባለማግኘታቸው ምህላ ይዘው ሳሉ ከመቅደሱ ውስጥ አንድ አንበሳ መሬቱን ሲስም በራእይ ዐዩ፤ የካቲት 16 ቀንም ቦታውን ሲያስቆፍሩት የተሰወሩትን ታቦቶች አገኙ (መርሶ ሕይወት መጽሔት፣ ነሐሴ 2003 ዓ.ም)።

ተሰውሮ የቆየን ነገር ለማግኘት ሰዎች ብዙ መጣር አለባቸው። ጥረታቸውም እውን ይሆን ዘንድ በፈጣሪ መታገዛቸው የግድ ነው። እኚህም ጻድቅ የተሰወሩትን ታቦታት ለማግኘት ብዙ

ጥረዋል። በመጨረሻም በፈጣሪ ርዳታ ማግኘት መቻላቸውን ተረኩ ያስረዳል።ራእይ እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለማድረግ የሚፈልገውን የሚያመለክትልን አንዱ መንገድ ነው። በራእይ የተተረከውም ተረክ እግዚአብሔር እንዲገኙ የፈለጋቸውን ታቦታት እንዲገኙ ለማድረግ አንበሳን እንደ ማሳያ አድርጎ ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል የሚሉትንሐሳቦች ለመሠንዘር ታስቦ የተነገረ ተረክ ነው ማለት እንችላለን።

### 4.1.6. በፈውስ መልክ ከተገለጹ ተአምራት ጋራ በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

የፈውስ ዐይነቶች የተለያዩ ናቸው። እነዚህንም ከፋፍለን ስንመለከት የመጀመሪያው የፈውስ ዐይነት ከአካላዊ ሕመም መዳን ሲሆን ለምሳሌ፡- የዐይንን መብራት፣ የጆሮን መስማት፣ የስብራትን መጠገን፣የቁስልን መሻር፣ ከእንፉቅቅ ቆሞ መሄድንወዘተ ይመለከታል። ሁለተኛው ከአጋንንት እስር ነጻ መውጣት ነው፤ሦስተኛው ፈውስ ከሞት መነሣት ነው።

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ጠበል ፈዋሽነት፣ በታቦቷም ፈጥኖ ሰሚነት እልፍ አእላፍ ሕመምተኞች ተፈውሰዋል፤ ብዙ ተአምራትም ታይተዋል። ከፈውሶቹ መካከል ዕውር ማብራት፣ ሽባ ማቅናት፣ ለምጽ ማንጻት፣ የውስጥ ደዌ መፈወስ፣ የአእምሮን ደዌ ማዳን፣ ከአጋንንትና ከርኩሳን መናፍሳትመላቀቅና ሌሎችም ይጠቀሣሉ። በዚህ ሥር በዝርዝር የተመለከትኳቸው የፈውስ ዐይነቶች የተከናወኑት በጠበል፣ በሰንበቴ ቤት፣ በተግባር ቤት፣ በዳቤ፣ በንፍሮ ውሀ፣ በንፍሮ እና በመስቀል አማካይነት ነው።

ከዚሁ ጋራ በተያያዘ በ(*መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ መጋቢት* 20፣2009 *ዓ.ም*)ሲፈጸም ያየሁት ነው በሚል የነገሩኝን ተረኮች አቀርባለሁ።

> *ልጁ ወጣት ነበር፤የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነበር የሚሠራው። በኋላ ላይ ግን በደረሰበት የመኪና አደጋ የተነሣ መራመድ ባለመቻሉና በሕክምና ሊስተካከልለት ባለመቻሉ ወደ ገዳሟ በመምጣት ዘወትር ይጸልይ ነበር። እንዲያውም ሁል ጊዜ የሚጸልየው ደወሏ ሥር በመሆን ነበር። ፈጣሪ የውስጡን ሰምቶ እሑድለት ነው ትዝ ይለኛል። የበቁ አባት መተው እግሩን ሲያሻሹለትና ሲጸልዩለት እግሩ ቀጥ ዓለለት።*

በወንጌል ውስጥ ስለ ርኩሳን መናፍስት መውጣት የሚነገሩ ተረኮች አሉ። ከእነዚህም ተረኮች (ማር 1፡21፣ 28፤ ሉቃ 4፡21-27፤ ማር 5፡1-10፣ሉቃ 10፡26-28፤ማቴ 10፡20-28) የሚሉት ይጠቀሣሉ።እኚሁ አባት የነገሩኝ ሌላኛው ተረክ

በገዳሚግቢ ውስጥ ውስጧ ሰይጣን ሰፍሮ ነው ተብላ ስትጮኽና ስትዘምር የነበረችውን ወጣት በመስቀል ግንባሯን በመምታት ልቀቅ! ብዬሃለሁ፤ ልቀቃት! ሲሉ ሰይጣኑ በልጅቷ ላይ ዐድሮ ብዙ ካሠቃያት በኋላ ሄጃለሁ፤ ለቅቄያታለሁ ሲል እንደተሰማ ነግረውኛል፤ በኋላም ልጅቷ ጤናዋ ተመልሶላት ወደ ገዳሟ ብዙ ጊዜ ትመጣ እንደ ነበር አጫውተውኛል (መሪጌታ ነቃዐ ጥበብ፣ መጋቢት 4፣2009 ዓ.ም)።

ርኩሳን መናፍስትን ማውጣት በኢየሱስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም።ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌል እንዲሰብኩ ሲልካቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን እንደሰጣቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። “ዐሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ፤ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፤ በርኩሳን መናፍስትምላይ ሥልጣን ሰጣቸው” (ማር 6፡7፤ ማቴ 10፡7-8፤ ሉቃ.9፡10-19) ።

በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜኢየሱስ ይህን ሥልጣን የሰጠው ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ስፍራ ላላቸው ክርስቲያኖች ሁሉም ነው። “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉዋቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ...” (ማር11፡17)። የሐዋርያት ሥራም ስለዚህ ይናገራል (የሐዋ.1፡16)። ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው በፊልጵስዩስ ከአንዲት ልጅ ርኩስ መንፈስ እንደወጣላትሁሉ በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በርካቶች በውስጣቸው ካደረው ርኩስ መንፈስ ነጻወጥተዋል። በተጨማሪም በተረኮች ፈውስን ያገኙት ወጣቶች እንደሆኑ የሚያወሡ ናቸው። ወጣቶቹ የተፈወሱትም በአንድ አባት አማካይነት መሆኑን ተረኮቹ ይናገራሉ ይሁን እንጂ የፈውሳቸው መንገድ የተለያየ ነው። የመጀመሪያው ተረክ በሠርክ ጸሎት አማካይነት የተገኘ ሲሆን የሁለተኛው ተረክ ደግሞ ወጣቷ በገዳሚደጇ ላይ በመገኘቷ የተደረገላት ፈውስ ነው። እነዚህ ሁለት ተረኮች አንድ የሚነግሩን ነገር አለ ይኸውም ወደ ቅዱስ ስፍራ አምኖ የሄደ ሁሉ የፈውስ ተቋዳሽ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ እንደሚኖር የሚያሳይ ነው።

*“እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ ኑ፤ ስሙኝ፤ ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ። በአፌ ወደርሱ ጮሁኩ፣ ባንደበቴም አመሰገንኩት። በልቤም በደልን ዐይቼ ብሆን ኖሮ ጌታ ባልሰማኝም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰማኝ፤ የልመናዬን ድምፅም አደመጠ፤ ጸሎቴን ያልከለከለኝ፣ ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ እግዚአብሔር ይመስገን” (መዝሙር 65፡ 16-20)።*

በተጨማሪም የተረኩ አቀራረብ የወጣቷን ጩኸት፣ የወጣቱንም ጸሎት ፈጣሪ ሰምቶ ፈውስ እንዳገኙ ለመንገር በማሰብ ላይ የተመሠረተ ይመስላል፡፡ በመጨረሻ ከተረኮቹ መዘን የምናየው ሁለቱም ወጣቶች የፈውሱ ተካፋይ መሆናቸውን መተረኩን ነው፡፡በዚህም ሁኔታ ለምንድነው ብዙ ጊዜ የፈውስን እና የተአምራት መፈጸምን ስናነሣ ዋና ገጸ ባሕርይ ወጣቶች ሆነው የሚቀርቡት? የሚሉትን ጥያቄዎች እንድናጭር ያደርጉናል፡፡ በእርግጥ ተረኮች ዋንኛ ተግባራቸው አማኙን አካል በእምነቱ እንዲጸና፣ አፈንጋጩም እንዲመለስ፣ስሕተት ፈጻሚው ከስሕተቱ እንዲታረም ማድረግ ነው፡፡ ይህ ክንዋኔ ደግሞ ቀጣይነቱ የታመነ እንዲሆን፣ አልያም ታሪክ ነጋሪ እንዲኖር ለማድረግም ወጣቶች የተሻሉ ናቸው በማለት ሊፈጸም ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚመረጡት ወጣቶች እነኚህን ተግባራት የመጫወት ሚናቸው የጎላም ስለሚሆን ይህንን ሚናቸውን እንዲያውቁ የተተረከ ተረክ ነው፡፡

ሌላው ወጣቷ የዳነችው በመስቀል መሆኑን ከተረኩ እንመለከታለን፤ማለትም ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ እኛን ያዳነበትን ምሳሌ በመውሰድ ሰዎች በመስቀል እንደሚድኑ ለማሳየት የተነገረም ጭምር መሆኑን ከተረኩ እንረዳለን፡፡ ከዚህ ጋራ በማያያዝ ፈውስን መሠረት አድርገው የተነገሩት ሁለት ተረኮች የተከናወኑት በተግባር ቤት መሆናቸውን እናስታውሳለን፡፡

> ተማሪ ነበረች፤ ብዙ ጊዜ ብቻዋን ነበር የምታሳልፈው፤ በአንድ ዕለትም በደረሰባት አደጋ የሴትነት ክብሯን ከማጣቷም በተጨማሪ በኤች አይቪ ኤድስ ተጠቃች፤ ይህችም ልጅ በተግባር ቤት እየመጣች ሁሌም የንፍሮ ውሀ ትጠጣ ነበር፤ በኋላም ስትመረመር ከሕመሟ መዳኗ ተነገራት (አባ ኪዳነ ማርያም፣ ሚያዚያ፣6 2009 ዓ.ም)፡፡

በተመሳሳይ መልክ በተረክ ዐሥራ ዐምስት በዚሁ በሽታ በበርካታ ጊዜያት ሲሠቃይ ቆይቶ ወደ ገዳሟ በመምጣት ወደ ተግባር ቤት በመግባት፣ ዳቤ፣ ንፍሮ፣ እንጀራ እየበላ፣ የንፍሮ ውሀ እየጠጣ ከበሽታው ሊፈወስ የቻለ ግለሰብ ታሪክ ቀርቧል፡፡

በሁለቱ ተረኮች የፈውሱ ክንዋኔ የተፈጸመው በተግባር ቤት ነው፡፡ እነኚህ በተግባር ቤት የተከናወኑት ፈውሶች ተረኩን ለሚሰማው አካል እንዴት ሊሆን ቻለ?የሚል ጥያቄ ያጭርበታል፡፡ የፈውሱ አካል ለሆነው ደግሞ በተቀደሰ ቦታ የተገኘ ነገር ሁሉ ካመኑበት ያድናል የሚል መልስ ያስከትልለታል፡፡ ይሁን እንጂ እነኚህ ተረኮች ሌላም ዕይታን ማስመዘዝ የሚችሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ድኅነትን ያገኙት በተመገቡት ነገር መሆኑ ፤ ሌላም ጊዜ የታመሙ ሰዎች ከተመገቡና እራሳቸውን ከጠበቁ ከሕመማቸው መዳን ይችላሉ

የሚለውን በተለመደ ብሂልም ላይ ተመሥርቶ በሰው ውስጥ ያለውን አመለካከት በተቀደሰው መንገድ ለማጎልበት ታስበው የተነገሩ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ቀላል የሚባል አይደሉም።

ለዚህ ማሳረጊያ እንዲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተረክ ላንሣ። ኤልያስ ኤልሣቤል ስትዝትበት ፈርቶ በሸሸ ጊዜ ሥንቅ ስላልያዘ ተራበ፣ ተጠማ፣ ዛለ፣ደከመም አንቀላፋም።የእግዚአብሔር ሰው በመሆኑ በእግዚአብሔር መልአክ እጅ ተዳሠሠ። ርቦት ነበር እና እንጀራ በመሶብ፣ ውኃ በመንቀል ስለቀረበለት በላ እና ተኛ። የእግዚአብሔር መልአክ የሚያበረታ ምግብ ይመግባው ዘንድ ዳግመኛ ቀስቅሶ ሲመግበው ሌላ ኃይል ሳያስፈልገው ለሁለተኛ ጊዜ የበላው ምግብ በሰጠው ብርታት ብቻ 40 መዐልት 40 ሌሊት ተጉዞ ኮሬብ ደረሰ የሚለውተጠቅሦ እናገኛለን። ይህም የሰው ልጅ በምግብ ሕይወቱን ማስቀጠል እንደሚችል የሚያሳይ ነው።

ይህ ከፈውስ ጋራ በተያያዘ በትንታኔ የተመረጠው ተረክ በሰንበቴ ቤት በተቀመጥንበት ወቅት ባለ ታሪኳ የነገረችን ነው።

> *ሴትዮዋ ሁለት ቀያይ ወንድ ልጆች አሏት። ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንደማትሄድ ገልጻልኛለች። ይሁንናአንድቀን ልጆቿን ለማዝናናት በወጣችበት ወቅት አንደኛው ወንድ ልጅ ድንገት ይታመምባታል። ሕመሙም ፈጣን ስለነበረ ባቅራቢያዋ ወደሚገኝ ሆስፒታል ብትወስደውም ወደ ከፍተኛ ሆስፒታል ይጻፍላታል። እዚያ በመሄድም ለዓመታት የበሽታ መከላከያ የሆነው የደም ሴሉ ዐልቋል በሚል በሆስፒታሉ ሕክምና ሲታገዝ ቢቆይም ሊሻለው አልቻለም። አንድ ቀን ነው፣ ሴትዮዋን አልግባባትም። እንዲያው አጠገቤ መጥታ ልጅሽ ይህንን ከታመመ ለምን እንጣጦ ኪዳነ ምሕረት ይዘሽው አትሄጂም? ስትለኝ በፍጹም ቤተክርስቲያኗን አላውቃትም ነበርና ሰዎችን እያጠያየኩ በእዚያው እለት መጣሁ። ስመጣ የበዓሏ ቀን ነው አሉ። ብዙ ሰው አለ። እኔም ልጄን ይዤ እያለቀስኩ ከአንድ ከሚያስተምሩ አባት ዘንድ ሄድኩ።ምን ሆነሻል? ሲሉኝ ልጄ ያለበትን ሁኔታ ነገርኳቸው። ለሰባት ቀን አስጠምቂው ብለውኝ ወደ ቤት ተመለስኩ። በነጋታው ጠበሉ በር ላይ ስደርስ ለዓመታት ያልፈሰሰኝ ደም በመፍሰሱ ልጄን እንዴት እንደማስጠምቅ ጨንቆኝ ሳለ ወጣቱ አስጠማቂ አሁንም ድረስ እንደ ቤተሰብ ነን፣ ልጄን አስጠመቀልኝ። እቤት ስመለስ ግን ደሙ መፍሰስ አቁሞ ነበር። በኋላም ለሰባት ቀን ልጄ ሲጠመቅ በእጅጉ ተሠቃይቷል። ይህ የሆነው ለካ! ርኩስ መንፈሱ ከውስጡ ሊወጣ ሲል ነው። እግዚአብሔር ይመስገን! አሁን ድኖልኛል።ከዚያ የሥቃይ ጊዜ በኋላ ለ8 ዓመታት ከኪዳነ ምሕረት ተለይቼ አላውቅም፣ በወር በወር ልጆቼን ይዤ ዐድሬ ነው የምሄደው። (ምህረት ገ/ ሕይወት የካቲት 6፣2009 ዓ.ም)።*

በተረኩ የተገለጸው ሕፃን ፈጣሪ ከሕመሙ ይድን ዘንድ መልእክተኛ ልኮ ወደ ጠበሉ እንዳመጣው እንድናስብ የሚያደርገንን ነገር እናገኝበታለን፡፡ በሌላም ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ የማታውቀውን ሴት ወደ ደጁ እንድትመጣና ተአምሩን በልጇ ፈውስ እንድትመለከት አደረጋት ልንልም እንችላለን፡፡ በርግጥም ብዙውን ጊዜ ሃይማኖታዊ ተረኮች አማኞችን በእምነታቸው የማጽናት፣ የማያምኑትን እንዲያምኑ የማድረግ ሚና የተላበሱ ናቸው፡፡ ይህም ተረክ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ እንዲሁም "ልጆቼ ኑ ስሙኝ"፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ" (መዝ 33፡12) እንዳለ የልጁ እናት ከቤተክርስቲያን ሩቅ መሆን በልጆቿ እንዳይደገም ለማድረግ የተነገረ ሊሆን ይችላል፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር ከፈለገ ሁሉን ማድረግ ይችላል፡፡ ታዲያ ለምን በሕመም ወደ እርሱ እንዲመጡ ያደርጋቸዋል? የሚል ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል፡፡ ይሁንና ሰዎች በመከራቸው ጊዜ የደረሰባቸውን አይረሱምና እርሱን ያምኑ፣ ተአምሩን ያዩ፣ ከምሕረቱም ተቋዳሽ ይሆኑ፣ እምነታቸው ይጸና ወዘተ ዘንድ በማሰብ የተነገረ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በተረኩ ውስጥ የሕፃኑ እናት ለዓመታት ያልፈሰሳት ደም ልጇን ለማስጠመቅ ስትል እንደፈሰሳት የተናገረችውን ቃል እናገኛለን፤ በመጨረሻም በልጁ ውስጥ የነበረው ርኩስ መንፈስ እንደተወገደለት ተረድተናል፡፡

ይህም የእናትዮዋ ደም መፍሰስ ርኩስ መንፈሱ ከልጁ ላለመውጣትና ልጁ እንዳይጠመቅ ለማድረግ ፈልጎ ያደረገው ይመስላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር "ሕፃናትን ተውአቸው፤ ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና" (ማቴ19፡14) የሚለው ቃል እንደተናገረ ሁሉ በመጠመቅ መዳናቸው እውነት ስለሆነ ርኩስ መንፈስ በዚህ ሥጋት ውስጥ በመውደቁ ልጁ እንዳይሄድ ለማድረግ በእናትዮዋ ላይ ይህንን ነገር አደረገ ልንል የምንችልበትን ነገር የሚጠቁመን ተረክ ነው፡፡ ስለ ተአምር ማድረግ ብናነሣ በሥሩ ልናየው የምንችለው አንዱ ነጥብ በፈውስ መልክ የተደረገውን የተአምር ክፍል ነው፡፡በዚህም ሥር በሰፊው የተቃኘው ጠበል በመጠመቅና በመጠጣት የተገለጹ ምሕረቶች እንዲሁም ሙታንን እስከ ማስነሣት ያደረሰውን የምሕረት ታላቅነት የሚዘክረው የተረክ ዐይነት ነው፡፡ ቀዳማዊ ተረክ (መምሬ ልሳነ ወርቅ ሚያዚያ 3፣2009 ዓ.ም) የነገሩኝ ነው፡፡

> *ለዓመታት በሕመም ስትሠቃይ የነበረች ወጣት የተለያዩ የሕክምና ተቋማት ጋራ ብትሄድም ከሕመሟ መዳን ባለ መቻሏ ተስፋ በቆረጠችበት ሰዓት በሰዎች ጠቋሚነት ወደ ኪዳነ ምሕረት በመምጣትና ጠበሏን በመጠመቅ በመጨረሻም ከሕመሟ መፈወሷን የሚተርክ ነው፡፡*

ቀጣዩም ተረክ እንዲሁ ለሃያ ዓመት በእንፉቅቅ ሲሄድ የነበረ ወጣት በጠበሉ በመጠመቅና ሠርክ ጸሎት በማድረግ ቆሞ ለመሄድ መብቃቱን የሚነገር ነው፡፡ (ማሜ አይተንፍሱ፣ ሚያዚያ 3፣2009 ዓ.ም)፡፡ እነዚህ ሁለት ተረኮች በተመሳሳይ መልክ የሚያሳዩት በጠበሉ አማካይነት ምሕረት ማግኘታቸውን ነው፡፡ ከላይ የጠቀሥነው የነቢዩ ዳዊት ትንቢት የእነዚህ ሁለት ተረኮች ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በጠበል ይፈወሳሉ፤ ይድናሉና፡፡ በተረክ ዐሥር የተነገረው ሌላው ተረክ ለዚህ ክፍል በተጨማሪ ግብአትነት ስለሚያገለግል በቀጣይ እንመለከተዋለን፡፡

> *እግሩ አልራመድ እያለው ማስቸገር የጀመረው በዐሥራዎቹ ዕድሜ ላይ እያለ ነበር፤ በኋላ ላይ ግን አልራመድ ማለት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነን ሕመም እያስከተለበት መጣ፡፡ በሰዎች ጠቋሚነት ከጎጃም ድረስ በመምጣት ጠበሏ ንበመጠመቅ፣ ከጠበሏ በመጠጣት፣ የሚያርፍበትም ስለሌለው ከቤተክርስቲያኗ ጥግ በማደር፣ ለዐሥራ ሦስት ዓመታት ያክል ሠርክ በመጸለይና ከጠበሉ ድኅነት እንደሚያገኝ በማመን ቆየ፡፡ አንድ ቀን አንደኛው እግሩ የተለየ መልክ በማሳየት፣ የሟሟ በመምሰል፣ በመጨረሻም በመፈንዳት እሾህ የበዛበት አውሬ መሰል ነገር ወጣለት፡፡ የኋላ ኋላም ቆሞ ለመሄድ መቻሉንበአሁኑ ሰዓት በጧፍ መሸጥ የሚተዳደረውየዚሁ ታሪክ ባለቤት የሆነው ወጣት ይናገራል (አንተነህ ደግ ሰው፣መጋቢት 15፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

ተረኩ የሚነግረን ሰዎች በአመኑበት ነገር እንደሚድኑ ነው፡፡ በተረኮቹ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ቃላት ለይተን ስንመለከት ከላይ እንደገለጽናቸው ተረኮች ከጠበሉ በመጠጣት ብቻም ሳይሆን በመጠመቅም ልጁ እንደተፈወሰ ይተርካል፡፡ መጠመቅን ስናነሣ መጥምቁ ዮሐንስ “የንስሓንም ጥምቀት በኀጢአት ስርየት ያጠምቅና ይሰብክ ነበር (ማር.6፡4፤ማር1፡5)፡፡ ሰዎች በሚታመሙበት ወቅት “ምን ኀጢያት ሠርቼ ነው? ፈጣሪዬ! እባክህ ማረኝ?” ብለው መለመናቸው የተለመደ ነው፡፡ ፈጣሪ ሁሌም መሓሪ ነውና እኛን ሰዎችን በተለያየ መንገድ የምሕረቱ ተቋዳሽ ያደርገናል፡፡ በዚህም ተረክ የተገኘው ምሕረት ይህንን ነገር ለማጽናት ተብሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው አውሬ መሰል ነገር እንደወጣለት የሚገልጸው ነው፡፡ አውሬው ርኩሳንመናፍስትን ለመግለጽ ወክሎ የገባ ይሆናል፡፡ ርኩሳን መናፍስት በአካላችን በተለያዩ መንገዶች ገብተው ይቀመጣሉ፡፡ አውሬው እሾህ የበዛበትና እጅግ አስፈሪ ሆኖ መገለጹ የርኩሳንመናፍስትን አስፈሪነት እና የብዙ መልክ ባለቤትነት አጉልቶ ለማሳየት ጭምር የተነገረ ተረክ ይመስላል፡፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ላካቸው፤ የእግዚአብሔርንም መንግሥት እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ” (ሉቃ 9፡1-2) እንዳለ÷ ይህ ወጣትም የዚህ በረከት ተቋዳሽ መሆኑን ለማሳየት ተረኩ በምስክርነት ቆሟል፡፡ በዚህ ሥር የሚቀርበው ቀጣይ ተረክ

*ሙስሊም ወንድምና እኅትናቸው፡፡ እኅቱ በሆድ ሕመም ስትሠቃይ ለበርካታ ጊዜያት በመቆየቷ ሰዎችን አጠያይቆ ወደ እዚህች ገዳም እንዳመጣት የልጅቷ ወንድም ይናገራል፡፡ እኅቱም ጠበል መጠጣትና መጠመቅ በመጀመሯ በየጊዜው የተለያዩ ስሜቶችን ታሳይ ነበር፤ አንዳንዴም ጩኸቷ እጅግ የበዛ በመሆኑ ድምጿን ሁሉ ዘግቷት ለረጅም ጊዜ ትቆይ ነበር፡፡ በኂላም በኪዳነ ምሕረት መሓሪነት በጠበሏ ተአምር ልጅቷ ብዙውንጊዜ ስትሠቃይ ቆይታ ከሆዷ ውስጥ እባብ መሰል ነገር እንደወጣላት ይነገራል (ሲራጅ ሁሴን የካቲት 2፣2009 ዓ.ም)፡፡*

ሰዎች በተለያዩ ሕመሞች ይጠቃሉ ከእዚህም ይድኑ ዘንድ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ሁሉም እንደየእምነቱ ለፈጣሪው ከሕመሙ ይፈውሰው ዘንድ ይጸልያል፤ ይሳላል፤ከዚያም ሲያልፍ ወደ ቤተ እምነቱ በመሄድ እዚያ በመቆየት፣ ከጠበሉ በመጠጣትም በመጠመቅም የመዳኛውን ቀን በእምነቱ በመታገዝ ይጠባበቃል፡፡ ይሁን እንጂ ከእዚህ ተረክ የምንረዳው ሰዎች ሃይማኖታቸው ምንም ይሁን ምን ያድነኛል ብለው አምነው ወደ እመቤታችን ከመጡ ድኅነትን እንደማያጡም ጭምር ለማሳየት የተነገረ ይመስላል፡፡

ወጣቷ ከሆድ ሕመሟ ለመዳን ሠርክ ጠበል መጠጣቷ እና ጠበል መጠመቋ ተጠቅሟል፤ በዚህም ወቅት ከፍተኛ ጩኸት ታሰማ እንደነበርም ተነግሯል፡፡ ሕሙማን የተቀደሰውን ጠበል በሚጠጡበት ወቅት ውስጣቸው ያሉ ርኩሳን መንፈሶች እንደሚጨነቁ፣ አንዳንዴም በልጅቷ ላይ በማደር፣ ድምፅ በማውጣት፣ አንለቃትም! እስከ ማለት የሚደርሱባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ከዚህም ጋራ ተያይዞ ይሆናል ልጅቷ ያልተለመደ የጩኸት መጠን እንድታስተናግድ የሆነችው፡፡በተጨማሪም ከውስጧ ወጣ የተባለው ነገር እባብ መሰል ፍጡር ነው፡፡ ይህም ፍጡር በዚህ መልክ መገለጹ የርኩስ መንፈስንመልከብዙነት ለማሳየት ሊሆን ይችላል፡፡ በአጠቃላይ መናፍስት ምንም ይምሰሉ ምን በቅዱስ ስፍራ እንደትቢያ የሚከስሙ መሆናቸውንም ጭምር ለማሳየት የተነገረ ይመስላል፡፡

እግዚአብሔር በአንድ መንገድ፣ በሌላም ይናገራል" (ኢዮብ 33፡14)፡፡ ለእዚህችም ወጣት ከሕመሟ መፈወሻ መንገድ የሚነግራት ሰው አዘጋጅቶላት በእነርሱ መሪነት ከሕመሟ እንድትድን አደረጋት የሚለውን በመስበክ የተነገረ ይሆናል ብለን ተረኩን ልንወስደው እንችላለን፡፡በዲያቆን ፈቃደ የተነገረኝ ይህኛው ተረክ ከሞት መነሣትን የሚዘክር ነው፡፡

*ልጅቷ በወንድሟ አስታማሚነት ከሕመሟ ለመዳን ጠበል ስትጠመቅ ብዙ ጊዜያት አሳልፋለች፤ ይሁንና ሕመሟ እየከፋ በመሄዱ እና የመዳን አዝማሚያዋ በመመናመኑ እቤቷ መዋል ጀምራለች፤ ያው ሞት አይቀርምና*

*በመሞቷ ወንድሟ ያስገባችውን ቃል ኪዳን ለማክበር ወደ ቤተክርስቲያኗ እሬዋን ይዞ በመምጣት ሦስት ጊዜ ቤተክርስቲያኗን ሲያዞሩት ልጅቷ ተነሥታለች (ዲያቆን ፈቃደ የካቲት 21፣2009 ዓ.ም)።*

እዚህ ተረክ ላይ ቃል ኪዳን፣ ሦስት ጊዜ ቤተክርስቲያን መዞር እንዲሁም ከሞት መነሣት የሚሉትን ቃላት በዝርዝር እንመልከት። ቃል ኪዳን ማለት መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ሰው ልጆች ይቅርታ የገባላትን ቃል ኪዳን የሚወክል ሆኖ የተገለጸበት ነው። ይኸውም እኅትዮዋለወንድሟ ያስገባችውን ቃል ኪዳን ወካይ ሆኖ እናገኘዋለን። ሦስት ጊዜ ቤተክርስቲያኑን እሬሳዋ መዞሩም የሦስቱ ሥላሴን የሚወክል ተደርጎ የተነገረ ሊሆን ይችላል። ከሞት መነሣቷ መገለጹም እንዲሁ የጌታን በሦስተኛው ቀን ከሙታን መነሣቱን በማሰብ የተነገረ ነው ማለት ይቻላል። ይህም ተረክ የሚያሳየን ብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ ተረኮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክን መሠረት አድርገው የሚነገሩ መሆናቸውን ነው። ተረኮች ሲተረኩ ወዲህ ሃይማኖታዊ፣ ወዲህ ዓለማዊ መሠረት አድርገው ነው ልንል እንችላለን። ለሃይማኖቱ ኃይልም ለዚያ የሚሰጡ በየተረኮቹ ውስጥ ያሉት ምሳሌዎች፣ ትእምርቶች በነዚህም አማካኝነት ተዋቅረው የሚገኙት ሐቲቶች ናቸው።

በዚህ ሥር በዘውግ ከፋፍለን (አዋግነን) በትንታኔ ያየናቸው የተረክ ዐይነቶች ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆኑ ትእምርታዊ ምግባር፣ ነገረ ሰብ፣ ነገረ መለኮትነት ያላቸውን ያህል ርእዮታዊ ዓለማዊ እና ፖለቲካዊ የሰዎች ኑሮ በሥጋም ይበል በነፍስ የሚመራባቸው የሚገዟቸውም መሣሪያዎች ጭምር ናቸው።

## 4.2. በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም የተሰበሰቡ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በትንታኔ የተመረጡት ቁሳዊ ባህሎች ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ከፋፍሎ ለማሳየት የሞከረ ሲሆን ቁሳዊ ባህሎቹ ያላቸውን ተምሳሌታዊ ፍቺ በትንታኔው ላይ ቀርቧል። በዚህ የትንታኔ ክፍል የሚቃኙት ሃይማኖታዊ ቁሶች ውስጥ መስቀል፣ ደወል፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሥዕል፣ መንበር፣ የቤተክርስቲያኗ ሕንጻ፣ መሶበ ወርቅ፣ የቅዱሳን ዋሻ እና ሌሎችም ይጠቀሣሉ። ትንታኔውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክን መሠረት በማድረግ እንዲሁም ከፎክሎራዊ ዕይታ አንጻር የተካሄደ ነው።

### አ4.2.1. ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት የሚያገለግሉ ቁሶች

በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት ገዳም ከሚገኙ ቅርሶች መካከል አብዛኛውን ቦታ ይዘው የሚገኙት የብራና መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህም መጻሕፍት ለገዳሟ በተለያዩ ዘመናት አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ አሁንም ድረስ እየሰጡ ያሉ ናቸው፡፡ ከመጽሐፍቶቹም መካከል በወርቅ፣ በብር የተለበጡ ከተለያዩ አካላት በስጦታ የተሰጡ ይገኙበታል፡፡ መጻሕፍቱም ሃይማኖቱን ለማስተማርና የእምነቱን ሥርዓት ለማጽናት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚህች ገዳም በጥንታዊነታቸው የሚጠቀሱ የብራና መጻሕፍት እንዳሉ ይነገራል፡፡ በዚህ ዙሪያ ያነጋገርኳቸው የዕቃ ቤት ኀላፊ የሆኑት አባ ኪዳነ ማርያም ሙዚየሙን ባስጎበኙን ወቅት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *ይህች ገዳም በውስጧ ጥንታዊ የሚባሉ መጻሕፍቶች አሏት፡፡ በርግጥ ትክክለኛ ጊዜውን ማስቀመጥ ባይቻልም ግብረ ሕመማት፣ ሃይማኖተ አበው እና ተአምረ ማርያም ካሉት መጻሕፍቶች ሁሉ በተለየ ረጅም ዘመን ያሥቆጠሩ ናቸው፡፡ እንዲያውም እኮ አንዳንዶቹ አሁን ላይ አገልግሎት መስጠት ወደማይችሉበት ደረጃ እየደረሱ ነው (አባ ኪዳነ ማርያም  ሚያዚያ 4፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*




**በገዳሟ በሚዚየም ውስጥ የሚገኙ የብራና መጻሕፍት**

ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን ስያሜያቸውን የሚያገኙት አንድም የተጻፉት በቅዱሳን ሲሆን ይዘቱ ስለ ቅዱሳንና ስለ ቅድስና አገልግሎት የሚያወራ ከሆነ ነው፡፡ መጻሕፍ ቅዱስ ሁለት አበይት ክፍሎች አሉት፡፡ አንዱ መጽሐፈ ኦሪት፣ሌላው ሐዲስ ኪዳን ናቸው፡፡



**እቴጌ መነን ከእንግሊዝ አገር ሲመለሱ ያሠሯት ደወል**

**ደወል፡-** የገዳሟ ደወል ከነሐስ የተሠራ እና እቴጌ መነን ከእንግሊዝ ከተመለሱ በኂላ ያሠሩት እንደሆነ ይነገራል፡፡ የደወሉ ቅርጽ ከላይ ጠበብ ብሎ ወደ ታች ሰፋ እያለ የሚሄድ ነው፡፡ ደወሉ በተሠራበት ትልቅ የድንጋይ ቤት ውስጥ ተንጠልጥሎ ይገኛል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ እንደሚገልጸው ደወል ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋል የጀመረው በኖኅ ዘመን ነው፡፡ ኖኅ ከጥፋትውሃ ራሱን፣ ቤተሰቡን፣ እንስሳትን ለማዳን በመርከብ ውስጥ ገብቷል፡፡ በዚያም ሳቢያ በቀን ሦስት ጊዜ ጠዋት፣ቀን፣ ማታ ደወል ይደውል ነበር፡፡የጠዋቱ ለጸሎትና ለተግባር፣ የቀኑ የመመገቢያ ሰዓት መድረሱን ለማብሠር፣ የማታው ለጸሎትና በተለያየ ተግባር በአንድነት የዋሉትን ወደ ማደሪያ ክፍላቸው እንዲገቡ ለማድረግ ነበር፡፡ ዛሬም ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት /በሰዓታት፣ በማሕሌት፣ በቅዳሴ ጊዜ፣ ለንግሥ ጊዜና የምእመናን ርዳታ በሚያስፈልግበት ጊዜ በተጨማሪም ለሐዘን፣ ለደስታ ደወል ይመታል፡፡ እነዚህም የራሳቸው የሆነ ምሳሌና መልእክት አላቸው፡፡

**የተጋብኦ ደወል፡-** ይህ ደወል የሚደወለው ለሰዐታት፣ በማሕሌት፣ ለፍታት፣ለካህናት ሰዓት መድረሱን ለማስታወስ ነው፡፡ ምሳሌነቱም ደወሉ ሲደወል በሩቅ መሰማቱና ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲመጡ ማድረጉ የነቢያት ምሳሌ ነው፡፡ ሌላው የጌታን መወለድ አስቀድመው ያወቁት አዳምና የልጅ ልጆቹ በተስፋ እንዲጠባበቁ አድርጓል፡፡

**የግብር ደወል፡-** ቅዳሴ ሊገባ ሲል የሚደወል ነው፡፡ ምእመናን ለቅዳሴ እንዲዘጋጁ የማድረግ አገልግሎት አለው፡፡ ምሳሌውም የብሥራተ ገብርኤል እና የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ስብከት ነው፡፡ ዮሐንስ ጌታ ከመወለዱ ስድስት ወር ቀድሞ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችን ንስሓ ግቡ" (ማቴ4፡17) እያለያወጀበት፣ ደወሉም ቅዳሴ ከመገባቱ በፊት እንደተደወለ ሁሉ ገብርኤልም ድንግል ማርያም ከመፅነሷ አስቀድሞ ስለነገራት ነው፡፡ ዮሐንስም ጌታ ከመወለዱ ቀድሞ ስለታሰበ ደወሉም ከቅዳሴ በፊት ይደወላል (ዮናስ አባተ 1995 ዓ.ም)፡፡

**የወንጌል ደወል፡-**ይኸኛው ደወል የሚደወለው በቅዳሴ መካከል ወንጌል ተነቦ እንዳበቃ ዲያቆኑ "ዓኡ ንኡሰ ክርስቲያን" ከማለቱ ቀድሞ ነው፡፡ ምሳሌነቱም የስብከተ ዮሐንስ፣ የሐዋርያትና የሰብአ አርድእት ለቅሶ ምሳሌ ነው፡፡ ጌታ ሕገ ወንጌልን ከማስተማሩ በፊት ሰዎች ልባቸውን በንስሓለክርስቶስ እንዲዘጋጅ ዮሐንስ አስተምሯል፡፡ እንዲሁም ጌታ በአይሁድ እጅ ተይዞ መከራ ሲቀበል ዮሐንስ አልቅሷል፡፡ ይህም የእርሱ ምሳሌ ነው፡፡

**የእግዚኦታ ደወል፡-** ክርስቶስ ሲሰቀል እናቱ ድንግል ማርያም እና ወንጌላዊ ዮሐንስ አልቅሰዋል፡፡ ምእመናንም በዚህ ደወል ስለ በደሉት በደል "አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን" የሚሉበት ነው፡፡ ቅዳሴው ወደ መጠናቀቁ ሲደርስ ሥጋውና ደሙንለምእመናን ሲቀርብ የሚደወለው ደወል የድርገት ደወል ይባላል፡፡ ይህ ደወል ሲደወል የሚያስቀድሱ በሙሉ ይሰግዳሉ፡፡ የሚሰግዱትም (ማቴ 28÷9) ላይ እንደተገለጸው ጌታ ከሞት በተነሣ ዕለት ወደ መቃብሩ ሔደው የነበሩ ሴቶች ከእግሩ ወድቀው የመስገዳቸው ምሳሌ ነው፡፡ ደወሉም የሐዋርያት የሰብዓ አርድእት ትእምርት፣ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን ሲገንዙት ያለቀሱት ለቅሶ ምሳሌ ነው፡፡



**በገዳሚ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረአሁን ላይ በዕቃ ቤት ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ የሰጎን ዕንቁላል**

**ጉልላት፡-** በቤተክርስቲያን አናት ላይ ክብ ሆኖ በንጉሥ ዘውድ ወይም በቁም መሶብ ቅርጽ የሚሠራ ትንሽ ቤት የሚመስልና በአናቱም ላይ መስቀል ያለው በመስቀሉ ዙሪያ ዕንቁላል ቅርጽ ያላቸው ከተለያዩ ነገሮች የተሠሩ ወይም የሰጎን ዕንቁላል የተሰካበት ነው፡፡ ይህም አብዛኛውን ጊዜ የሚሆነው ክብ ቅርጽ ያላቸው ቤተክርስቲያኖች ላይ ነው፡፡ በመስቀሉ ላይ መሰካት አለባቸው የሚባሉት የሰጎን ዕንቁላሎች ቁጥራቸው ሦስት፣ ዐምስት፣ ሰባት እና ዐስራ ሁለት የሚደርሱ ናቸው፡፡ ሶስቱ ሶስቱ ስላሴ ምሳሌ፣ሰባቱ የሰባቱ ሚስጥራት፣አስራ ሁለት የአስራ ሁለቱ ሀዋርያት ምሳሌ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በተለይም በከተማ የሚገኙ ቤተክርስቲያኖች የሰጎን ዕንቁላል ለማግኘትና ለማድረግ የማይችሉ በመሆኑ ከብረት፣ ከቆርቆሮ፣ ወይም ብርጭቆ መሰል ነገር በመጠቀምና ነጭ ቀለምበመቀባት ይገለገላሉ፡፡ በፎቶም ላይ የምትመለከቱት የሰጎን ዕንቁላል አሁን ላይ በገዳሚ ዕቃቤት የተቀመጠ ነው፡፡ የሰጎን ዕንቁላል ተምሳሌቱ የሰጎኑ እንቁላሉ ተፈልፍሎ እስኪወጣ ድረስ ዐይኑን ከዕንቁላሉ ላይ አይነቅልም፡፡ ሰጎኑ ለምግብ ሲነሣ እንኳን ሌላ ሰጎን ተክቶ ነው የሚሄደው ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን ለአፍታም ዐይናቸውን ካነሡ ሰጎኑ ይበላሻል፡፡ ይህም ፈጣሪ ቤተክርስቲያን በማንኛውም ጊዜ ይጠብቃታል ይህ ግን ከተቋረጠ ሰይጣን ቤተክርስቲያኗን እንደሚፈታተናት በማሰብ ነው(ገ/ሚካኤል ወልደሰንበት፣የካቲት8፣ 2009 ዓ.ም)፡፡





**ውዳሴ ማርያም** **ቅዳሴ ማርያም**

**በገዳሟ ከሚገኙ የተአምረ ኪዳነ ምሕረት መጻሕፍት የተወሰዱሥዕሎች**

**ሥዕል፡-** በብሉይ ኪዳን በታቦተ ሕጉ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥል ሙሴ እንደታዘዘ /1ኛ ነገ 6፡2ኛ/2ኛ ነገ.6፣2-7/ ሕዝ 9፣3፡10÷3) ተጠቅሟል፡፡ እነዚህም ሥዕሎች ከታቦት አይለዩም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ትእዛዝ ዐብነት አድርጎ ጠቢቡ ሰሎሞን ታላቁን ቤተ መንግስት በሠራበት ወቅት ውስጡንም፣ ውጪውንም በሥዕል አስጊጦ ነበር፡፡ በቤተክርስቲያን ሥዕል የመሣሉ ሌላው ምክንያት በቂ የሃይማኖት መጻሕፍት ስላልነበሩና ሕዝቡን እንደ ልብ ለማስተማር ባለመቻሉ ነበር፡፡ ሥዕል በመንፈሳዊ ሕይወት፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ ወንጌልን በማስተማር፣ በሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ያገለግላል፤ወደ ፎክሎሩም ስናመጣው እንዲሁ የራሱ የሆነ የዕይታ አቅጣጫን ይፈጥራል፡፡ አንደኛው አገልግሎቱ ሲሆን ሌላኛው በሥዕሉ ላይ የሚታየው የአሣሣል ዘይቤ ነው፡፡ አገልግሎቱን ስናነሣ መቼ? ለምን? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንድንጠይቅ የሚያደርገን ነው፡፡ የአሣሣል ዘይቤውም እንዲሁ የአሣሣል ጥበብ ጥንታዊ መሆን፣ ታሪክ ወይም ገላጭ ድርጊቶች ላይ ማተኮር፣ የቀለም ምርጫና ትርጉሙ ምስጢር ዐዘል መሆን እና አካባቢያዊ ዕፅዋትን እና ቁሶችን በመጠቀም የሚፈጠሩት ቀለማት ሳቢነት በሥዕላትና ሐረጋት የሚታይ ነው፡፡

### 4.2.2. ሥርዓት አምልኮን ለመፈጸም የሚያገለግሉ ቁሶች

በዚህ ሥር ለትንታኔ የተመረጡት ቁሶች ሃይማኖታዊ ሥርዓተ አምልኮ ለመፈጸም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡



**የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም(ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን)**

ስለ ቤተ ክርስቲያኗ አሠራር ከማውራቴ በፊት ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ስያሜና አሠራር ምን ይመስል እንደነበር የተወሰኑ ምንጮችን በመጥቀሥ ላስፍር፡፡ ዛሬ ሕንጻ ቤተክርስቲያን የሚባለው ሕንጻ ቤተክርስቲያን ከመባሉ በፊት በብሉይ ኪዳን በተለያየ ቅርጽና መጠሪያ ይሠራ ነበር፡፡ ይኸውም የማደሪያ ድንኳን በኋላም የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በዘመናቸው የእግዚአብሔር የማደሪያ ቦታ ነበረ፡፡ በአሠራረራቸው፣ በክፍላቸው ብዛት እና በውስጣቸው በሚገኙት ንዋያተ ቅድሳት ልዩነት አልነበራቸውም፡፡ ልዩነታቸው የማደሪያው ድንኳን ተንቀሳቃሽ ሲሆን፣ ቤተ መቅደሱ ቋሚ ነበር፡፡ የተሠራበትንም ቁስ ስንመለከት ድንኳኑ ከጨርቅ፣ ሕንጻው ደግሞ ከዕንጨትና ከድንጋይ ነበር፡፡ የማደሪያ ድንኳን አሠራር የተሰጠው ለሙሴ ሲሆን፣ ቤተ መቅደሱ ደግሞ ለዳዊት ነው፡፡ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን የሆነው ታሪክ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ባርነት በሙሴ አማካይነት ነጻ እንደወጡና ከእግዚአብሔር ጋራም ኅብረት መጀመራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሲና በረሀ የተሠራው የማደሪያው ድንኳንም የኅብረቱ ማእከላዊ ቦታ ነበር፡፡ የብሉይ ኪዳን የማደሪያ ድንኳን ለሐዲስ ኪዳኑ /በዛሬው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን/ መሠረት ሆኗል፡፡ ለዚህም መነሻ አምላክ ሰው ሆኖ አዳምን ለማዳን በዚህ ዓለም በመጣበት ጊዜ በአልዓዛር ቤት ሥርዓተ

ቁርባንን አስተማራቸው። ምስጢረ ትንሣኤውም የቤተክርስቲያን ምስጢር ሆኖ ተሠራ። ክርስቲያኖቹም በየቤቱና በየዋሻው እየተሰበሰቡ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ሲያቀርቡ ቆዩ። ምስጋና ማቅረቢያና መሰብሰቢያቸውም የአልዓዛር ቤት ምሳሌ ነበር።

የመጀመሪያዋ ክብ ቤተክርስቲያንም የታነጸችው ሐዋርያት ጳውሎስና በርናባስ በፊልጵስዩስ አማካይነት ነው። ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ የሚሠሩት ቤተ ክርስቲያኖች የአሠራር ቅርጻቸው ይለያያል። የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቤተክርስቲያን አመሠራረቷ በፊት ታቦቷ በድንኳን ለሦስት ዓመታት እንደተቀመጠች ይነገራል። ይህም ምናልባት ጥንት በብሉይ ኪዳን ይሠራ የነበረውን ወይም አሁን ላይ ሕንጻ መገንባቱ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ በማሰብ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ እንችላለን። ሌላው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሦስት ዐይነት የቤተክርስቲያን ቅርጽ አለ። ሰቀላ፣ ክብ (ቤተ ንጉሥ) እና ፍልፍል (ዋሻ) ናቸው። የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቤተክርስቲያንም ክብ ናት። ክብነት የፍጹምነት ምሳሌ እንደሆነ ይነገራል። ሌላው በዚህች ቤተክርስቲያን ሥር የመቅደሱ ጠለል እንደሚፈልቅ ይነገራል። ዙሪያዋንም በአጸድ መከበቧ ቅዱሳን መላእክት ሌሊትና ቀን በቤተክርስቲያን ዐጸድ ዙሪያ ለመዘመራቸው ምሳሌ ነው።



**በ1890ዎ አካባቢ ከንግሥት ዘውዲቱ የተበረከተ መሶብ ወርቅ**

በገዳሟ ሙዚየም ውስጥ የተቀመጠችው መሶበ ወርቅ በ1890ዎቹ አካባቢ ከንግሥት ዘውዲቱ ለገዳሟ በስጦታ መልክ የተበረከተች ናት። እሸቱ 1987፣ 103-104 በአንድምታ ትርጓሜ ላይ ስለ መሶበ ወርቅ የተገለጸውን አስፍሮ እናገኛለን። ይኸውም ሙሴ ወንድሙን አሮንን ጠርቶ ወርቁን እንደ ቅጠል አሳስቶ፣ መሶቡን ውስጡንና ውጪውን በወርቅ ለብጦ፤ በውስጧም ዘመን ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና እንዲያኖርበት ማዘዙን፣ አሮንም የሙሴን ቃል ሰምቶ ለልጅ ልጁ ዘመን ይጠብቅላቸው ዘንድ መሶበ ወርቁን ወስዶ በደብተራ ኦሪት ማኖሩን፤ ይኸውም በጊዜው ቀጣዩ ትውልድ በአባቶቻቸውላይ እግዚአብሔር ይህን የመሰለ መና ሲመግባችሁ እንዴት ከዳችሁት? ብለው መፈራረጃ እንዲያደርጉባቸው ሲሆን ፍጻሜው ግን መሶበ ወርቅ የድንግል ማርያም ወርቁ የንጽሕናዋ፣ የቅድስናዋ፣ መና የወልደ እግዚአብሔር፣ መናውን ብዙ ዘመን ሲኖር ዘመን እንዳለወጠው፣ እግዚአብሔርም ሰው ሲሆን አምላክነቱን ላለመለወጡ ምሳሌ ነው። በሥዕሉ ላይ የምንመለከታቸው መሶበ ወርቆች አሁን ላይ በሙዚየሙ ውስጥ የተቀመጡ ናቸው። መሶበ ወርቆቹ ወደዚህች ገዳም በስጦታነት ከመሰጠታቸው በፊት ንግሥት ዘውዲቱ ጌጣ ጌጦቻቸውን ያስቀምጡባቸው የነበረ መሆኑን አባ ኪዳነ ማርያም ይገልጻሉ።



**ስውራን እንደሚኖሩበት የሚነገርለት ዋሻ**

በመጽሐፈ ነገሥት በኤልዛቤልና በአክዓብ ዘመነ መንግሥት ለጣዖት ያልሰገዱ ሁሉ ይገደሉ፣ ነቢያቱም ይሰደዱ ስለነበር ነቢዩ ኤልያስ ለፈጣሪው ብቻዬን ቀርቻለሁና ውሰደኝ ብሎ ሲለምን፤ እግዚአብሔርም ብቻህን አይደለህም ለጣዖት ያልሰገዱ ሰባት ሺህ ሰዎች አሉ በማለት እንደመለሰለት በ(1ኛ ነገ 19፣10-18፤ ሮሜ 11፣3-5)፡፡ ተጽፏል፡፡ የመሰወር ፅንሰ ሐሳብ ከዚህ ይጀምራል፡፡ በቅዱሳን ታሪክ ሁሉ መሰወር አንድ ትልቅ ትእምርት ነው፡፡ መጽሐፈ መነኮሳት ላይ ከማዕረግ ምንኩስናዎች ውስጥ አንዱ መሰወር (መብቃት) ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ታሪክ ውስጥ እንኳን ከመካከላቸው አለ፤ዝግ በሆነቤት ውስጥ ገባ ተሠወረባቸው የሚሉ ጥቅሦች እናገኛለን፡፡ ይህም የቅዱሳን ታሪኮች ውስጥም ተደጋግመው የሚገለጹበት የመባያ ጉዳይ ነው፡፡

ከእነዚህ ዋሻዎች ጋራ በተያያዘ የሚነገረው ነገር ገዳሟ ከመመሥረቷ በፊት እንደማረፊያና በተለያዩ ወቅቶች እንደ መሸሸጊያ ማገልገላቸው ነው፡፡

ይህ ተረክመነገሩ በቦታው ለሚኖሩ ገዳማውያን የቦታውን ታላቅነትና ክብር እንዲያምኑ የሚያደርግ ሲሆን፣ ወደ ገዳሟ ለሚመጡ ምእመናን ደግሞ በረከትን እናገኛለን ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው፡፡

በገዳሟ የሚኖሩት መነኮሳት የሚያርፍባቸው ትላልቅ ሦስት የዋርካ ዛፎች ነበሩ በኋላ ዋርካዎቹ ስለተቆረጡባቸው ወደዚህ ዋሻ ገብተዋል፡፡ እኔ ዋሻ ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ ውስጡም በጣም ረጅም መንገድ ያለው ነው፡፡የተወሰነ በኩራዝ አማካይነት ከተራመድኩ በኋላ ሰፊ የሆነ ባሕር በማየቴ ፈርቼ ተመለስኩ ሲሉ ስለ ዋሻው ታሪክ የነገሩኝ 90 ዓመት የሆናቸው መምሬ ልሳነ ወርቅ ናቸው፡፡



**በገዳሟ ሙዚየም ውስጥ የሚገኝ መንበር**

**መንበር፡-** መንበር በዕንጨትና በብረት ነው የሚሠራው፡፡ አሠራሩም /አራት ማእዘን ቅርጽን ይዞ ነው፡፡ አራት ማእዘን መሆኑ ነቢዩ ሕዝቅኤል ያያቸው የሥላሴን መንበር የሚሸከሙት የአራቱ ኪሩቤል አምሳል ነው፡፡ /ሕዝ.1፣5-28/፡፡ ሌላኛው ምሳሌ ጌታን በማኅፀኗ የተሸከመችውን እናቱን ይመስላል፡፡

ይህ መንበር በቤተክርስቲያኗ ለበርካታ ዘመናት ሲያገለግል በመቆየቱ አሁን ላይ ወደ ሙዚየም እንዲገባ የተደረገ ነው፡፡



**በሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ገዳሟ ስትቆረቆር የነበሩ ጥንታዊ መስቀሎች**

**መስቀል፡-** ከዕንጨት፣ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከወርቅ፣ ከድንጋይ ሊሠራ ይችላል፡፡ በእነዚህ መሠራቱ የእራሱ የሆነ ምሳሌዎች አሉት፡፡

በዕንጨት መሠራቱ ጌታ የተሰቀለው በዕንጨት ላይ ስለመሆኑ፡፡ ብረት በመስቀሉ ላይ የተቸነከረው ብረት ምሳሌ፡፡ ከወርቅ ሰብአ ሰገል በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ የገበሩለትና የባሕርይ ንጉሥ የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡ ከብር መሠራቱ የአስቆሮቱ ይሁዳ በሠላሳ ብር የመሸጡ ምሳሌ ነው፡፡ ከነሐስ ንጹሕ ሆኖ ሳለ የፈሰሰው አማናዊ ደሙ ምሳሌ ነው፡፡ የዕንጨት መስቀሉ በዘፍ 7፣1-6/ የተገለጸውን የኖኅ መርከብ የተሠራችበት ዕንጨት እንዲሁም (ዘፀ 4፡2-9) ሙሴ የፈርዖን መሰላልን ድል ያደረገበት በትር ምሳሌም ጭምር ነው፡፡

የመስቀል አገልግሎት በሦስት ይከፈላል፡፡ ይኸውም የእጅ መስቀል፣ የአንገት መስቀል እና የመጻር መስቀል ናቸው፡፡ እነዚህ መስቀሎች እንደሚሠሩበት ቁስ ሁሉ ቅርጻቸውም የተለያየ ነው፡፡ በፎቶ ላይ የምንመለከታቸው መስቀሎችም ይህንን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ መስቀሎቹ በገዳሟ ለምን ያህል ጊዜ እንዳስቀጠሩ ጽሑፋዊ መረጃዎች ባይኖሩም የጥንት ናቸው በሚል በአሁኑ ሰዓት በሙዚየም ውስጥ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡

# ምዕራፍ ዐምስት

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና ዐላማ አድርጎ የተሣው ከእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ለገዳማውያንና ለገዳማዊ ህይወት የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመርን ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዐላማ ከግብ ለማድረስ የጽሑፍ መረጃዎችን በመመልከት ቃለ መጠይቅን እና ምልከታን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

መረጃዎቹን በጽሑፍ ማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍ እና በመቅረጸ ድምፅ አማካይነት ተቀርጸዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም የተለያየ ማጣቀሻ መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በጥናቱ ትንታኔ ገዳሟ ጥንት የነበሯት ታሪኮች፣ ምእመናኑ በገዳሟ ያላቸው አመለካከት፣ የተደረገላቸው ተአምራት፣ የሚነገሯቸው ትንቢቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በጥናቱ ዐሥራ ሦስት ተዛማጅነት ያላቸው ሁለት ከታሪክ ትምህርት ክፍል አምስት ከስነ መለኮት ኮሌጅ ቀሪዎቹ ስድስት ጥናቶች ከስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሩ ናቸው፡፡

በእነዚህም ጥናቶች የታዩ ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ በገዳሟ የሚተረኩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ ከተሰጡት ትንታኔዎች በመነሳት የሚተረኩት ተረኮች የተወሰኑት የገዳሟን አመሰራረት በማን እና እንዴት እንደተመሰረተች የሚገልጹ ናቸው፡፡ ከዚህም መካከል አባ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ ከተባለው ገዳም በመለአኩ መሪነት ወደዚህች ገዳም በመምጣት ገዳሟን መገደማቸው የሚተረከው አንዱ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቹ የሚነግሩን ነገሮች ምንድን ናቸው? ቁሶቹስ ያላቸው አገልግሎት ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አስችሏል፡፡ በመሆኑም ከገዳሟ አመሠራረት ጋራ በተያያዘ በርካታ ልዩ ልዩ ተረኮች እንደሚነገሩ፣ እነዚህም ተረኮች የገዳሟን ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተልነትና በማስረጃነት የሚቀርቡ መሆናቸው ታይቷል፡፡

ቁሳዊ ባህሎቹም እንዲሁ የተረኩን መረጃ ለማጎልበት በተጨማሪም በራሳቸው ቆመው ታሪክን የመንገር ዐቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ሌላው ቁሳዊ ባህሎቹ ከገዳሚ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋራ የተያያዙ እና የአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ መሆናቸውን በጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ተረኮቹንም የገዳሚን ጥንታዊነት፣ የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ፣ የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ፣ የገዳሚን ቅርስየሚዘክሩ ወዘተ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ እነዚህ ተረኮች ከሚያስተላልፉት መልእክት በተጨማሪ የሚቀርቡት በቅዱሳን በመታጀብ እና በቁሶች በመደገፍ መሆኑ ታውቋል፡፡

## 5.2 የይሁንታ ሐሳቦች

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ ከተከናወኑ የቅድመ መስክ፣ በመስክ ላይ በድሕረ መስክ ከታዩ ተግባራት በመነሣት የሚከተሉት የይሁንታ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡

የገዳሚን ንብረት ቁሳቁስ ለመንከባከብና ለጎብኚዎች ለማሳየት እንዲመች ቁሶቹ በሙዚየም ውስጥ መቀመጣቸውይበል የሚያስብል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት ሙዚየሙ በተለያዩ ነገሮች አለመመቻቸት አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የገዳሚን ታሪክ ለማወቅ ለሚፈልጉ አካላት ሊሰጥ የሚችላቸውን የተወሰኑ መረጃዎች ለማድረስ እንዳይችል አድርጎታል፡፡

ከዚያ በተጨማሪ ገዳሚ ልታገኛቸው የምትችላቸውን ገቢዎች እያጣች በመሆኑ ሙዚየሙ አገልግሎቱን የሚቀጥልበት ሁኔታ ቢመቻች ሌላውና ዋነኛው ጉዳይ 1500 ዓመት እንዳስቆጠረች የሚነገርላት ይህች ገዳም በቂ የሆነ ጽሑፋዊ መረጃዎችን በተገቢ ሁኔታ ያልያዘች መሆኗ የገዳሚን ታሪክ በተጨባጭነት ለማወቅ ለሚፈልጉ አካላት የመረጃ ውስንነት እንዳይፈጠር ምርጃውን ሰንዶ በማስቀመጥ ቁሶቹንም እንዲሁ በተገቢው ሁኒታ በማኖር ላይ ብዙ ቢሠራ፣ በመጨረሻም ገዳሚ የንፍሮ ገዳምነቷን እያጣች በመሆኗ ስያሜዋን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋልና (በእርግጥ አሁን ወደዚያ በመመለስ እየተሠራ ነው)፡፡ የተጀመሩት ሥራዎች ተጠናክረው ወደ ቀድሞ ይዞታዋ መመለስ ብትችል የሚሉት ናቸው፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


*ሉሌ መልአኩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣1997 ዓ.ም።*

*መንግሥቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ። የቤተክርስቲያን ታሪክ(ቁጥር ሁለት)። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች ድርጅት፣ 2000 ዓ.ም።*

*መርሶ ሕይወት መጽሔት። ነሐሴ 2003 ዓ.ም።*

*መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ማኅበር። የኦሪት ዘ ፍጥረት ትርጓሜ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሳለም ማተሚያ ቤት 1999 ዓ.ም።*

ምሕረት ተስፋዬ።/"ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2003 ዓ.ም።

ሞገስ ጀንበሩ። "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ሥርዓቶች"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎርክፍለ ትምህርት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2003 ዓ.ም።

ሰሎሞን ተሾመ። ፎክሎር ምንነቱና የትኩረት አቅጣጫ። አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግልማህበር፣ 2007 ዓ.ም።

ሰሎሞን ቶልቻ ድንቁ። ፍኖተ ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጉዞ ሒደት ከ1826-1991 ዓ.ም።አዲስ አበባ፣ አዲስ ኅትመት ማተሚያቤት፣1991ዓ.ም።

*ስንታየሁ አባተ። ደወል በቤተክርስቲያን አገልግሎት ሐመር። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት 1995 ዓ.ም ገጽ 47-49*

ሥርግው ኃብለ ሥላሴ። "የአማርኛ የቤተ ክርስትያን መዝገበ ቃላት"አዲስ አበባ ፣1971ዓ.ም።

*ብርሃኑ ገብረ አማኑኤልና ሌሎችም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ። አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ መጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1997ዓ.ም።*

ተስፋዬ ተገኝ፡፡ "የደብረ ነጐድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2003 ዓ.ም፡፡

ታደሰ አይችሉህም፡፡ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምንኩስና ሥርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ከትእምርታዊነት አንጻር በዝቋላ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ ተክለ ሃይማኖት ገዳም"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣1999፡፡

*ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥ-ጽሑፍ ንባብ፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም፡፡*

*አማና በላይ፡፡ መጽሀፍ ክቡር "ክብረ ሊቃውንት ቅዱሳን ወ ምእራፍ ሀያውያን"፡፡ ማተሚያ ቤት አልተገለጸም 2001 ዓ.ም፡፡*

*አሸናፊ መኮንን፡፡ የሚለወጥ ፍቅር፡፡አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት/ ሁለተኛ እትም/፣2000 ዓ.ም፡፡*

*ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1962 ዓ.ም፡፡*

*ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣1980ዓ.ም፡፡*

*ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ ፣አርትስቲክ ማተሚያ ቢት፣1993ዓ.ም፡፡*

*እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው፡፡ ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ፡፡ አዲስ አበበ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1987 ዓ.ም፡፡*

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1948 ዓ.ም፡፡

*ዘሪሁን አስፋው፡፡ የሥነ-ጽሑፍ መሠረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2004ዓ.ም፡፡*

ያረጋል አበጋዝ፡፡ ፍኖተ ቅዱሳን፡፡ ማተሚያ ቤቱ አልተገለፀም፣1995 ዓ.ም፡፡

ዮሴፍ በኪ፡፡ "የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ታሪክ ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ፣የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2007 ዓ.ም፡፡

ዮናስ አድማሱ፡፡ "አስረኛንኩዋ?" ሀዲስ አለማየሁና የመኀበራዊ ሂስ ሥልታቸው"፡፡ የኢትዮጵያ የቋንቋዎች የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፡፡ ቁጥር 10፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ገጽ 77-119፣ 1992 ዓ.ም

*ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ ዐዲስዐማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962ዓ.ም፡፡*

*ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል፡፡ የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ቤተ ደናግል፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ ማተሚያ ቤት 1999 ዓ.ም፡፡*

*ዳንኤል ክብረት፡፡ የቤተክርስቲያን መረጃዎች፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1999 ዓ.ም፡፡*

*ዳኛቸው ካሳሁን(መልአከ ሰላም)፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እና መንፈሳዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኀበረ ቅዱሳን ማተሚያ ቤት፣1999 ዓ.ም፡፡*

*ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፡፡ ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ፡፡ አዲስ አበባ፣ 2008 ዓ.ም፡፡ (ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም)፡፡*

*ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነ-ቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም፡፡*

ፍጹም ኩራባቸው፡፡ "የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2006 ዓ.ም፡፡

Bascom, William. “The Form at Folklore”: Prose Narrative.The Journal of American Folklore,1965.

Benamos, David Jules. Mind in Matteri An: introduction to Material Culture theory and method on line. Avaliable at http://www.Jstor.org/vcpress.1982.

Danielson, Larry. “Religious Folklore”. Folk Groups and Folk Genres: An Introduction. lo ngan Utah State University Press, 1986.

Dan, Ben-amos. Taward A Definition at folklore incontext. The *journal at American folklore,1971.*

Deign,Linda .“Oral Folklore, oral narratives”.In Folklore And Folk life; Richard M.Dorson (ed) Chicago and Londo; The University of Chicago press,1972.

Dorson, Richard. “Current folklore Theories”.Journal At Current Antropology, 4 (1), (93 -112), 1963.

______ . *Folklore and Folk Life :An Introduction. Chicago;The University of Chicago Press, 1972.*

Finnagane,Ruth_.*Oral Traditions And The Verbal Arts. Londa And Newyork; Routledge,1992.*

GlAssie,Henry.“Material Culture”.Chicago and London; The University of Chicago Press, 1999.

Habtamu Mengiste. “A History at Monastery at Mertulamariam (1500-1974)”.Addis Ababa University; Department History,B.A Thesis,1988.

Hailemichael Welde Tekle Haymanot .“A brief History of Debrahayk Sanit Stephen Abuna Yasus Mom Communal Monastery in South Wollo’’.Addis Ababa; Holy rinity Theology College,B.A Thesis

Marivate,C.Tsonga folktale: form, Content Delivery unpublished Masters thesis, Pretoria: UNISA.1973.

Mengistu Kebede. “The Role of Debre Libanos Monatery in the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church”.Addis Ababa; Holy Trinity Theology College,B.A Thesis 1999.

Olriex, Axes. Principle for Oral Narrative Research. Trans Wolt. K and Jenson.J. Indian polls university press, 1992.

Oring, Elliot. *Folk Groups And Folklore Geners: An Introduction .Logan; Utah: State University Press, 1986.*

Smith,J. Robert*.Festivals Celebration folklore and folk life. An introduction Chiago: The University of Chicago Press, 1972.*

Solomon G/Michale. “The Brief History of Entoto Hamere Non Kidane Mihret Monastry’’.at Addis Ababa; Holy Trinity Theology College,B.AThesis 2007.

Taddese Tamrat.*The Abbots at Dabra Hayk 1248-1535 in journal at Ethiopian studies; Addis Ababa,1970. V8.*

Tegabu Beze. “The Ethiopian Claim on the Monastery Deir Essultain Jerusalem: 1850-1994.” Addis Ababa University, Department of History, MA Thesis 2002.

Tegbaru Adane.‘’A brief History of Dima Giorgis Monastery’’.Addis Ababa University Department of History BA.Thesis, 2002.

Zelalem Asefa. ‘’A brief History and Activities of Zeway Debre Tsion Monastery”’Add isAbaba; Holy Trinity Theology College, B.A thesis,2001.

## ዐባሪዎች

## ዐባሪ አንድ ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች

### ተረክ አንድ

*ልጆቼ ሆይ! በሉ ይህችን ቅድስት ቦታ አደራ ሰጥቻችኋለሁ። በኋላ ዘመን ታላቅ ቦታ ትሆንላችኋለች፤ አጋንንት ይወገዱባታል፤ የብዙ ቅዱሳን ዐጽም ያርፍባታል፤ ታላላቅ ነገሥታትና ጳጳሳት ይሰግዱባታል፤ ብዙ መናንያን መጠጊያ ያደርጓታል፤ ቤተ መቅደሷም በወርቅና በብር ታጌጣለች። ያንድነት ገዳም ተሻሽሎ ይቋቋምባታል፤ ብለው ተንብየው እግዚአብሔር ወዳዘዛቸው ቦታ ሄደዋል።*

### ተረክ ሁለት

*አባ ሊባኖስ ደብረ ሊባኖስ እያሉ ጌታ በመልአኩ ይገለጥና ይህ ቦታ ያንተ አይደለም።"እዚህ ቦታ የሚቀመጥ ከፀሓይ ሰባት እጅ የሚያበራ ልጅ ይወለዳል" ሲላቸው እንዴ እኔ 7 ዓመት ሙሉ ደጅ እየጠናሁ በአቴን እንዴት አድርጌ እለቃለሁ? ቢሉ ላንተ አልተፈቀደም፣ በስምህ ግን ይጠራልሃል ስላላቸው አባ ሊባኖስ ረጅም ጉዞ አድርገው የአሁኗ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቦታ እንደደረሱ እና ገዳሟን እንደገደሟት ይነገራል (መሪጌታ ነቃዐ ጥበብ እና ሌሎች የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)።*

### ተረክ ሦስት

*በ12ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የግብጽ ተወላጅ የሆኑት ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት÷ከንጉሥ ላሊበላ ጋራዐብረው በመሆን ወደ ገዳሟ መጥተው፣ከጠበሏ ተጠምቀው፣በእንግድነት ዐድረው፣ ቦታዋንም ባርከው፣"ይህች ገዳም ከዚህም በላይ ታላቅ እና ስመጥር ትሆናለች፤ ከዚህ ወደ ታች የሚታየው ጫካ መናገሻ ከተማ ይሆናል" ብለው ተንብየዋል (ዲያቆን ፈቃደ፣ መጋቢት 7፣ 2009 ዓ.ም እና መርሶ ሕይወት መጽሔት)።*

## *ተረክ አራት*

*በዘጠነኛው (9ኛው) ክፍለ ዘመን ዮዲት የአክሱም ጽዮንን ቤተ መቅደስ ለማቃጠል መነሣቷ በታወቀበት ወቅት ንጉሡ አንበሳ ውድም ታቦተ ጽዮንን በምስጢር አሲይዘው ወደ ሸዋ በስደት በሄዱበት ወቅት በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም እንዳረፉ እና ታቦተ ጽዮንንም በቦታዋ (በገዳሟ) አሳድረው ሲሄዱ ለገዳሟ በርካታ ስጦታዎችን እንደሰጡ ጽሑፋዊ መረጃዎችና የቃል ማስረጃዎች እንዳሉ ይነገራል (አባ ኪዳነ ማርያም፣መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም፣ መርሶ ሕይወት መጽሔት፣ ነሐሴ 2003 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አምስት*

*አባ ሊባኖስ ለበርካታ ዘመናት ታቦቷ በሾላ ዛፍ ውስጥ ተሰውራ የቆየችበት አካባቢ በንብ ተከቦ እና ብርሃን በርቶበት በማየታቸው ጠጋ ብለው ይመለከታሉ፤ ከሾላው ዛፍ ላይም በሳንቃ የተዘጋ ክፍል ያስተውላሉ። በኋላም ያንን ሳንቃ ሲከፍቱ "ዝ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት" የሚል ጽሑፍ ያገኛሉ (መምሬ ልሳኑ፣ የካቲት 20፣ 2009 ዓ.ም፣ መርሶ ሕይወት መጽሔት)።*

## *ተረክ ስድስት*

*በአንድ ዕለት ነው በርግጥ ሰውዬው መነኩሴ መስሎ በገዳሟ ሲንቀሳቀስ ሰንብቷል። ሁሉም ደግሞ መነኩሴ ስለመሰላቸው ያዋሩታል፤ አብረውት ይውላሉ። በኋላ ላይ ግን ወደ ዕቃ ቤት በመግባትንዋያተ ቅድሳትን፣ የወርቅ መስቀሎችን በወገቡ ደብቆ ሊወጣ ሲል÷የገዳሟ የውጪ በር አላስወጣ ይለዋል። ይኼን እንጂ ብዙ ጊዜ እየተመላለሰ ለመውጣት ሲሞክር የተመለከቱት ሰዎች ሁኔታውን ለበላይ አካላት በማሳወቃቸው ሰውዬው ተይዞ፣ የደበቃቸውን ንዋያተ ቅድሳትም እንዲመልስ ተደርጎ ንዋያተ ቅድሳቱ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመልሰዋል። ይገርማል እኮ!ሰውዬው ወደ ገዳሟ ውስጥ ሲገባ መራመድ ይችላል፤ ሊወጣ ሲፈልግ ግን እግሩ አልራመድ እያለው ይቸገር ነበር፤ ይገርማል- የፈጣሪ ሥራ!(ሚያዚያ 8፣2009 ዓ.ም)።*

### *ተረክ ሰባት*

*የዕቃ ቤት ጠባቂው እንደ ወትሮው የመኝታ ሰዓት በመሆኑ ተኝቷል፡፡ዕቃ ቤቱ ግን በተመሳሳይ ቁልፍ ተከፍቶ ባንድ ሰው እየተዘረፈ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጠባቂው ይሄንን አላየም፡፡ በዚህም ወቅት እርሱእንደሚለው ቅድስት ድንግል ማርያምበብርሃን ልብሷ ተገልጣ ትከሻውን እየነካካች ተነሥ! ተነሥስ! ስትለው እንደነቃ እና ወደ ዕቃ ቤቱ ሲያመራ የዘረፈው ሰው ለመሄድ ሲል የዕቃ ቤት ጠባቂው ስለደረሰበት የሰበሰባቸውን ንዋያተ ቅድሳናት ትቶ መሮጡ ይነገራል፣ (መምሬ ልሳኑ ሚያዚያ 2፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

### *ተረክ ስምንት*

*ልጆቼ ሆይ! በሉ! ይህችን ቅድስት ቦታ አደራ ሰጥቻችኋለሁ፡፡ በኋላ ዘመን ታላቅ ቦታ ትሆናለች፤ አጋንንት ይወገዱባታል፤ የብዙ ቅዱሳን ዐጽምያርፍባታል፤ ነገሥታትና ጳጳሳት ያርፉባታል፤ ብዙ መናንያን መጠሪያ ያደርጓታል፡፡ ቤተ መቅደሷም በብርና በወርቅ አጊጣ ትታነጻለች፤ የአንድነት ገዳም ተሻሽሎ ይቋቋምባታል" (መምሬ ተዘራ፣መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም እና መርሶ ሕይወት መጽሔት)፡፡*

### *ተረክ ዘጠኝ*

*"ወዳጄ ኤልያስ ሆይ! ስምህን ጠርቶ ለጸሎት በቆምክበት በዚህች ቦታ የሚጸልየውን ፣ዝክርህን የሚዘክረውን፣የቆምክበትን መሬት የሚረግጠውን ዐስራት ሰጥቼሃለሁ፤ እንደ ወዳጄ ነቢዩ ኤልያስም ክብርህን አበዛዋለሁ፤ይህችንም ቦታ ጠለ ምሕረቴ አይለያትም፡፡ ብዙ አስደናቂ ተአምር እንዲሠራባትም አደርጋለሁ፡፡ ገዳሟንም ታላቅ እና ስመጥር ካደረካት በኋላ በዚህች ገዳም እንደ ሙሴ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ መላእክት ይቀብሩሃል መቃብርህም ስውር አደርግልሀለሁ ሲል ቃል ኪዳን መግባቱ ይነገራል(መምሬ ተዘራ፣ መጋቢት 4፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

## *ተረክ አስር*

*አባ ሊባኖስ ወደዚህች ገዳም ሲመጡ ባለ ወይባ 1000፣ ባለ ማቅ 1000፣ ባለ ደበሎ 1000 በአጠቃላይ 3000 ቅዱሳን አጅበዋቸው ነበር የመጡት፡፡ የተክለ ሃይማኖት መወለድ ራዕይ ተነግሯቸው ሲሄዱ 1000ዎቹ ቅዱሳን አጅበዋቸው እንደሄዱ ይነገራል (መምሬ ልሳነ ወርቅ መጋቢት 2009 ዓ.ም)፡፡*

## *ተረክ አስራ አንድ*

*ኀይለ ሥላሴ አንድ ባህታዊን ወደ ኢየሩሳሌም ይዤህ ልሂድ ይሏቸዋል አይ ያንተ ቆርቆሮ ይጥለኛል የእኔ (በኢትዮጵያ) ፈረስ ይሻለኛል ይሏቸዋል (ፈረስ መልዐክ ነው) ከዛም በመንፈስ ቅዱስ ቀድመው እየሩሳሌም እንደደረሱና ዳዊት ይደግማሉ፡፡ ጃንሆይም ከአየር ወርደው ሲደርሱ ያገኟቸዋል ይደነግጣሉ በኋላም ሊመለሱ ሲሉ አሁንስ ይዤህ አልሄድም ቢሏቸው አይታክትህም እንዴ ብለው አሏቸው፡፡ (መምሬ ልሳነ ወርቅ መጋቢት 20፣ 2009 ዓ.ም)፡፡*

## *ተረክ አስራ ሁለት*

*ተማሪ ነበረች፤ ብዙ ጊዜ ብቻዋን ነበር የምታሳልፈው፤ በአንድ ዕለትም በደረሰባት አደጋ የሴትነት ክብሯን ከማጣቷም በተጨማሪ በኤች አይቪ ኤድስ ተጠቃች፤ ይህችም ልጅ በተግባር ቤት እየመጣች ሁሌም የንፍሮ ውሀ ትጠጣ ነበር፤ በኋላም ስትመረመር ከሕመሟ መዳኗ ተነገራት (አባ ኪዳነ ማርያም፣ ሚያዚያ፣6 2009 ዓ.ም)፡፡*

## *ተረክ አስራ ሦስት*

*ሴትዮዋ ሁለት ቀያይ ወንድ ልጆች አሏት፡፡ ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንደማትሄድ ገልጻልኛለች፡፡ ይሁንናአንድቀን ልጆቿን ለማዝናናት በወጣችበት ወቅት አንደኛው ወንድ ልጅ ድንገት ይታመምባታል፡፡ ሕመሙም ፈጣን ስለነበረ ባቅራቢያዋ ወደሚገኝ ሆስፒታል ብትወስደውም ወደ ከፍተኛ ሆስፒታል ይጻፍላታል፡፡ እዚያ በመሄድም ለዓመታት የበሽታ መከላከያ የሆነው የደም ሴሉ ዐልቋል በሚል በሆስፒታሉ ሕክምና ሲታገዝ ቢቆይም ሊሻለው አልቻለም፡፡ አንድ ቀን ነው፤ ሴትዮዋን አልግባባትም፡፡ እንዲያው አጠገቤ መጥታ ልጅሽ ይህንን ከታመመ*

*ለምን እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ይዘሽው አትሄጂም? ስትለኝ በፍጹም ቤተክርስቲያኗን አላውቃትም ነበርና ሰዎችን እያጠያየኩ በእዚያው እለት መጣሁ። ስመጣ የበዓሏ ቀን ነው አሉ። ብዙ ሰው አለ። እኔም ልጄን ይዤ እያለቀስኩ ከአንድ ከሚያስተምሩ አባት ዘንድ ሄድኩ። ምን ሆነሻል? ሲሉኝ ልጄ ያለበትን ሁኔታ ነገርኳቸው። ለሰባት ቀን አስጠምቂው ብለውኝ ወደ ቤት ተመለስኩ። በነጋታው ጠበሉ በር ላይ ስደርስ ለዓመታት ያልፈሰሰኝ ደም በመፍሰሱ ልጄን እንዴት እንደማስጠምቅ ጨንቆኝ ሳለ ወጣቱ አስጠማቂ አሁንም ድረስ እንደ ቤተሰብ ነን፤ ልጄን አስጠመቀልኝ። እቤት ስመለስ ግን ደሙ መፍሰስ አቁሞ ነበር። በኋላም ለሰባት ቀን ልጄ ሲጠመቅ በእጅጉ ተሠቃይቷል። ይህ የሆነው ለካ! ርኩስ መንፈሱ ከውስጡ ሊወጣ ሲል ነው። እግዚአብሔር ይመስገን! አሁን ድኖልኛል።ከዚያ የሥቃይ ጊዜ በኋላ ለ8 ዓመታት ከኪዳነ ምሕረት ተለይቼ አላውቅም፤ በወር በወር ልጆቼን ይዤ ዐድሬ ነው የምሄደው። (ምህረት ዘ ሕይወት የካቲት 6፣2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አስራ አራት*

*ለዓመታት በሕመም ስትሠቃይ የነበረች ወጣት የተለያዩ የሕክምና ተቋማት ጋራ ብትሄድም ከሕመሟ መዳን ባለ መቻሏ ተስፋ በቆረጠችበት ሰዓት በሰዎች ጠቋሚነት ወደ ኪዳነ ምሕረት በመምጣትና ጠበሏን በመጠመቅ በመጨረሻም ከሕመሟ መፈወሷን የሚተርክ ነው።*

## *ተረክ አስራ አምስት*

*እግሩ አልራመድ እያለው ማስቸገር የጀመረው በዐሥራዎቹ ዕድሜ ላይ እያለ ነበር፤ በኋላ ላይ ግን አልራመድ ማለት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነን ሕመም እያስከተለበት መጣ። በሰዎች ጠቋሚነት ከጎጃም ድረስ በመምጣት ጠበሏንበመጠመቅ፣ ከጠበሏ በመጠጣት፣ የሚያርፍበትም ስለሌለው ከቤተክርስቲያኗ ጥግ በማደር፣ ለዐሥራ ሦስት ዓመታት ያክል ሠርክ በመጸለይና ከጠበሉ ድኅነት እንደሚያገኝ በማመን ቆየ። አንድ ቀን አንደኛው እግሩ የተለየ መልክ በማሳየት፣ የሟሟ በመምሰል፣ በመጨረሻም በመፈንዳት እሾህ የበዛበት አውሬ መሰል ነገር ወጣለት። የኋላ ኋላም ቆሞ ለመሄድ*

*መቻሉንበአሁኑ ሰዓት በጢፍ መሸጥ የሚተዳደረውየዚሁ ታሪክ ባለቤት የሆነው ወጣት ይናገራል (አንተነህ ደግ ሰው፣መጋቢት 15፣ 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አስራ ስድስት*

*ሙስሊም ወንድምና እኅትናቸው። እኅቱ በሆድ ሕመም ስትሠቃይ ለበርካታ ጊዜያት በመቆየቷ ሰዎችን አጠያይቆ ወደ እዚህች ገዳም እንዳመጣት የልጅቷ ወንድም ይናገራል። እኅቱም ጠበል መጠጣትና መጠመቅ በመጀመሯ በየጊዜው የተለያዩ ስሜቶችን ታሳይ ነበር፤ አንዳንዴም ጩኸቷ እጅግ የበዛ በመሆኑ ድምጿን ሁሉ ዘግቷት ለረጅም ጊዜ ትቆይ ነበር። በኋላም በኪዳነ ምሕረት መሓሪነት በጠበሏ ተአምር ልጅቷ ብዙውንጊዜ ስትሠቃይ ቆይታ ከሆዷ ውስጥ እባብ መሰል ነገር እንደወጣላት ይነገራል (ሲራጅ ሁሴን የካቲት 2፣2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አስራ ሰባት*

*ልጅቷ በወንድሟ አስታማሚነት ከሕመሟ ለመዳን ጠበል ስትጠመቅ ብዙ ጊዜያት አሳልፋለች፤ ይሁንና ሕመሟ እየከፋ በመሄዱ እና የመዳን አዝማሚያዋ በመመናመኑ እቤቷ መዋል ጀምራለች፤ ያው ሞት አይቀርምና በመሞቷ ወንድሟ ያስገባችውን ቃል ኪዳን ለማክበር ወደ ቤተክርስቲያኗ እሬዋን ይዞ በመምጣት ሦስት ጊዜ ቤተክርስቲያኗን ሲያዞሩት ልጅቷ ተነሥታለች (ዲያቆን ፈቃደ የካቲት 21፣2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አስራ ስምንት*

*ይህች ገዳም በውስጧ ጥንታዊ የሚባሉ መጻሕፍቶች አሏት። በርግጥ ትክክለኛ ጊዜውን ማስቀመጥ ባይቻልም ግብረ ሕመማት፣ ሃይማኖተ አበው እና ተአምረ ማርያም ካሉት መጻሕፍቶች ሁሉ በተለየ ረጅም ዘመን ያሥቆጠሩ ናቸው። እንዲያውም እኮ አንዳንዶቹ አሁን ላይ አገልግሎት መስጠት ወደማይችሉበት ደረጃ እየደረሱ ነው (አባ ኪዳነ ማርያም ሚያዚያ 4፣ 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ አስራ ዘጠኝ*

*ጸናጽሉ የተገኘው ያኔ የገዳሟ ንብረቶች አባ ዘክርስቶስ የወይራ ዛፍ ቆርጠው፣ የሰው ቁመት የሚያህል ቆፍረው፣ርብራብ በመሥራት እውስጥ በመጨመር በላዩ ላይ ሌላ ርብራብ አድርገው አፈር አልብሰውት ሲሄዱ በድንገት ይህች (አሁን) የተገኘችው ጸናጺ መረሳቷን ይመለከታሉ። በኋላም ጉድጓዱን እንደገና መክፈት አልሆነላቸውምና ለብቻዋ መሬት ቆፈር፣ ቆፈር አድርገው ቀብረዋት ይሄዳሉ። ስለዚህ ነበር ጸናጺ ብቻዋን የተገኘችው (መምሬ ልሳነ ወርቅ፣ የካቲት 7፣ 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ ሃያ*

እቴጌ ጣይቱ በአንድ እለት ከአሽከሮቻቸው ጋራ በበቅሎ ሆነው ሲሄዱ ቦታው አሁን ሽቦ ግቢ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነው በጣም እረግረግ ስለነበር ከበቅሎ ወርደው በገረዶቻቸው እረዳትነት በእግራቸው በሚጓዙበት ወቅት እግራቸው ላይ ትርፍ ጣት ሆና ዘወትር ታማቸው የነበረችው ጣታቸው መቆረጧ እና ከህመማቸው መዳናቸውን በማየታቸው ጠበሏን እግረግጩ ነው የዳንኩት በማለት ግብር ጥለው ሰንጋ አርደው ካህናቱን አብልተዋል። በአካባቢው ያለው ውሃ ሰዎች አሁን የተለያዩ ግልጋሎት ይጠቀሙባቸዋል እንጂ ጠበል ነው(መምሬ ልሳነ ወርቅ መጋቢት 6፣2009 ዓ.ም)።

## ተረክ ሃያ አንድ

*ዲያቆን በሚያስቀድስበት ጊዜ ጓደኛውን በሚያይበት ጊዜ ቅዳሴውን በመርሳቱ የያዘው መስቀል ከግድግዳ አጣብቀው ከዚያም ከፍተኛ ጸሎት ተደርጎለት ከተላቀቀ በኋላ መነኮሳት እንዲቀድሱ ሆነው ቅዳሴው አበቃ ከዚያ በኋላ ግን ይህ ዲያቆን ቀራኒዮ የሚባል ቦታ ሄዶ ጫካ ውስጥ እራሱን እንዳጠፋ ይነገራል (መምሬ ልሳነ ወርቅ ካሴት ቁጥር 4A መጋቢት 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ ሃያ ሁለት*

በተመሳሳይም በተረክ ዐሥራ አራት ቅዱሳን ይኖሩበታል ተብሎ የሚታመነውን ዋሻ የአካባቢው ወጣቶች ጣልያን ወርቅ ደብቆበታል ብለው በተለያዩ መሣሪያዎች ሊያፈርሱ ሲሞክሩ ያመጧቸው መሣሪያዎች እንደተበላሹባቸው፣ ከመሀላቸውም አንደኛው ሰውዬ አደጋ እንደደረሰበት ይጠቀሣል (አባ ኪዳነ ማርያም፣የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)።

## ተረክ ሃያ ሦስት

*ይህቺ ገዳም ክርስትናን ለማጥፋት በተነሣው በአሕመድ ኢብን ኢብራሂምዘመን ምክንያት ተደርምሳ ስለነበር አሕመድ ኢብን ኢብራሂምሳያያት ነው ያለፈው። በኋላም ጠፍ ሆና ከቆየች በኋላ በገበሬው አማካኝነት  በተገኘችበት ወቅት ገበሬው ወደ ቤቱ ወስዶ በበረት ካስቀመጠው በኋላ የቤተሰቦቹ ጤና ሁሉ እየታወከ በበሽታ ስለተጠቁበት የክርስትና አባቱን ከእንጦጦ ማርያም አስጠርቶ ቤቱን እንዲረጩለት አደረገ። በኋላም ክርስትና አባቱ ሊወጡ ሲሉ አንድ ነገር ሣርስ ውስጥ አግኝቼ ከበረት አድርጌዋለሁ። የእናንተ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አሳያቸው። እርሳቸውም በበርኖስ ጠቅልለው ወደ እንጦጦ ማርያም ወሰዱት (አባ ኪዳነ ማርያም የካቲት፣20 2009 ዓ.ም)*

## *ተረክ ሃያ አራት*

*ሰውዬው በሚያርስበት ወቅት ሃይማኖታዊ ቁስን በማግኘቱ ለአንድ አባት በሚያሳይበት ወቅት ውሰድና እጎተራህ ውስጥ ክተተው ባሉት መሠረት እዚያ ውስጥ ይከተዋል። ከዚያ ቀን ጀምሮ ገበሬው በጎተራ ያለውን እህል ቢዝቀው፣ ቢዝቀው አይጎድልም። ይህንን በተከት በሠከረበት ወቅት ከጓደኛው ጋራ ሲጣላ እየተከራራ እና እየጮኸ እኔ እንዳንተ እንዳልመስልህ። ጎተራዬ እኮ! ብዝቀው፣ ብዝቀው የሚያልቅ ነው ብሎ ወደቤቱ ተመለሰ። ፈጣሪም በሰውዬው ተግባር በመቆጣቱ ጎተራውን ባዶ አደረገበት (መምሬ ልሳነ ካሴት ቁጥር 3A፣ መጋቢት 4፣2009 ዓ.ም)።*

### *ተረክ ሃያ አምስት*

አባ ልብነ ድንግል ከጎጃም መንገድ ከዋሻ ሚካኤል ከሚባል ቦታ መጥተው በገዳሟ (በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት) ከተሾሙ በኋላ ታቦታቱ ተቀብረውበታል የተባለውን ቦታ ሲያስቆፍሩ ታቦተ ልደታን ብቻ አገኙ። በዚህም ጊዜ ታቦተ ኪዳነምሕረትን እና ታቦተ ሚካኤልን ባለማግኘታቸው ምህላ ይዘው ሳሉ ከመቅደሱ ውስጥ አንድ አንበሳ መሬቱን ሲስም በራእይ ዐዩ፤ የካቲት 16 ቀንም ቦታውን ሲያስቆፍሩት የተሰወሩትን ታቦቶች አገኙ (መርሶ ሕይወት መጽሔት፣ ነሐሴ 2003 ዓ.ም)።

### ተረክ ሃያ ስድስት

ልጁ ወጣት ነበር፤የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነበር የሚሠራው። በኋላ ላይ ግን በደረሰበት የመኪና አደጋ የተነሣ መራመድ ባለመቻሉና በሕክምና ሊስተካከልለት ባለመቻሉ ወደ ገዳሟ በመምጣት ዘወትር ይጸልይ ነበር። እንዲያውም ሁል ጊዜ የሚጸልየው ደወሏ ሥር በመሆን ነበር። ፈጣሪ የውስጡን ሰምቶ እሑድለት ነው ትዝ ይለኛል። የበቁ አባት መተው እግሩን ሲያሻሹለትና ሲጸልዩለት እግሩ ቀጥ ዓለለት።

### ተረክ ሃያ ሰባት

*በ544 ዓ.ም ጥር 11 ቀን በዓለ ጥምቀትን ለማክበር የበረከት ኪዳነ ምሕረትንና የዐቢዩ መድኀኔዓለም ገዳም አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን በዋዜማው ዕለት ጥር 10 ቀን ታቦቶቻቸውን በረከት ላይ አውርደው፣ በድንኳን አስቀምጠው በሠሩት ዳስ ውስጥ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ፣ ሲበሉና ሲጠጡ፣ የማይገባ ሥራ ሲሠሩ የሰብሐተማሕሌቱ አጀማመርና የቅዳሴው መግቢያ ሰዓት በማለፉ የበቁ ባሕታዊ ተገልጸው የተናገሩት ይጠቀሣል (መሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ሚያዚያ 2፣2009 ዓ.ም)።*

### *ተረክ ሃያ ስምንት*

በገዳሟግቢ ውስጥ ውስጧ ሰይጣን ሰፍሮ ነው ተብላ ስትጮኽና ስትዘምር የነበረችውን ወጣት በመስቀል ግንባሯን በመምታት ልቀቅ! ብዬሃለሁ፤ ልቀቃት! ሲሉ ሰይጣኑ በልጅቷ ላይ ዐድሮ ብዙ ካሠቃያት በኋላ ሄጃለሁ፤ ለቅቄያታለሁ ሲል እንደተሰማ ነግረውኛል፤ በኋላም ልጅቷ ጤናዋ ተመልሶላት ወደ ገዳሟ ብዙ ጊዜ ትመጣ እንደ ነበር አጫውተውኛል (መሪጌታ ነቃዐ ጥበብ፣ መጋቢት 4፣2009 ዓ.ም)።

## *ተረክ ሃያ ዘጠኝ*

*በተረክ ዐሥራ ሁለት በገዳሙ አካባቢ የልማት ሥራን ሲሠሩ የመጡ ጣልያኖች በኪዳነ ምሕረት ዕለት ሲሠሩ ምእመናኑ ተው ቢሏቸውም ሥራቸውን በመቀጠላቸው ሥራውን ይሠሩ ከነበሩት መካከል አንዱ በድንገት መሞቱ ተተርኳል (አባ ኪዳነ ማርያም፣የካቲት 22/ 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ ሠላሳ*

*በተረክ ዐሥራ ሦስት እንዲሁ ጣልያኖች ወደ ገዳሟ በመግባት እና ከቤተክርስቲያኗ ጫፍ ላይ ዎፍ ዐርፋ በማየታቸው አንደኛው ይህችን ወፍ እገድላለሁ ብሎ በመተኮሱ አንድ ጣቱ ተቆርጣ መሬት ላይ መውደቋ ወፏም ምንም አለመሆኗ ይነገራል (አባ ኪዳነ ማርያም፣ ካሴት ቁጥር 1A የካቲት 22፣ 2009 ዓ.ም)።*

## *ተረክ ሠላሳ አንድ*

*ልጁ ወጣት ነበር፤የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነበር የሚሠራው። በኋላ ላይ ግን በደረሰበት የመኪና አደጋ የተነሣ መራመድ ባለመቻሉና በሕክምና ሊስተካከልለት ባለመቻሉ ወደ ገዳሟ በመምጣት ዘወትር ይጸልይ ነበር። እንዲያውም ሁል ጊዜ የሚጸልየው ደወሏ ሥር በመሆን ነበር። ፈጣሪ የውስጡን ሰምቶ እሑድለት ነው ትዝ ይለኛል። የበቁ አባት መተው እግሩን ሲያሻሹለትና ሲጸልዩለት እግሩ ቀጥ ዓለለት።*

# አባሪ ሁለት

## ከገዳሟ የተሰበሰቡ ፎቶዎች





አጥኚዋ መረጃ በመሰብሰብ ላይ እያለች






በገዳሟ ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ መጻሕፍቶች
















በገዳሟ የሚገኙ ልዩ ልዩ አልባሳት





ከእቴጌ ጣይቱ ብጡል እና ከንግስት ዘውዲቱ የተሰጡ ልዩ ልዩ አልባሳቶች ባለ ከፋይ ልብ አልማ ጥልፍ ስራ፣ ወርቀዘቦ ጥልፍ ስራ ባለ መርገፍ ጥልፍ ስራ፣ ነጭ ክር ጥልፍ ስራየተለያዩ ክሮች ጥልፍ ሥራዎች



ጠበሏ የምትገኝበት ሸለቆ



በገዳሟ ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚገኝ በአቡነ ቴዎፍሎስ የተሰሩ የወንዶች መነኮሳት መኖሪያ





በገዳሟ በየሳምንቱ ለምዕመናን የሚሰጥ ንፍሮ

ምዕመናኑ ንፍሮ ሲቀበሉ





ምዕመናኑ ንፍሮ ተቀብለው ሲሄዱ

በገዳሟ ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ

ጥንታዊ መስቀሎች

## ዐባሪ ሦስት

## ክፍል አንድ

## መረጃ ለመሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች

### ከገዳሚ ስያሜና መመሥረት ጋራ በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች

1. አመሰግናለሁ
2. ስምዎትን ማን ልበል
3. የእርሶ የስራ ድርሻ ምንድነው ቢነግሩኝ?
4. ገዳሚን የመሠረቱት ማን ናቸው? መቼ ነው የተመሠረተችው
5. የገዳሚ ስያሜ እንዴት እንደተሰጠ የሚያቁትን ቢነግሩኝ?
6. ገዳሚ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ከመባሏ በፊት ሌላ ስያሜ ነበራት?
7. ገደሚ ከመመሥረቷ በፊት ህዝቡ እምነቱ ምን ነበር (በምን ነበር የሚያመልከው)?
8. አባ ሊባኖስ ወደዚህች ገዳም ሲመጡ ይዘዋቸው የመጡ ነገሮች እንዳሉ የሚነገሩ ነገሮች ካሉ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ?
9. ስለ አካባቢው የሚነገሩ ነገሮች ትንቢቶች ከሉ

## ክፍል ሁለት

### ገዳሚ ከመመሥረቷ ጋራ በተያያዘ እና በጊዜ ሂደት የተፈጠሩ ክስተቶችን አስመልክቶ የሚተረኩትን ተረኮች ለመሰብሰብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

10. በቤተ ክርስቲያኗ ምን ያህል ድላቶች ናቸው ያሉት? በጥንቱና በአሁኑ ጊዜ የቁጥር ልዩነት አለ ካለ ቢነግሩኝ?
11. በቤተ ክርስቲያኗ ቅዳሴ የሚመራው በማን ነው?
12. ለዚህች ገዳም መመሥረት መነሻዋ ጠበሏ ናት ወይስ ሌላ ታሪክ ይኖር ይሆን
13. ስለ ገዳሚ ሥናነሣ ተያይዞ የሚነሣው ጽላቷ የተደበቀችበት ዋርካ ነች ከዚህ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ካሉ?
14. ቤተክርስቲያኗ አሁን ከተሰራችበት ቦታ ላይ ነው መጀመሪያም ተሰርታ የነበረው ወይስ ሌላ ቦታ ላይ ነበረች
15. ከቤተክርስቲያኗ ሥር የጠበሉ ምንጭ እንዳለ ይነገራል እርሶ ስለዚህ ነገር ቢያብራሩልኝ?
16. ቤተክርስቲያኗ በተለያዩ ዘመናት እየፈረሰች እንደገና እንደተሰራች ይነገራል በማን በማን ዘመን ነበር? ያሰሯትስ እነማን ናቸው?

17. ይህቺ ገዳም ስትነሣ አባ ሊባኖስ፣ ገበሬው እና እቴጌ ጣይቱ ተደጋግመው ይነሣሉ ለምንድን ነው?
18. ወደ ገዳሟ የተለያዩ ቅዱሳንና ነገስታት ይመጡ እንደ ነበር ይነገራል ከመጡት መካከል የሚያውቁትን ቢነግሩኝ? እንዲሁም ተናገሯቸው ስለሚባሉ ትንቢቶች የሰሙት ነገር ካለ?
19. ገዳሟ ቀደም ሲል የንፍሮ ገዳም እንደነበረች ይነገራል አሁን ላይ በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለችው? ለወደፊትስ የታቀደ ነገር አለ?
20. የገዳሟ አስተዳደር መዋቅር ምን ይመስላል?
21. በገዳሟ ምን ያህል መነኮሳትና መነኮሲስያት ይገኛሉ?
22. አሁን ላይ የሴቶቹ ገዳም በምን ዐይነት ሁኔታ ላይ ነው ያለው?
23. አመሠራረቱ ከወንዶቹ ገዳም እኩል እንደነበር ይነገራል እርሶ ምን ይላሉ?
24. ከመነኮሲያቱ ቁጥር መመናመን ጋራ ተያይዞ የታሰበ ነገር አለ?
25. የገዳሟ መተዳደሪያ ምንድነው? (የገቢ ምንጭ)
26. የገዳሟ ይዞታ አሁን ያላትንና ቀደሞ የነበራትን እያነጻጸሩ ቢነግሩኝ?
27. ይህንን ታሪካዊ ስፍራ ለማስተዋወቅ አሁን ላይ በገዳሟ እየተሰራ ያለ ነገር ምን ይመስላል?

## ክፍል ሦስት

### በገዳሟ ከሚገኙ ቁሶች ጋራ በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች

1. በገዳሟ ውስጥ ተመዝግበው ያሉትን ጥንታዊ ቁሶች (ንዋያተ ቅዱሳተ) ቢነግሩኝ
2. ከገዳሟ መመሥረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች አሉ?
3. ከተለያዩ ነገሥታት ለገዳሟ የተበረከቱ ቅርሶች አሉ? ካሉ በዝርዝር ቢነግሩኝ
4. ይሄንን ስፍራ ከሌሎች ቦታዎች ልዩ ሆኖ እንዲጠራ ያደርገዋል የሚሉት ቅርስ ካለ?
5. በገዳሟ ከሚገኙት መጻሕፍቶች አብዛኛውን ቦታ የሚይዙት የትኞቹ መጻሕፍት ናቸው?
6. በሙዚየሙ ያሉት ቅርሶች ውስጥ አሁን ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ካሉ ቢነግሩኝ? ካሉስ መቼ መቼ ነው ለአገልግሎት የሚውሉት?
7. የብራና መጻሕፍት እዚህ ይዘጋጅ ነበር?
8. አሁን እዚህ የሚገኙት የብራና መጻሕፍቶች ከምን ቆዳ የተሰሩ ናቸው?
9. ጥንታዊ ቅርሶቹ ድሮ ከነበረው ይዞታቸው አንጻር አሁን ያሉበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻሉ?

## ዐባሪ አራት
## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

### ሀ. ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | የሥራ ድርሻ | የሰጡት መረጃ ዐይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መምሬ ልሳነ ወርቅ | ወ | 90 | የቀድሞ የገዳሚ መምህር | ስለ ገዳሚ አመሠራረት ታሪክ፣ በገዳሚ ስለሚገኙ ቁሶችና ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽና በቪዲዮ ካሜራ |
| 2. | መርጌታ ነቃ ጥበብ | ወ | 76 | የቀድሞ የገዳሚ አስተዳዳሪ እንዲሁ የቅኔ ማህደት | ስለ ገዳሚ አመሠራረት እና ስለ ተበረከቱላት ስጦታዎች | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታወሻ |
| 3. | አባ ኪዳነ ማርያም አማኑኤል | ወ | 70 | የእቃ ቤት ኃላፊ እና የሙዚየሙን ንብረት ተቆጣጣሪ | ስለ ገዳሚ አመሠራረት እና በገዳሚ ስለሚገኙ ቁሶች | በቪዲዮና ካሜራ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 4. | አባ ኪዳነ ማርያም ወልደ አምላክ | ወ | 57 | መነኩሴ | ጽሑፋዊ መረጃ | በቪዲዮና ካሜራ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 5. | ቀሲስ ብርሃኑ ኢሳያስ | ወ | 37 | ጠቅላይ ቤተ ክህነት የቢሮ ኃላፊ | መረጃ ሰጪ በማገናኘት | በቪዲዮና ካሜራ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 6. | አባ ገብረ ሚካኤል ገብረ ኢየሱስ | ወ | 59 | ጠበል አጥማቂ | ስለ ጠበሉ ግቢ፣ በጠበሉ ግቢ ስላሉ ቅዱሳን፣ ስለሚጠብቋቸው እንስሳት | በመቅረጸ ድምጽ |
| 7. | መጋቢ ገ/ሚካኤል ወልደሰንበት | ወ | 47 | መጋቢ | ስለ ተአምር የተነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 8. | ዮሐንስ መንግስቱ | ወ | 29 | ሰብሳቢ | ስለ ሰንበት ትምህርት ቤት መረጃ እና ጽሑፋዊ መረጃዎችን በመስጠት | በቪዲዮ ካሜራ |
| 9. | ረድእ ገብረ ሕይወት ገ/ጻዲቅ | ወ | 39 | ረእድ | በገዳሚ ዙሪያ ስለሚነገሩ ተረኮች እና ቅዱሳን ይኖሩበታል ተብሎ የሚታመንበትን ዋሻ ፎቶ | በመቅረጸ ድምጽ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | በማንሳት | |
| 10. | አንተነህ ደግሰው | ወንድ | 33 | ጧፍ ሻጭ | ስለተደረገላቸው ተአምር | በመቅረጸ ድምጽ |
| 11. | ምሕረት ገ/ሕይወት | ሴት | 47 | ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ጸሐፊ | ለልጇ ስለተደረገላት ተአምር | በመቅረጸ ድምጽ |
| 12. | አቶ ተሰማ ገላው | ወንድ | 46 | የጠበል ግቢ ጠባቂ | ስለ ጠበሉ ግቢ መረጃ | በመቅረጸ ድምጽ |
| 13. | ሲራጅ ሁሴን | ወንድ | 27 | ሰራተኛ | ለእህቱ ስለተደረገላት ተአምር | በመቅረጸ ድምጽ |
| 14. | ዳንኤል ሰይፉ | ወንድ | 33 | የገዳሚ ዋና ጸሐፊ | በገዳሚ ስለሚነገሩ ትንቢታዊ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 15. | ፈቃደ ዐባይ | ወንድ | 34 | ዲያቆን | ሰንበት ት/ቤቱ ያሳተመውን መጽሔት በመስጠት | በመቅረጸ ድምጽ |
| 16. | ዘነብ አስረስ | ወንድ | 30 | ቀሲስ | ከገዳሚ ስለሚነገቱ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ |
| 17. | ሊቀ ዲያቆን አበበ አየለ | ወንድ | 27 | ዲያቆን | ስለ ሰንበት ት/ቤት ታሪክ | በመቅረጸ ድምጽ |
| 18. | አቶ ምስጋናው አደመ | ወንድ | 34 | የገዳሚ አገልጋይ | ስለ ገዳሚ አመሠራረት | በእጅ ማስታወሻ |
| 19. | ገብረ ማርያም መሐሪ | ወንድ | 41 | መነኩሴ | ስለ ገዳሚ አመሠራረት | በእጅ ማስታወሻ |
| 20. | ዲያቆን ፋንታሁን አየለ | ወንድ | 36 | የጠበል ኃላፊ | ስለ ጠበሉ አንዳንድ መረጃዎች | በመቅረጸ ድምጽ እና በእጅ ማስታወሻ |
| 21. | ማሜ አይተንፍሱ | ሴት | 34 | ጽዳት | በገዳሚ ፈውስን ያገኙች ስለ ተፈወሱ ሰዎች መረጃ በመስጠት | በመቅረጸ ድምጽ |

## ዐባሪ አምስት

### የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ንብረቶች

| ተ.ቁ | መጻሕፍቶች | ዐይነት | ብዛት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወንጌል ግዕዝ ትልቁ | በወርቅ የተለበጠ | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 2. | ወንጌል ግዕዝ ትልቁ | የተደጎሰ | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 3. | መጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ | በወርቅ የተለበጠ | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 4. | ተአምረ ማርያም ግዕዝና አማርኛ | የብራና | 4 | በብር ጌጥ የተለበጠ |
| 5. | ተአምረ ኢየሱስ ግዕዝና አማርኛ | የብራና | 2 | የተደጎሰ |
| 6. | አእማደ ምስጢር | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 7. | ግብረ ሕማማት | የብራና | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 8. | አርጋኖን | የብራና | 3 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ባለ ስዕለ |
| 9. | የአመት ስንክሳር | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 10. | ነገረ ማርያም | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 11. | ድርሳነ ኪዳነ ምሕረትና ሰይፈ ሥላሴ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 12. | ሃይማኖተ አበው | የብራና | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ግዕዝና አማርኛ |
| 13. | ግንዘት | የብራና | 3 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ግዕዝና አማርኛ |
| 14. | ገድለ ተክለሃይማኖት | የብራና | 2 | በጥሩ ሁኔታ የተደጎሰ |
| 15. | ገድለ መንፈስ ቅዱስ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነምልክቱ |
| 16. | ቅዱስ መጸሐፍ | የብራና | 3 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነምልክቱ |
| 17. | የድጓ መጽሐፍ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነምልክቱ |
| 18. | ምዕራፍ ድጓና ምዕራፍ ቅዱስ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ከነምልክቱ |
| 19. | ሰንበት አምኜ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነምልክቱ |
| 20. | ያመ ድጓ | የብራና | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነምልክቱ |
| 21. | ዝማሬ | የብራና | 1 | ያገለገለ |
| 22. | መስዋዕት | የብራና | 1 | ያገለገለ |
| 23. | ዳዊት | የብራና | 8 | ሁለቱ ከጥቅም ውጪ |
| 24. | ወንጌል ምልክትና ትርጓሜ | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 25. | መልክአ ኪዳነ ምሕረት | የብራና | 1 | ያገለገለ |
| 26. | ድርሳነ ኪዳነ ምሕረት | የብራና | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ግዕዝ |
| 27. | ዳዊት | የብራና | 1 | ግዕዝ በጥሩ ሁኔታ ያለ |

| ተ.ቁ | መስቀሎች | ዐይነት | ብዛት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ትልቅ ባለ መያር | የወርቅ | 1 | ሥነ ስቅለት |
| 2. | መካከለኛ ባለ መያር | የወርቅ | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 3. | ትልቅ ባለ መያር | የብር | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 4. | ትልቅ ባለ መያር | የወርቅ | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 5. | መካከለኛ ባለ መያር | የብር | 4 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 6. | መካከለኛ ባለ መያር | የብር | 1 | በደህና ሁኔታ ያለ |
| 7. | ትልቅ ባለ መያር | የንሐስ | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 8. | መካከለኛ ባለ መያር | የንሐስ | 1 | ለጠበል ቦታ ተሰቷል |
| 9. | አነስተኛ ባለ መያር | የንሐስ | 3 | 1 የተሰበረ |
| 10. | አነስተኛ የእጅ ባለ መያር | የወርቅ ቅብ | 2 | 1 የተሰበረ |
| 11. | አነስተኛ የእጅ ባለ መያር | የነሐስ | 3 | 1 የተሰበረ |
| ተ.ቁ | ሥዕሎች | ዐይነት | ብዛት | መግለጫ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ሥዕል በተለያየ መጠን | ያቡጀዲ | 41 | በጥሩ ሁኔታ ያለ |
| 2. | ሥነ ስቅለት ትልቁ | ያቡጀዲ | 1 | በጥሩ ሁኔታ ያለ ከነልብሱ |
| 3. | ሥዕል ትንንሽ | ያቡጀዲ | 6 | በጥሩ ሁኔታ ያለ የተለያየ መጠን |
| 4. | ሥዕል ትንንሽ | መንበረ ቅርፅ | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ የተለያየ መጠን |
| 5. | ሥዕል ጌጠኛ | የእንጨት | 2 | በጥሩ ሁኔታ ያለ 1ዱ ተከፋች |
| **ተ.ቁ** | **ጽላቶች** | **ዐይነት** | **ብዛት** | **መግለጫ** |
| 1 | ጽላተ ኪዳነ ምሕረት | ጥንታዊ | 1 | የእቴጌ ጣይቱ |
| 2 | ጽላተ ኪዳነ ምሕረት | በአደራ ያለች | 1 | የእቴጌ ጣይቱ |
| 3 | ጽላተ ልደታ | 1927 የገባች | 1 | የእቴጌ መነን |
| 4 | ጽላተ ሚካኤል | ጥንታዊ | 1 | የእቴጌ ጣይቱ |
| 5 | ጽላተ ጊዮርጊስ | ጥንታዊ | 1 | የእቴጌ ጣይቱ |
| 6 | ጽላተ ተክለሀይማኖት | ጥንታዊ | 1 | ዐፄ ምኒልክ |
| 7 | ጽላተ ኤሊያስ | ጥንታዊ | 1 | ዐፄ ምኒልክ |